# በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ
# የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች
# ትንተናና ግምገማ

ለድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የቀረበ ቴሲስ
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አማርኛን በማስተማር
ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ

በ
አቴነሽ ተገኝ
ሰኔ ፤ 1986

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች ትንተናና ግምገማ


በ

አቴነሽ ተገኘ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም


ጥናቱን ያጸደቁት

[illegible] (ዶ/ር)

አማካሪ

Marew Zewdie (D)

ፈታኝ

Haile Michael Aberra, Dr

ፈታኝ

መግለጫ :-

ይህ ቴሲስ የራሴ ወጥ ሥራ መሆኑንና በሌላ በየትኛውም ዩኒቨርሲቲ ያልቀረበ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ ።

ስም = አቴነሽ ተገኘ

ፊርማ = 

ቦታ = የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ ፲ 1986

2.12 ከተደራስያን የሚቀርቡትን አስተያየቶችና ጥያቄዎች በሚገባ በማ ዳመጥ ማስታወሻ በመያዝ ተጨባጭና መፍትሄ የሚሆኑ ሃሳቦችን አቅርብ::

2.13 ተደራሲያንን በጥሞና በሥነ ስርአት ስላዳመጡህ አመስግን::

## የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ መምሪያ

ክርክር ሁለት ሰዎች ወይም ሁለት ቡድኖች ዳኞች በመሰየም የሚያደር ጉት ስርአት ያለው ሙግት ነው::

1. የክርክር ዝግጅት፣
   1.1 ርእሱን በሚመለከት ከተለያዩ ምንጮች ሃሳብ መሰብሰብ::
   ለምሣሌ:-
      1.1.1 ከባለሙያዎች
      1.1.2 ከልዩ ልዩ ጽሁፎች
   1.2 በርእሱ መሠረት ጠይቀህ ካገኘሀውና ካነበብከው ለክርክርህ ጠቃሚ የሆኑትን ሃሳቦች በቅደም ተከተል አስተካክለህ ያዝ::
   1.3 ክርክርህን ለአድማጮች ከማቀረብህ በፊት ልምምድ አድርግ::
   1.4 ለክርክር ከመቀረብህ በፊት ሰብእናህን በስነ ስርአት አሟላ::

2. የክርክር አቀራረብ:-
   2.1 የመከራከሪያ ርእስህን ለአድማጮች አስተዋውቅ::
   2.2 የክርክርህን ፍሬ ሀሳቦች በቅደም ተከተል አቅርብ::
   2.3 ክርክር በምታደርግበት ጊዜ ረጋ ባለ መንፈስ በልበ ሙሉነት አቅርብ
   2.4 ከክርክርህ ጋር የማይስማማ እንቅስቃሴ አታድርግ
   2.5 ተቃዋሚህ የሚሰጠውን ሃሳብ በትክክል በማዳመጥ ማስታወሻም በመያዝ የተቃወሞ ሃሳብ አዘጋጅ::
   2.6 አነስተኛ ወይም ብጣሽ ወረቀት ለመያዝ ብትችል ማንበብህና መያዝህ እንዳይታወቅ አድርግ፣:
   2.7 የምታቀርበው ሃሳብ ወይም ማስረጃ በአድማጮችህ ችሎታ የተመጠነ ይሁን::
   2.8 ለክርክር የተሰጠህን የጊዜ ገደብ አክብር::
   2.9 በክርክር ወቅት ከርእስህ ዉጪ የሆነ ሃሳብ እንዳታቀርብ ጥንቃቄ አድርግ::
   2.10 ክርክርህን ስታበቃ አድማጮችህን አመስግን::/ገጽ 95/

## ማውጫ

ርእስ ገጽ


አህጽሮተ ጥናት ........................ i

ምስጋና ........................ ii

የሠንጠረዦና የግራፍ ማውጫ ........................ iii

ምዕራፍ ፩ : መግቢያ ........................ 1

1.1 የጥናቱ አላማ ........................ 1

1.2 የጥናቱ ጠቀሜታ ........................ 1

1.3 ወሰነ ጥናት ........................ 1

1.4 ሰበበ ጥናት ........................ 2

1.5 የቃላት መፍቻ ........................ 4

ምዕራፍ 2:— የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ........................ 5

2.1 ሀገርኛ ሥራዎች ........................ 5

የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ........................ 5

2.2 ንድፈ ሀሳባዊ መንደርደሪያዎች ........................ 8

2.2.1 መርሀ ትምህርት ........................ 8

_ ትርጉም ........................ 8

_ አስፈላጊነት ........................ 9

_ ዓይነት ........................ 11

_ አዘገጃጀት ........................ 13

2.2.2 የማዳመጥ ክሂሎ ........................ 18

_ የማዳመጥ ትምህርት ........................ 18

_ የማዳመጥ ይዘት ምርጫ ........................ 22

_ የማዳመጥ ይዘት ቅንብር ........................ 26

ምዕራፍ 3 :— የአጠናን ዘዴ ........................ 28

3.1 ይዘቶችን መለየት መተንተንና መገምገም ... 28

3.2 መጠይቆችን ማዘጋጀት ........................ 28

3.3 ናሙና መምረጥና መጠይቅን ማስሞላት ..... 29

ርእስ ገጽ


ምዕራፍ 4:— ጥናቱና ውጤት .................... 32
4.1 የይዘት ትንተናና ግምገማ ውጤት ....... 32
4.2 የመጠይቆች ምላሽ ................ 45
4.2.1 ከተማሪው መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ....... 46
4.2.2 ከመምህሩ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ....... 62
4.2.3 ከመርሀ ትምህርት ባለሙያው የተገኘ ምላሽ. 72
4.3 የመጠይቆች ምላሽ ትንተናና ንጽጽር .... 75

ምዕራፍ 5:— ማጠቃለያና ጥቆማ ................ 81
5.1 ማጠቃለያ ...................... 81
5.2 ጥቆማ ........................ 85

የዋቢ መጻሕፍት ዝርዝር .................... 86
አባሪዎች:— ......................... 89
አባሪ 1 : የተማሪው መጠይቅ ...........
አባሪ 2 : የመምህሩ መጠይቅ ...........
አባሪ 3 : የመርሀ ትምህርት ባለሙያው መጠይቅ.
አባሪ 4 : የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርትን አወቃቀር የሚያሳይ ሠንጠረዥ ...............
አባሪ 5 : ጥናቱ ያተኮረበትን የመርሀ ትምህርቱን ክፍል የሚያሳይ ሠንጠረዥ .......
አባሪ 6 : በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጸሀፍ ውስጥ የቀረቡ መምሪያዎች — የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር ከቀረቡ ይዘቶች ጋር ግንኙነት ያላቸው....
አባሪ 7 : በአዲስ አበባ የሚገኙ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ዝርዝር በፊደል ተራ ቀደም ተከተላቸው መሠረት.......

## በጽሁፍና በንግግር ላይ አስተያየት ማቀረብ።

አስተያየት የአንዱን ጽሁፍ ወይም የአንዱን ንግግር ጠንካራና ደካማ ጐን ከስሜታዊነት ነጻ በሆነ መንገድ ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ የራስን ሃሳብና አመለካከት የሚያቀርቡበት ዘዴ ነው:: በመሆኑም አስተያየት ከማቀረብህ በፊት የሚከተሉትን ነጥቦች አስተውል::

1. የቋንቋ አጠቃቀም
   1.1 የቃላት አመራረጥ
   1.2 የሀረጎች አመራረጥና አሰካክ
   1.3 የአረፍተ ነገሮች ቀንበር
2. የተለየ የአጻጻፍና የንግግር ስልት መከተሉ አለመከተሉን።
3. አስተያየት የምትሰጥበት ጽሁፍ ወይም ንግግር ግልጽነት ያለው መሆን ያለመሆኑን።
4. የጽሁፍ ወይም የንግግሩ ይዘት።
   4.1 የሚታመን ወይም የማይታመን መሆኑን።
   4.2 ከኅብረተሰቡ ስሜ ጋር ያለውን ዝምድና፣ ቀራኔና ተቀባይነቱን።
   4.3 የሃሳቡን ክብደትና ቀለት መመዘን።
5. የጽሁፍ የንግግሩ ዋና መልእክት ምን እንደሆነ በመመርመርና በማወቅ አስተያየት መስጠት::
   5.1 የጽሁፉን ወይም የንግግሩን መልእክት መገምገም።
   5.2 ጽሁፉ ወይም ንግግሩ የሚሰጠውን ትምህርት ከራስ አስተሳሰብ ጋር ማዛመድ።
   5.3 ከተለያዩ ምንጮች ሃሳቦችን በማሰባሰብ አስተያየትህን አጠናክር::

/ገጽ 99–100/

## አህጽሮተ ጥናት

በዚህ ጥናት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶችን ለመተንተንና ለመገምገም፣ ከተማሪዎች ፍላጎት ችሎታና ዝንባሌ ጋር የሚጣጣሙ መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ ተሞክሯል ::

ጥናቱም ይዘቶቹን በለማዳመጥ ክሂል ከተለያዩ ምሁራን ከተገኙ ንድፈ ሃሳቦችና ከተማሪዎች ፍላጎት አሰሳ ከተገኙ ውጤቶች ጋር በማገናዘብ ተጠንቷል :: ከጥናቱም የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል ::

- በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች ከተማሪዎቹ ፍላጎት አንጻር ሲታዩ በጣም አነስተኛና የተለያዩ የማዳመጥ አይነቶችን ያላካተቱ ናቸው ::
- ይዘቶቹ የተኛውን ክሂል ለማዳበር እንደተፈለገ በግልጽና በዝርዝር አያሳዩም :: ይዘቶቹም ሆኑ በየይዘቶቹ አንጻር የቀረቡት የክፍል ውስጥ ልምምዶች የተገለጹበት ቋንቋ ግልጽነት የጎደለው በመሆኑና ከዚህም ጋር የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን የሚያዳብሩ ይዘቶች በአንድነት በመቀረባቸው በየትኛው ክሂል ላይ ሊተኮር እንደተፈለገ አሻሚ ትርጉም ይሰጣሉ ::
- ይዘቶቹ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡበት ቅደም ተከተል የክብደት ደረጃቸውን የጠበቀ አይደለም :: በአንዱ ሴሚስተር በተከታታዩ በቀረቡትም ሆነ በአንደኛውና በሁለተኛው ሴሚስተር በቀረቡት ይዘቶች መካከል የክብደት ደረጃቸው አለመጠበቁ በግልጽ ታይቷል ::
- ይዘቶቹ ግልጽነት በጎደለው ሁኔታ በቃላት ተደባብሰው ቢገለጹም አንዳንዱ የማዳመጥ ዋናና ንዑሳን ክሂሎችን ለመዳሰስ ሞክረዋል፤ በዚህም በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማዳመጥ ትምህርት ሊተኮርባቸው በሚገቡ የማዳመጥ አይነቶች ላይ አተኩረዋል :: ይህም በተማሪዎች የፍላጎት አሰሳ የተገኘው መረጃ ከሚያሳየው የተማሪዎቹ አፍ መፍቻ ቋንቋ 92.6 % አማርኛ /ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ/ ከመሆኑ ጋር የሚጣጣምና በይዘቶቹ ላይ የታየ ጠንካራ ጎን ነው ::

በአጠቃላይ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ተገቢውን ትኩረት አላገኘም :: የማዳመጥ ክሂል በአጠቃላይ ሲታይ፣ በዝርዝር አላማና በይዘት ምርጫ ደረጃ ከመናገር ክሂል ጋር ተደርቦ በመቀረብ ረገድ ራሱን ችሎ መቀረብና በርካታ ይዘቶችና ልምምዶች ሊቀርቡበት ያስፈልጋል :: ከዚህም ጋር [illegible] ያስፈልጋል ::

## ም ስ ጋ ና

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስከጨረሰ ድረስ ውድ ጊዜያቸውን መስዋእት በማድረግ ረቂቁን በማረም ገንቢ ሃሳቦችን በመስጠት ለረዱኝ አማካሪዬ ለዶክተር ደጀኔ ለታ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ::

ለዚህ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዱ መጠይቆችን በማዘጋጀት ጊዜ መጠይቆችን በማረምና ገንቢ አስተያየታቸውን በመስጠት ለተባበሩኝ ለዶክተር ታደለ አጎሙ ፤ ይህን ጥናት በምሰራበት ጊዜ ሁሉ በሃሳብና በቁሳቁስ ረገድ ያጋጠሙኝን ችግሮች በመካፈል ለረዱኝና ላበረታቱኝ ለአቶ ወልደሰላሴ አቡቴና ለወይዘሮ ሣሌሀት አወል ፤ እንዲሁም ጥናቱን በረቂቅ አንስቶ እስከ መጨረሻው ተየባ ድረስ ያለ መታከት በመተየብ ለረዱኝ ለወ/ት በዛወርቅ ወ/ዮሐንስና ለወ/ት ፋጡማ አወል ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ::

ርእስ ገጽ

## የሠንጠረዥና የግራፍ ማውጫ


ሠንጠረዥ 1: የማዳመጥን ክሂሎ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ለማዳበር በወርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች ................ 30

ሠንጠረዥ 2: በየአጠቃላይ አላማው ሥር የቀረቡ ይዘቶች ብዛት ................ 32

ሠንጠረዥ 3: በየሴሚስተሩ የቀረቡ የማዳመጥ ይዘቶች. 34

ሠንጠረዥ 4: የተማሪዎች አፍ መፍቻ ቋንቋ ...... 46

ሠንጠረዥ 5: የተማሪዎች እድሜ ............. 46

ሠንጠረዥ 6: የተማሪዎች ጾታ .............. 47

ሠንጠረዥ 7: የማዳመጥን ክሂሎ ማዳበር ለሚለው አላማ የተሰጠ ምላሽ ................ 48

ሠንጠረዥ 8: ተማሪዎች የሚያዘውተሯቸው የማዳመጥ ተግባራት..................... 50

ሠንጠረዥ 9: የማዳመጥ ጉዳይ የአቀራረብ ዝንባሌ .. 51

ሠንጠረዥ 10: የተማሪዎች የማዳመጥ ችግር ....... 52

ሠንጠረዥ 11: የማዳመጥ ይዘቶች ጠቀሜታ ........ 54

ሠንጠረዥ 12: የማዳመጥ ችሎታ የመተማመን መጠን ... 55

ሠንጠረዥ 13: በቋንቋ ክሂሎች የመጠቀም ችሎታ .... 56

ሠንጠረዥ 14: የክሂሎች መዳበር የሚያስገኘው ጠቀሜታ መጠን ..................... 57

ሠንጠረዥ 15: የተማሪዎች ዝንባሌ :- የሚዳመጥ ጉዳይ. 58

ሠንጠረዥ 16: የተማሪዎች የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ... 60

ሠንጠረዥ 17: የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ ማጠቃለያ .................. 61

ርእስ | | ገጽ

ሠንጠረዥ 13 : በቋንቋ ክሂሎች የመጠቀም ችሎታ ......... 56
ሠንጠረዥ 14 : የክሂሎች መዳበር የሚያስገኘው ጠቀሜታ መጠን. 57
ሠንጠረዥ 15 : የተማሪዎች ዝንባሌ :— የሚዳመጥ ጉዳይ ... 58
ሠንጠረዥ 16 : የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ...... 60
ሠንጠረዥ 17 : የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ ማጠቃለያ. 61
ሠንጠረዥ 18 : የተማሪዎች የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጾች የመ
ረዳት ሁኔታ በመምህራን አይን ......... 62
ሠንጠረዥ 19 : መምህራን ተበረተ በጥ ተው የሚያስተምሩት ክሂል 63
ሠንጠረዥ 20 : የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የተመረጡ ዘርዘር
አሰማዎች ብዛት ................... 64
ሠንጠረዥ 21 : የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የተመረጡ ዴዘቶች
ብዛት ....................... 66
ሠንጠረዥ 22 : የተማሪዎች የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ በመምህራን
ምዘና ....................... 68
ሠንጠረዥ 23 : የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ በመምሀ
ራን ምዘና — ማጠቃለያ ............. 69
ሠንጠረዥ 24 : የተማሪዎች አዳምጦ የመረዳት መጠን ...... 70
ሠንጠረዥ 25 : በአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ችሎታ ለሌሎች ትምህ
ርቶች ያለው ጠቀሜታ ............... 71
ሠንጠረዥ 26 : የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ዴዘቶች የ
ብቃት ደረጃ በመርሀ ትምህርት ባለሙያው ምዘና 74
ግራፍ 1 : የዴዘቶችን ስርጭት የሚያሳይ መስመራዊ ግራፍ. 33

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## 2.2:- <u>ንድፈ ሃሳባዊ መንደርደሪያዎች</u>

### 2.2.1:- <u>ወርሀ ትምህርት</u>

<u>ትርጓሜ</u>

የተለያዩ ምሁራን በወርሀ ትምህርት ትርጓሜ ላይ የተለያዩ አስተያየቶችን ሰንዝረዋል ። በአብዛኛው ተቀባይነት ያገኘው ትርጓሜ:-

> ወርሀ ትምህርት በስርአተ ትምህርት ላይ ተመርኩዞ የሚዘጋጅ፣ የስርአተ ትምህርቱ ፍልስፍና በተግባር የሚተረጎምባቸው የመማርና ማስተማር መሠረታዊ ነገሮች በስፋትና በዝርዝር የሚቀርቡበትና፣ በዕቅድና ተከታታይነት ባለው ሁኔታ በየደረጃው ያሉት የትምህርት አላማዎች ግባቸውን የሚመቱበት ተግባራዊ መመሪያ ነው / ዳጊንና ስለሺ ተገኝ፣ 1986 : 37/ ።

የሚለው ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ስርአተ ትምህርትና ወርሀ ትምህርት የሚሉት ቃላት በተለያዩ ቦታዎች ለአንዱ ዓይነት አሳብ መገለጫነት ሲውሉ ይስተዋላሉ ። ዝርዝር የትምህርት ፕሮግራምን አሜሪካኖች "ስርአተ ትምህርት" ሲሉ፣ እንግሊዞች ደግሞ "ወርሀ ትምህርት" ይሉታል / አስተርጎ፣ ELT Documents : 1984:118: /

ስርአተ ትምህርትም ሆነ ወርሀ ትምህርት ሁለቱም ከትምህርት ፕሮግራም ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ናቸው ። በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ቃላቱ በብዙዎቹ የቋንቋ ምሁራን ዘንድ የተለመደውን -

> ስርአተ ትምህርት ለአንድ የትምህርት ፕሮግራም አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የፍልስፍና፣ የማህበራዊና አስተዳደራዊ ሁኔታዎችን አቢቶ የሚይዝ በጣም አጠቃላይ የሆነ አሳብ ነው ። በሌላ በኩል ወርሀ ትምህርት የትኞቹ የቋንቋው አካሎች ለትምህርት ይቀረቡ ብሎ የሚወስነውን የስርአተ ትምህርቱን ንኡስ ክፍል ይገልጻል / ለለን፣ ELT Documents : 1984 : 118:61 /

የሚለውን ትርጓሜ ይዘው ይገኛሉ ።

በርእሰ ትምህርት አጠቃላይ የትምህርት ግቦችን ሲይዝ መርሀ ትምህርት ደግሞ የአንዱ የተወሰነ ትምህርት ፕሮግራም አላማዎችን፣ አላማዎቹን ከግብ የሚያደርሱ ይዘቶችን፣ ይዘቶቹ በክፍል ውስጥ ተግባራዊ የሚሆኑበትን መንገድ የሚጠቁሙ የክፍል ውስጥ ክንውኖችንና በአላማው የተገለጸው ነገር ከግቡ መድረሱ የሚረጋገጥበት ምዘናን አካቶ ይይዛል ፡፡ በዚህ መሠረት መርሀ ትምህርት በርእሰ ትምህርቱ ላይ የሚመሠረት ሲሆን፣ የርእሰ ትምህርቱ ፍልስፍናዎች የሚተረጎሙትና ለተግባራዊነት የሚዘጋጁት ደግሞ በመርሀ ትምህርቱ አማካይነት በመሆኑ በመሀከላቸው ተደጋጋፊ ግንኙነት አለ ፡፡

<u>አስፈላጊነት</u>

የመርሀ ትምህርት አስፈላጊነትን በተመለከተ የተለያዩ አመለካከቶች አሉ ፡፡ አንዳንድ ምሁራን እንደ ብሪንና ካንደሊን /1984/ ያሉ፣ አስቀድሞ የተዘጋጀ መርሀ ትምህርት የመምህሩንና የተማሪውን የይዘት ምርጫ ነጻነት ስለሚገድብ አስፈላጊ አይደለም፣ ስለዚህ በክፍል ውስጥ በመምህሩና በተማሪው መሀከል በመማር ማስተማር ሂደት ለክፍሉ ተማሪዎች የሚስማማ መርሀ ትምህርት ይዘጋጃል ሲሉ፣ ሌሎች እንደ ዊደውሰንና ብሩምፊት /1984/ ያሉት ደግሞ መምህሩ በመርሀ ትምህርቱ ላይ ነጻነት ሊኖረው እንደሚገባ ሲስማሙ አስቀድሞ የሚዘጋጅ መርሀ ትምህርት ጊዜንና ገንዘብን በመቆጠብና መነሻና መድረሻን አስቀድሞ በማሳወቅ አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይደለም ይላሉ ፡፡ /አስቱርን ፣ ELT Documents 1984 : 118 : 7 - 10 /

"በክፍል ውስጥ የሚዘጋጅ መርሀ ትምህርት" የሚለው ጽንሰ ሃሳብ በተለይም የኅብረተሰባቸው የእድገት ደረጃ ዝቅተኛ በሆኑ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገሮች ለሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መምህራንና ተማሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ተግባራዊነቱ አጠያያቂ ሊሆን ይችላል ፡፡

...//10

ለምሳሌ በትምህርት ቤት የምናገኛቸው የተማሪዎች ዕድሜ በአስተሳሰብ ከመብሰሉና የሚያስፈልጋቸውን የቋንቋ ትምህርት ለይቶ ከማወቅ ጋር ሊኖር የሚችለው ሁኔታ፣ የትምህርት ባህል — ተማሪው ሁሉን ነገር ከመምህሩ የሚጠብቅ መሆኑ፣ ለነዚህና የመሳሰሉት ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ ::

አስቀድሞ የሚዘጋጁ መርሀ ትምህርት የትምህርቱን ግብና ከግቡ ሊያደርሱ የሚችሉ አማራጮችን አስቀድሞ በመምረጥ ጊዜንና ገንዘብን ይቆጥባል፣ ለትምህርት የሚቀርበው ይዘት ደረጃ በደረጃና በቅደም ተከተል እያደገ እንዲሄድ ያደርጋል፣ ለመምህሩ የሚያስተምርበትን፣ ለተማሪውም የሚማርበትን አላማና ግብ አስቀድሞ ማሳወቅ ወደ ተፈለገው ግብ እንዲገሰግሱ ይመራል ::

> በየጊዜው የቋንቋና ቋንቋ የማስተማር ቲዎሪዎች ውስብስብ እየሆኑ ከመምጣታቸውና የተማሪዎች ፍላጎት፣ ዝንባሌና ምኞት በጣም የተለያየ እየሆነ በመምጣቱ ጋር የሁለተኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት አስፈላጊነትና ጠቀሜታ እየጎላ መጥቷል :: ...... መርሀ ትምህርት በአሁኑ ጊዜ የሚታየው፣ መምህሩ በመርሀ ትምህርት አዘጋጅ እየታገዘ በተማሪዎች ፍላጎትና አላማ ለና በክፍል ውስጥ በሚካሄዱ የመማር ማስተማር ክንውኖች መሀከል መስማማትን የሚፈጥርበት መሣሪያ ሆኖ ነው / ያልደን ፣ 1987 : 85-86 / ::

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY



<u>አይነተ</u>

የተለያዩ የመርሀ ትምህርት አይነቶች በየጊዜው በተለያዩ ምሁራን ሲዘጋጁ፣ አገልግሎት ላይ ሲውሉና ሲተቹባቸው፣ አዳዲስ የቋንቋ ትምህርት ጽንሰ ሃሳቦች በረቀቁ ቁጥር ቀደም ብሎ ሲሰራባቸው የነበረት የመርሀ ትምህርት አይነቶች ሲሻሻሉና በሌላም ሲተኩ ቆይተዋል :: በተለያዩ የመርሀ ትምህርት አይነቶች መሀከል የሚኖረው መሠረታዊ ልዩነት የቋንቋ ትምህርት ይዘትንና የማስተማር ዘዴን በተመለከተ የሚታየው ልዩነት ነው :: ለምሳሌ በቅርፃዊ /አገባባዊ መርሀ ትምህርት በይዘት መረጣ ረገድ በቋንቋው የድምጾች፣ የቃላት፣ የዐረፍተ ነገር ቅንብር፣ በምእላዳች፣ በአገባብና በመሣሰሉት ላይ ሲያተኩር ዘዴውም እነዚህን ለተማሪው በማስጠናት ላይ ያተኮረ ነው :: በሌላ በኩል ደግሞ አሰቤያዊ/ተግባራዊ መርሀ ትምህርት ይዘቶቹ በቋንቋው ተግባቦታዊ አገልግሎት ላይ ያተኮሩና የቋንቋ ክሂሎችን የሚያዳብሩ ሲሆኑ፣ የማስተማር ዘዴውም ተማሪው በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ በቋንቋው መግባባት እንዲችልና በቋንቋው እንዲጠቀም በማለማመድ ላይ ያተኮረ ነው ::

የመርሀ ትምህርት አይነቶች በየጊዜው ቁጥራቸው እየጨመረ መጥተዋል :: በቅርፁ ላይ ያተኮረ፣ ትርጉም ላይ ያተኮረ፣ ማህበራዊ አገልግሎት ላይ ያተኮረ፣ መነጋገሪያ ርዕስ ጉዳይ ላይ ያተኮረ፣ ወዘተ... ::ዋና ዋና የሚባሉት የመርሀ ትምህርት አይነቶች በቅርፃዊ/ አገባባዊ፣ ... ሁኔታዊ፣ አሳቤያዊ/ተግባራዊ መርሀ ትምህርቶች ናቸው ::

እንግዲህ አይነተ መርሀ ትምህርት ሁሉንም የትምህርት አላማዎች ከግብ ማድረስ በማይቻልበት ሁኔታ የተለያዩ የመርሀ ትምህርት አይነቶችን በማቀናጀት ለመጠቀም የሚደረግ ጥረት እንዳለ ኑኤት ሲገልጽ :-

> በመርሀ ትምህርት ንድፍ ሃሳብ ምክንያት ሳይሆን
> በማስተማር የዕለት ተዕለት ሂደት ምክንያት አንዱ
> የተወሰነ አይነተ መርሀ ትምህርት ፍላጎታቸውን ሊያሟላ
> ባለመቻሉ፣ ከተለያዩ አይነት መርሀ ትምህርቶች
> የተውጣጣ መርሀ ትምህርት መጠቀም የብዙዎችን
> ፍላጎት እያሟላ መጥቷል /ኑኤት ፣ 1988 :111/ ::

እነ ሀቺንሰን፣ እስያን 1985ን በመጥቀስ እንዳስረዱት፡—

> ዋናው ጉዳይ የትኛው የመርሀ ትምህርት አይነት ይቀድም የሚለው ሳይሆን የተለያዩ መርሀ ትምህርቶችን/ ተግባራዊ፣ አሳቢያዊ፣ ሁኔታዊ፣ ርዕስ ጉዳያዊ፣ ሥነ ድምጻዊ፣ ጸርገማዊ፣ አገባባዊ፣ ከ ሂሳዊ/ አቀናጅቶ በሜት ሊሰጥ የሚችል የትምህርት ፕሮግራም ማዘጋጀት መቻሉ ላይ ነው፡፡ /ሀቺንሰንና ዎተርስ፣ 1987፡89/ ፡፡

ከሁሉም በላይ የመርሀ ትምህርት አይነት ምርጫን በተመለከተ ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ የታቀደውን አላማ ከግብ የሚያደርስ መርሀ ትምህርት ማዘጋጀት መቻሉ ነው፡፡ የመርሀ ትምህርት አይነት ምርጫም የሚወሰነው በቋንቋው ትምህርት አላማ ላይ ተንተርሶ ይሆናል፡፡

የትኛውን የመርሀ ትምህርት አይነት እንጠቀም ለሚለው ይህ ኛው ወይም ያኛው መርሀ ትምህርት ጥሩ ነው ብሎ በደፈናው መወሰን ትክክለኛ ውሳኔ አይሆንም፡፡ በአሁኑ ጊዜ የቋንቋ አገልግሎት ነጣጥሎ የማቀረቡ ሁኔታ እየቀረ፣ ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ የግንኙነትና የመግባባት ችሎታን ማዳበር የሚለው ትኩረት እያገኘ መጥቷል፡፡ ለዚህም በተማሪው ፍላጎት ላይ በመመስረት የተገባበት ክሂሎን የሚያዳብሩ ይዘቶችን የያዘ መርሀ ትምህርት የማዘጋጀቱ አስፈላጊነት አጠያያቂ አይሆንም፡፡

<u>አዘገጃጀት</u>

የቋንቋ መርሀ ትምህርት ለማዘጋጀት አንዳንድ ቅድመ ዝግጅቶችን ማድረግ ያስፈልጋል ፡፡ ዋና ዋናዎቹ የአገሪቱን የቋንቋ ፖሊሲ ማወቅ፣ ለትምህርት የሚቀርበው ቋንቋ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን አገልግሎት :- የጋራ መግባቢያ ፣ ለተወሰኑ ጉዳዮች የሚያገለግል፣ የማስተማሪያ ቋንቋ፣ ወዘተ... መሆኑን ማወቅ፣ የተማሪውን ዕድሜ፣ የትምህርት ዓራ፣ ፍላጎትና ዝንባሌ ማወቅ ናቸው ፡፡

የመንግሥት የቋንቋ ፖሊሲ ቋንቋው ለማን ? ለትምህርት ይቀረብ ? ለምን አላማ ይማሯት ? በትምህርት ቤት ምን ያህል ክፍለ ጊዜ ይመደብለት ? በሚያስፈልጉት የትምህርት መሣሪያዎች ረገድ ምን ያህል ወጪ ይመደብለት ? በሚሉት ውሳኔዎች ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል ፡፡ ለትምህርት የሚቀርበው ይዘት በኅብረተሰቡ ውስጥ ባለው የቋንቋ አጠቃቀም ላይ የተመሠረተና ተማሪው በኅብረተሰቡ ውስጥ ሊገለገልበት የሚችለውን የቋንቋ ገበራዊ ክሂሎች የሚያዳብር እንዲሆን ቋንቋው በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚኖረውን አገልግሎት ማወቅ አስፈላጊ ነው ፡፡ የተማሪው ዕድሜ ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ፍላጎትና ዝንባሌ የመሣሰሉትን ማወቅ ለተማሪው የሚቀርብለትን ይዘት በመወሰን ረገድ፣ ከተማሪው ሥነ-ልቦና፣ ችሎታ፣ ፍላጎትና ዝንባሌ አንጻር ተስማሚና ተማሪው አጥቀም ላይ ሊያውለው የሚችል ልምምድ የሚቀርብበት ይዘት ለመምረጥ ይረዳል ፡ ፡

አንድ የቋንቋ መርሀ ትምህርት አዘጋጅ መርሀ ትምህርት ለማዘጋጀት ሲነሳ ከላይ የተጠቀሱትን መሠረታዊ ጉዳዮች በግንዛቤ ማስገባት ይኖርበታል ፡፡ ከዚህም ጋር መርሀ ትምህርት ሲዘጋጅ ተከታታይ የክንዋኔ ደረጃዎችን እንደሚከተል ማወቅ ይሻል ፡፡ ራቸርደስ፣ ታባ 1962ን በመጥቀስ እንዳሰፈረው የአንድ የተወሰነ ትምህርትን መርሀ ትምህርት የሚያዘጋጅ ባለሙያ የሚከተሉትን ደረጃዎች ሊከተል ይገባል፡ -

...// 14

1. የተማሪውን ፍላጎት ማጥናት ፣
2. አላማ መንደፍ ፣
3. ይዘት መምረጥ፣
4. ይዘት ማቀናበር ፣
5. የትምህርት ልምዱ መምረጥ፣
6. የትምህርት ልምዶችን ማቀናበር፣
7. ምን እንደሚገመገምና እንዴት እንደሚገመገም መግለጽ፣ / ሪቻርድስ ፣ 1990 ፣ 8 / ።

የቋንቋ ትምህርትን አላማና ይዘት ከመወሰን በፊት ተማሪው በቋንቋው በት/ቤትም ሆነ በኅብረተሰቡ ውስጥ እንዴትና ለምን ለምን ጉዳዮች እንደሚጠቀም ፍላጎቱን ማጥናት በመርሀ ትምህርት ዝግጅት ወቅት ቀዳሚ የሚሰጠው ተግባር ነው ። የፍላጎት ጥናት በሰፋት የሚታወቀው ቋንቋን ለተወሰነ ጉዳይ የሚማሩ ክፍሎችን ፍላጎት በማጥናት ቢሆንም በአጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት መስክም የፍላጎት ጥናት ማድረግ አበፈላ ጊነቱ ጠቀሜታው አየጎላ መጥቷል ።

> ተማሪው እንግሊዝኛን ለምን መማር ፈለገ ? የሚለው ጥያቄ ቋንቋውን ለተወሰነ አላማ ለሚማሩት ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ለሚማሩትም ምላሽ ማግኘት ያለበት ጥያቄ ነው ። ሁሉም ትምህርቶች ሊገለጽ በሚችል በአንዱ አይነት ፍላጎት ላይ የተመሠረቱ ናቸው ። ... የትኛውም ትምህርት በተማሪው ፍላጎት ጥንቱና ላይ መመስረት ይኖርበታል / ሀቺንሰንና ዎተርስ፣ 1987 : 53 /

...// 15

የተማሪውን ፍላጎት ማወቅ ሲባል ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን ይይዛል ። አንደኛው ተማሪው ቋንቋውን ለመማር ምን ማድረግ እንዳለበት፤ በቋንቋው ለመጠቀም እንዲችል ምን ምን እውቀቶችና ችሎታዎች እንደሚያስፈልጉት ማወቅ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚታየውን የቋንቋ አጠቃቀም ማወቅና በዚህም በመነሳት ለተማሪው የሚያስፈልገውን የቋንቋ አጠቃቀም ማወቅ ነው ። /ሀቺንሰንና ዎተርስ 1987 / ።

ስለ ተማሪው ፍላጎት በቀላሉ ማወቅ የሚቻል ባይሆንም መጠይቆችን አዘጋጅቶ በተማሪው በራሱ በማስሞላት፤ የቋንቋ መምህራንን ስለ ተማሪዎቻቸው ችሎታና ዝንባሌ በመጠየቅ፤ ቋንቋው በትምህርት ቤትና በሥራ መስክ እንዲሁም በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን አገልግሎት በማጥናት በተለያዩ መንገዶች መረጃ ማሰባሰብ ይቻላል ። በነዚህ መንገዶች መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ ከመረጃዎቹ በተገኘው ውጤት መሠረት የቋንቋ ትምህርት አላማ ይነደፋል ።

የተማሪውን ፍላጎት መሠረት አድርገው የተነደፉት አላማዎች ወደ ትምህርት ይዘት ይተረጎማሉ ። ማለት አላማውን በግቡ ለማድረስ ለተማሪው በተለያዩ ሁኔታ እየቀረቡለት ለምምዱ የሚያደርገባቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ይመረጣሉ ። ይዘት ምርጫንና ቅንብርን አጣምሮ ይይዛል ።

ለተማሪው የሚቀርበው የትምህርት ይዘት አመራረጥና ቅንብር በመርሀ ትምህርት ዝግጅት ወቅት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው ።

> ቋንቋን የማስተማር ተግባር ' ጥሬ ' የመርሀ ትምህርት አይነት ከመምረጥ በላይ የሚሄድ ነው ። ከሁሉም በላይ ይዘትን ለመምረጥና ለማቀናበር ረጅም ጊዜና ጥረት ሊደረግ ይገባል / ኑይት፤ 1988 ፡ 111 / ።

የይዘት ምርጫ በመርሀ ትምህርት ውስጥ የሚቀርበው የቋንቋ ክህሎት የትኛው ነው ? የሚለውን ጥያቄ ሲመልስ የይዘት ቅንብር ደግሞ በመርሀ ትምህርት ውስጥ የሚቀርበው የቋንቋ ክህሎት በምን ቅደም ተከተል ይቀርባል ? ቅደም ተከተሉንስ ለመወሰን የምንጠቀመው መመዘኛ ምንድነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል ::

በትምህርት ቤት የሚቀርበው የቋንቋ ትምህርት ይዘት የተመረጠ መሆን ይኖርበታል :: ሁሉንም የቋንቋ ክህሎት እና ቀርበም :: ለይዘት ምርጫ መሠረት የሚሆነን የተማሪው ፍላጎት መሆኑ ተደጋግሞ ተነስቷል :: ለዚህም ነው የፍላጎት ስሰሳ ማድረግ የሚያስፈልገው :: የይዘት ብቃትና ተገቢነት ከሚመዘንባቸው መመዘኛዎች አንዱና የነኛው ከተማሪው ፍላጎት ጋር መጣጣም ነው ::ለትምህርት የሚቀርቡት ይዘቶች ለተማሪው ከሚሰጡት ጥቅምና ፍላጐትን ከማሟላታቸው አንጻር ይታያሉ :: ዊደውስን ስለዚሁ ጉዳይ ሜስኬንስ 1976ን ጠቅሶ ያሰፈረውን ብንመለከት :—

> ምን ማስተማር እንደሚገባ የመወሰን ሂደት
> ተማሪዎቹ በቋንቋው ለመግባባት በአብዛኛው
> የሚጠቀሙበት የትኛውን የቋንቋ ክህሎት ነው ?
> ለሚለው ጥያቄ ትኩረት በመስጠት ላይ
> የተመሠረተ ይሆናል :: ይላል / ዊደውሰን፣1990:131/::

የቋንቋ ትምህርት ይዘት ተማሪዎቹ በዕለት ተለት ኑሮአቸው ወይም ለአንዱ ለተወሰነ ጉዳይ ሊጠቀሙበት የሚያስፈልጋቸው መሆን ይኖርበታል ::ከቋንቋ ክፍል ውጭ አጥቅም ላይ የማያውሉትን የቋንቋ ትምህርት ይዘት ማቅረቡ እምብዛም አርባና አይኖረውም ::

የተመረጡት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች የተማሪውን ችሎታ መሠረት በማድረግ የክብደት ደረጃቸውን ጠብቀው ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከግልጽ ወደ ውስብስብ ደረጃ በደረጃ እያደጉ በሚሄዱበት ቅደም ተከተል ይቀናበራሉ ::

ይዘቶች በክፍል ውስጥ ተግባራዊ የሚሆኑባቸው የትምህርት ለምዶች ደን
ደው በነበረ ተሰቡ ውስጥ ባለው አገልግሎት ላይ ተመሥርተው ይዘጋጃሉ ::

ምሳሌ:- የደንደውን ባህላዊ አገላለጾች ለማስተማር ቢፈለግ፣ በኅብ
ረተሰቡ ውስጥ ለደስታ መግለጫ፣ ለሀዘን መግለጫ፣ለአክብሮት፣
ወዘተ... የሚውሉ ባህላዊ አገላለጾችን ምን እንደሚገልጹና
እንዴት እንደሚገለጹ ለማሣየት ምልልሶችን በማዘጋጀት፣ ተማሪ
ዎች ባህርያትን ወክለው እንዲለማመዱ በማድረግ ይዘቱ ተግባ
ራዊ ሊሆን ይችላል ::

ታይለር የትምህርት ለምዶች ጥርቅም ውጤት እንዲያስገኙ አንዱ
በሌላው ላይ ተመሥርተው መቀናበር አለባቸው ይላል ::

> ውጤታማ በሆነ መንገድ የተቀናበሩ የትምህርት
> ለምዶችን ለማግኘት ሦስት ዋና ዋና መመዘኛዎች
> አሉ :: እነርሱም:- ተከታታይነት፣ ተለጣጣቂነትና
> አንድነት ናቸው :: ተከታታይነት:- የአንዱን
> የትምህርት ለምድ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለተማሪው
> መቅረብ ያመለክታል፣ ተለጣጣቂነት:- ከተከታታይነት
> ጋር ይመሣሰላል :: ነገር ግን ተለጣጣቂነት እያንዳንዱ
> የትምህርት ለምድ አንዱ በሌላው በቀደመው ላይ
> ተመሥርቶ እያደገ የሚሄድ መሆኑን ያሳያል ::
> አንድነት:- አንድነት አንዱ የትምህርት ለምድ ከሌላው
> የትምህርት ለምድ ጋር ተደጋግፎና
> ተቀናጅቶ መቅረቡ የሚታይበት ነው
> / ታይለር፣ 1949 :83 / ::

ሌላው በመርሀ ትምህርት ዝግጅት ወቅት የሚተኮርበት ጉዳይ
ግምገማ ነው :: ይኸውም በአሳሣው የተገለጸው ጉዳይ ከግቡ መድረሱ
የሚታይበት ክፍል ነው ::ግምገማ በትምህርት ውጤት ላይ ያተኩራል ::
ትምህርቱን ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን የአሠራርና
የአስተሳሰብ ለውጥ አሳይተዋል ወይ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ከእያ
ንዳንዱ ትምህርት በኋላ ግምገማዎች ይኖራሉ :: ግምገማው በክፍል ሥራ፣
በቤት ሥራ ወይም በፈተና መልክ ሊሆን ይችላል : :

## ምዕራፍ 1 ፡ መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዓላማ

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ላይ የቋንቋው ትምህርት አላማዎች ተገልጸዋል፡፡ ከአላማዎቹ አንዱ የማዳመጥን ክሂል ማዳበር ሲሆን ይህም "የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ያዳብራል" ተብሎ ተገልጿል /ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1984ዓ*1/ ፡፡ ከዚህ አላማ ሥርም የተማሪውን የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች ያዳብራሉ ተብለው የተመረጡ ይዘቶች ቀርበዋል ፡፡ የዚህ ጥናት አላማ እነዚህ ይዘቶች የማዳመጥ ክሂልን የማዳበር ብቃታቸው ምን ያህል ነው ? ይዘቶቹ የተማሪውን ፍላጎት መሠረት አድርገው የተመረጡ ናቸው? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ መፈለግ ይሆናል ፡፡

### 1.2 የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የሚመረጥ ይዘት እንዴት ያለ መሆን እንዳለበት በተለያዩ ምሁራን የተጠቆሙትን ንድፈ ሃሳቦች መሠረት በማድረግ በዘጠነኛ ክፍል መርሀ ትምህርት ውስጥ የቀረቡትን የማዳመጥ ክሂል ይዘቶች ጠንካራና ደካማ ጎን ለይቶ ለማሣየት ይሞክራል፤ ይዘቶቹ ከተማሪው ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ መሆን አለመሆናቸውን በተጨባጭ ለማረጋገጥ ይሞክራል ፡፡ በተጨማሪም ለመርሀ ትምህርት ዝግጅት በመረጃነት ሊያገለግልና ለመሣሣይ ጥናት ማድረግ ለሚሹ መነሻ ሊሆን ይችላል የሚል እምነት አለ ፡፡

### 1.3 ወሰነ ጥናት

ይህ ጥናት በ1984 ዓ.ም በታተመው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ያዳብራሉ ተብለው በቀረቡ ይዘቶች ላይ ያተኮረ ጥናት ነው ፡፡ ጥናቱ በአዲስ አበባ በሚገኙ በመንግስት

---

* በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተጠቀሰው ጊዜ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር /እ.ኤ.አ/ ተብሎ ካልተገለጸ ወይም በውጭ ጸሀፍት ጽሁፍ ውስጥ የተጠቀሰ ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር የተገለጸ መሆኑ ይታወቅ ፡፡

በሕዝብና በግል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመደበኛ ትምህርት ላይ የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን፣ ቀደም ሲል ወይም ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የነበሩ ተገና የሆኑትን እንዲሁም የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት አዘጋጆችን ያካተተ ነው ::

## 1.4 ሰበበ — ጥናት

የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶችን በተመለከተ ቀደም ሲል አንዳንድ ጥናቶች ቢቀርቡም፣ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ለቋንቋው ትምህርት የተመደበውን የክፍለ ጊዜ መጠን፣ የመምህራኖችን የሥልጠና ደረጃ፣ የትምህርቱን አኳማና ይዘት በጥቅሉ የሚያካትቱ ናቸው ::

በተለያዩ ጊዜያት በተካሄዱ የቋንቋ ሴሚናሮችና ሲምፖዚየሞች ላይ፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ክፍል የአራተኛ ዓመት ተማሪዎች ለዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ ባቀረቧቸው ጥናቶች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘት ላይ የሚታዩ ችግሮች ተነስተዋል :: በነዚህ ጥናቶች ላይ በአብዛኛው የተተኮረባቸው በፈተናዎችና በመማሪያ መጽሀፍት ውስጥ በቀረቡ ምንባቦችና መልመጃዎች ላይ ነው ::

መማሪያ መጽሀፍቱም ሆኑ ፈተናዎቹ ሲዘጋጁ ለክፍሉ የተዘጋጀውን መርሀ ትምህርት መሠረት አድርገው ይዘጋጃሉ :: ስለዚህ በመጽሀፍቱና በፈተናዎቹ ላይ የተጠቀሱትን ድክመቶች ለማስወገድ አስቀድሞ መርሀ ትምህርቶቹን መመርመር፣ በመርሀ ትምህርቶቹ ላይ የሚታየውን ጠንካራና ደካማ ጎን ከተለያዩ አቅጣጫዎች ማጥናት ያስፈልጋል :: በመማሪያ መጽሀፍቱና በፈተናዎቹ ላይ የታየው ደካማ ጎን ምናልባትም መንስኤው መርሀ ትምህርቱ ሊሆን ይችላል :: ከዚህም ጋር የአማርኛ ቋንቋ ስርአተ

...//3

ትምህርትን አላማና ይዘት ከመረመሩ ጽሁፎች ለመረዳት እንደተቻለው በተለያዩ ጊዜያት በወጡት ስርአተ ትምህርቶች ውስጥ የማዳመጥ ክሂሉ እምብዛም ትኩረት አላገኘም ። ስለዚህም በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶችን ማጥናትና መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ።

...// 4

## 1.5 : የቃላት መፍቻ

የሚከተሉት የአማርኛ ትርጉሞች ለእንግሊዝኛው ስያሜ ይመጥናሉ በማለት በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተጠቀምኩባቸው ናቸው ናቸው ::

| | |
|---|---|
| Abstract | = አህጽሮት ጥናት |
| Communication | = ተግባቦት |
| Curricculum | = ስርአተ ትምህርት |
| Grammatical /Structural Syllabus | = ሰዋሰዋዊ / አገባባዊ መርሀ ትምህርት |
| Interactional Listening | = ለማህበራዊ ምሰሰስ ማዳመጥ |
| Notional /Functional Syllabus | = አሳብያዊ / ግብራዊ መርሀ ትምህርት |
| Post- Listening | = ድህረ ማዳመጥ |
| Pre- Listening | = ቅድመ ማዳመጥ |
| Syllabus | = መርሀ ትምህርት |
| Transactional Listening | = ለመረጃ መሻት ማዳመጥ |
| While- Listenning | = እያዳመጡ |

## ምዕራፍ 2:- የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

### 2.1 ሀገርኛ ሥራዎች

### የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት

በየጊዜው ተዘጋጅተው በሥራ ላይ የዋሉት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶች በመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፎች ውስጥ ከመማሪያ መጽሀፍትና ከፈተናዎች ጋር ሊኖራቸው ከሚገባ ዝምድና አንጻር በጥቅሉ ተዳስሰዋል ። ለአብነት ያህል፡ ደመቀ ብርሃኑ /1973/ "የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናና የስርዓተ ትምህርት /ከ1969 – 72/"፣ ሰለሞን ደበታ /1976/ "በአዲስ አበባ በአራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ1975 ዓ/ም የተሰጡ የአማርኛ ፈተናዎች ግምገማ" የሚሉ ይገኙበታል ።

በነዚህ ጽሁፎች ውስጥ የቋንቋ ትምህርቱን ይዘት በተመለከተ ይዘቶቹ ከተማሪዎቹ ገጠመኝ የራቁ፣ ለተማሪው ፍላጎት፣ ለዕድሜና አካባቢ ተገቢነት የሌላቸውና አቀራረባቸውም አንድ ዓይነት በመሆኑ የተማሪዎችን ስሜት የማይቀሰቅሱ መሆናቸው ተጠቅሷል ።

እንዲሁም በ1982 ዓ/ም ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት ሲምፖዚየም በቀረቡ ጥናታዊ ጽሁፎች ላይ የቋንቋው ምሁራን የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አላማዎችን፣ ስርአተ ትምህርቱንና የመማሪያ መጽሀፉን በተመለከተ አንዳንድ የግምገማ ነጥቦችንና አስተያየቶችን ሰንዝረዋል ። ከነዚህም ውስጥ ፈቃደ አዘዘ /1982 / ፤ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ስርአተ ትምህርት ለመጀመሪያ ጊዜ በ1994 ሲዘጋጅ የትምህርቱ ይዘት የሰዋሰው፣ የንባብና የድርሰት ትምህርት መሆኑን "የስርአተ ትምህርት ታሪክ በኢትዮጵያ" የተሰኘውን ረቂቅ ጽሁፍ በመጥቀስ አስፍረዋል /1982 :1 / ።

በመቀጠልም በ1950 የወጣው የአማርኛ ስርአተ ትምህርት ሶስት አላማዎች ሲኖሩት፤አንደኛው አላማ ከመስማት በስተቀር ሌሎቹን የቋንቋ ክሂሎች ለማስተማር እንዳሰበ /በረዝ የተጠመረ/ ፤ ሁለተኛው አላማ ትርጉም ላይ ያተኮረ ሆኖ ይህም ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጋር ብቻ የተያያዘ አለመሆኑን ፤ ሶስተኛው አላማም ብሄራዊ የሥልጣኔና የልማት አላማ እንጂ የቋንቋ ትምህርት አላማ ሊሆን እንደማይችል ገለጸዋል /ገፀ4–5/፤ በ1956፤ በኋላም በ1960 የወጡት ስርአተ ትምህርቶች ይዘትም መጠነኛ ለውጥ ቢኖራቸውም በመሠረቱ በ1950 እና 51 ስርአተ ትምህርቶች ውስጥ ከቀረቡት ይዘቶች ጋር ተመሳሳይነት እንዳላቸው ጠቁመዋል/ገጽ 9/:: በ1968 ተዘጋጅቶ እስከ 1984 ድረስ በሥራ ላይ የዋለውን የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ስርአተ ትምህርት በተመለከተ ፤ አምስቱ የቋንቋ ትምህርት አላማዎችን እንደያዘ በመጥቀስ ትኩረታቸውን በአምስተኛው አላማ ላይ ብቻ አድርገው አንዳንዱ የግምገማ ነጥቦችን ሰንዝረዋል ::

በዚህ የአማርኛ ስርአተ ትምህርትን ከጅምሩ አንስቶ እስከደረሰበት ድረስ በያኘ ጽሁፍ ውስጥ ከሚስተዋሉ ነጥቦች መሀከል አንዱ የማዳመጥ ክሂል በየጊዜው በወጡት ስርአተ ትምህርቶች ውስጥ ትኩረት ሳያገኝ መቆየቱ ነው ::ይህ ሁኔታ በሌሎች ጥናታዊ ጽሁፎች ውስጥም ተጠቅሷል :: ይልማ ከበደና አሸቱ ከበደ/1982/ ፤ ከ1966 ወዲህ የወጣውን ስርአተ ትምህርትና እሱን ተንተርሶ የተዘጋጁትን የማስተማሪያ መጽሀፍት በመረመሩበት ጽሁፋቸው ውስጥ እንደሚከተለው አስፍረዋል ::

> በስርአተ ትምህርቱ ውስጥ የተቀመጡት አላማዎች በአጠቃላይ መልካቸው ሲታዩ የቋንቋን አራቱን ክሂሎች ለማዳበር የተጻፉ በመሆናቸው ተገቢነት ያላቸው ቢመስሉም ፤ እነዚህን አራቱን የቋንቋ ክሂሎች /ማዳመጥ፤ መናገር፤ ማንበብና መጻፍ/ ለማዳበር በመማሪያ መጽሀፍቱ/ከ9ኛ–12ኛ ክፍሎች /በተከታታይ ምንባቦች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ተጽፈው አናገኛቸውም::በተለይ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር ያስችላሉ የሚባሉ ምንባቦችም ሆኑ መልመጃዎች አናገኝም:: ተዘንግቶ ይሆን?/ በረዝ የተጠመረ/ገጽ 30–31/::

ተስፋዬ ሸዋዬ ቀደም ሲል አ.ኢ.አ የጧጠር በ1976 የቋንቋ ሰርአተ ትምህርቶች በተሰኘው ጽሁፍ በኋላም በ1982 ዓ.ም ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት ሲምፖዚየም ባቀረቡት ጽሁፍ ውስጥ በየጊዜው በወጡት ሰርአተ ትምህርቶች ውስጥ የቀረቡትን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አላማዎች እንዴት ያሉ ጉዳዮች ላይ ያተኩሩ እንደነበሩ በዝርዝር አሳይተዋል :: እስከ 1970 ድረስ በኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች አማርኛን ለማስተማር በየጊዜው በተዘጋጁት ሰርአተ ትምህርቶች ውስጥ ይቀርቡ የነበሩትን አላማዎች ስናይ በአብዛኛው ለሰዋሰው፣ ንባብ፣ ጽሕፈት፣ ድርሰት፣ አነጋገር፣ ትርጉምና ትችት ላይ ያተኩሩ ነበሩ ::

/ተስፋዬና ታይለር ፤ 1976 አ.ኢ.አ ፤ ተስፋዬ ፤ 1982 / ::

በ1970 የወጣው ሰርአተ ትምህርት ቀደም ሲል ከነበሩት የተለየና ዝርዝር ያለ ሆኖ አላማው የንግግርን፣ የማዳመጥን፣ የንባብንና የጽሕፈትን ክሂሎቹ የምርምር ችሎታንና የሥነጽሁፍ ዝንባሌን ለማሳደግ የታቀደ መሆኑን አሳይተዋል ::/ተስፋዬ፣ 1982/ ::

ከነዚህ ጥናታዊ ጽሁፎች ለመረዳት እንደተቻለው ከረጅም ጊዜ አማርኛን የማስተማር ፕሮግራም ውስጥ የማዳመጥ ክሂል በአላማ ደረጃ እንኳ ሲጠራ የምናገኘው በ1970 በወጣው ሰርአተ ትምህርት ውስጥ ነው :: ከዚያ በፊት በነበሩት ሰርአተ ትምህርቶች ውስጥ ግን በአላማ ደረጃ እንኳ እንዳልተጠራ ነው :: ይህም የማዳመጥን ክሂል በማስተማር ማዳበር እንደሚቻልና እንደሚያስፈልግ ግንዛቤው እንዳልነበረና አነስተኛ ሥፍራና ግምት ተሰጥቶት መቆየቱን ያሳያል ::

አባሪ ፡ 7፡ በአዲስ አበባ የሚገኙ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በፊደል ተራ ቅደም ተከተላቸው መሠረት:-

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. ሊሴ ገ/ማርያም | ከፍተኛ | ሁለተኛ | ደረጃ | ት/ቤት |
| 2. መድኃኔዓለም | " | " | " | " |
| 3. ምሥራቅ አጠቃላይ | " | " | " | " |
| 4. ሽመልስ ሀብቴ | " | " | " | " |
| 5. ቀጨነ ቁሊፍ | " | " | " | " |
| 6. ቅድስት ማርያም | " | " | " | " |
| 7. ቦሌ | " | " | " | " |
| 8. ተግባረዕድ | " | " | " | " |
| 9. ናዝሬት | " | " | " | " |
| 10. ንፋስ ስልክ | " | " | " | " |
| 11. እቴጌ | " | " | " | " |
| 12. አብዮት ቅርስ | " | " | " | " |
| 13. አወልያ | " | " | " | " |
| 14. አየር ጤና | " | " | " | " |
| 15. አዲስ ከተማ | " | " | " | " |
| 16. ኢትዮጵያ ትቅደም | " | " | " | " |
| 17. ኤስ ኦ ኤስ | " | " | " | " |
| 18. እንጦጦ | " | " | " | " |
| 19. ከፍተኛ 4 | " | " | " | " |
| 20. ከፍተኛ 7 | | | | |
| 21. ከፍተኛ 12 | " | " | " | " |
| 22. ከፍተኛ 20 | " | " | " | " |
| 23. ኮልፌ | " | " | " | " |
| 24. ኮከበ ጽባሀ | " | " | " | " |
| 25. ወንድይራድ | " | " | " | " |
| 26. ዊንጌት | " | " | " | " |
| 27. የካቲት 12 | " | " | " | " |
| 28. ዳግማዊ ምኒሊክ | " | " | " | " |
| 29. ጥቁር አንበሳ | " | " | " | " |

/ ከክፍለ 14 ት/ቤቶች ጽህፈት ቤት ትምህርት ክፍል የተገኘ መረጃ/

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

መርሀ ትምህርት አንዴ ተዘጋጅቶ ለሁልጊዜው የሚያበቃ አይደለም ::በጥቅም ላይ ውሎ ከታየ በኋላ በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት የታየው ጠንካራና ደካማ ጎኑ በመምህራንና በተማሪዎች በሚሰነዘሩ አስተያየቶች አማካይነት፣ እንዲሁም ከኅብረተሰቡ ዕድገትና በየጊዜው ከሚፈለቁ አዳዲስ የቋንቋና የመማር ቴዎሪዎች አንጻር መሻሻል መለወጥና እንደገና መዘጋጀት ይኖርበታል ::

## 2.2.2 <u>የማዳመጥ ክሂል</u>

### <u>የማዳመጥ ትምህርት</u>

ማዳመጥ ከተናጋሪው አንደበት የሚወጡ ቃላትን ብቻ መስማት ማለት አይደለም :: ተናጋሪው ለማስተላለፍ የፈለገውን መልእክት በትክክል መረዳት ማለት ነው :: ይህን ለማድረግ ደግሞ የተለያዩ ሁኔታዎችን መገንዘብ ያስፈልጋል፤ በተናጋሪዎች መሀከል ያለ ግንኙነትን፣ ንግግሩ የሚካሄድበትን ቦታ፣ ጊዜና ሁኔታ፣ የተናጋሪውን ማንነት፣ የተናጋሪውን የድምጹን ቀሏጸ :- በአድናቆት ፣ በቁጣ፣ በማግባባት፣ ወዘተ... መናገሩን፣ የተናጋሪውንና የንግግሩን አላማና የመሣሰሉትን ሁኔታዎች መገንዘብ ይጠይቃል :: በትክክል አዳምጠናል ማለት የምንችለው ንግግሩን ከቀረበበት አውድ ጋር አገናዝበን ስናዳምጥ ነው ::

> ማዳመጥ የምንሰማውን ጉዳይ ልብ የማድረግና ከሰማነው ነገር ትርጉም ለማግኘት የመጣር ተግባር ነው :: የንግግር ቋንቋ ለማዳመጥ ተናጋሪዎች የተወሰኑ ቃላትን በተወሰኑ መንገዶችና በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ ሲጠቀሙ ምን ማለታቸው እንደሆነ ለመረዳት መሞከር አለብን እንጂ ቃላቶችን በጥሬው ብቻ መተርጎም የለብንም / እንደርወው፣ 1989፡1 /

በቋንቋው ተጠቃሚ ኅብረተሰብ ውስጥ የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀም ሁኔታዎችን አዘውትሮ ለማዳመጥ ሰፊ ዕድል ይኖራል ። ከዚህም የተነሳ በቋንቋው የማዳመጥ ችሎታ ከፍተኛ ይሆናል ። የአፍ መፍቻ ቋንቋን የማዳመጥ ሁኔታ ስንመለከት በኅብረተሰቡ ውስጥ በቋንቋው ለረጅም ጊዜ በመጠቀም ለማዳመጥ ከሚረዱ ዝግጁ ሁኔታዎች ጋር በቂ ልምምድ ስለሚኖር በአፍ መፍቻ ቋንቋ በቀላሉ ማዳመጥ ይቻላል ። ባይረን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማዳመጥን በተመለከተ፡-

> በአፍ መፍቻ ቋንቋችን በምናዳምጥበት ጊዜ የምናዳምጠውን በቀላሉ እንረዳለን ። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች አሉ ። 1. ለንግግር ቋንቋ ያለን ልምድ ከልጅነት ጊዜ ጀምሮ ሰፊ ስለሆነ - ከተለያዩ ተናጋሪዎች ጋር፣ በተለያየ ርእስ ፣ በተለያየ የቋንቋ አይነት በመጠቀም ሰፊ ልምምድ ስላለን፣ 2. ንግግሩን ለመረዳት በልምድ ያዳበርነው የተለያዩ አገባባዊ መገለጫዎች የተናጋሪውና የአድማጩ ግንኙነት፣ ዕድሜ፣ ጾታ፣ የንግግሩ ርእስ፣ የንግግሩ ቦታና ሁኔታ ፣ ወዘተ... እውቀት ስላለን ነው ። ይላል / ባይረን፣ 1986፡13/

እንደ እንደርውድ አባባል ደግሞ ሰዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ያለምንም ችግር ማዳመጥ እንደሚችሉ ጥርጥር የለውም / እንደርውድ ፣ 1989/ ሆኖም ግን አንዳንድ ጊዜ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚነገረውን ለማዳመጥ የምንቸገርበት ሁኔታም አንዳለ እንደርውድ ጠቁማለች ።

ባይረን ፤ በቋንቋው አፋቸውን ለፈቱ እንኳ ቢሆን ሁሉም የማዳመጥ ሁኔታዎች ቀላል እንዳልሆኑ ሲገልጽ ፡-

ተናጋሪውን ማየት በማንችልበት ሁኔታ ስክሪፕቱ
ገለጻን ማየት በለማንችል፣ የተወሰኑ የንግግር
ርእሶችና የቋንቋ አጠቃቀሞች የምንሰማውን ነገር
በቀላሉ እንዳንረዳ ሊያደርጉ ይችላሉ ይላል ::
/ባይረን ፣ 1986 : 13 /

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ማዳመጥ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ቢታወቅም እስከቅርብ አመታት ድረስ ተገቢውን ትኩረት ሳያገኝ ቆይቷል ::

> የቋንቋ ጥበብ ምሁራን አጠቃላይ የተግባቦት ክሂሎችንና የማሰብ ክሂሎችን በማዳበር ረገድ ማዳመጥ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ቀደም ባሉት ጊዜያት ጀምሮ አረጋግጠዋል :: ነገር ግን ማዳመጥ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርአተ ትምህርቶች ውስጥ እስከ 1970ዎቹ አመታት ድረስ ትኩረት ሳያገኝ ቆይቷል :: / ሮስት ፣ 1990: 10 / ::

የማዳመጥ ክሂል በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሆነ ተብሎ ትኩረት ተሰጥቶት ይዘት ተዘጋጅቶለትና እንዲሁም ከሌሎች ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበር በቀረቡ ይዘቶች ውስጥ ሊዳበር ይችላል ::

የቋንቋ ክሂሎች አንዱ በሌላው ውስጥ የሚገኙ እርስ በርስ የተሳሰሩ ቢሆኑም አንዱ አንዱን ክሂል ትኩረት ሰጥቶ ለማዳበር፣ የተፈለገውን ያህል ዳበሮም እንደሆነ ለመገምገም ክሂሎችን ነጣጥሎ ማየቱም አስፈላጊ ነው :: ማዳመጥን በተለከተ ከተማሪው የሚጠበቀውን የማዳመጥ ችሎታ ለመወሰን፣ በተለያዩ የማዳመጥ ዓይነቶች ተማሪውን ለማለማመድና የተለያዩ የማዳመጥ ዘዴዎችን ለተማሪው ለማስጨበጥ የሚያስችሉ ይዘቶች ለመማሪያ ክሂሉን በተናጠል ትኩረት ሰጥቶ ማየቱም ተገቢ ነው ::

> ቋንቋን በማስተማር ሂደት ማዳመጥ ከፍተኛ ድርሻ አለው፤ ስለዚህ በሌሎች ክሂሎች ውስጥ በአንድነት መገኘት አለበት የሚለው አመለካከት ተቀባይነት ሊያገኝ መጥቷል ። ይህ ማለት ግን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በማዳመጥ ላይ ያተኮረ ትምህርት ማቀድ አይቻልም ማለት አይደለም ። በአንድ ክሂል ላይ ማተኮር ማለት ደግሞ ሌሎቹን ክሂሎች አለማገናኘት አይደለም ።
> / አንደርወድ ፣ 1989:23 /

ክሂሎችን ለማዳበር በሚቀርብ የቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቋንቋ ክሂሎችን በተቀናጀ ሁኔታ የማዳበሩ አስፈላጊነት እንደተጠበቀ ሆኖ በእያንዳንዱ ክሂል የሚፈለገውን የችሎታ ደረጃ ለመወሰንና ትኩረት ለመስጠት ሲባል ክሂሎችን ነጣጥሎ ማቅረቡም ተቀባይነት አለው ።

የማዳመጥ ክሂል በየጊዜው እየዳበረ የሚሄድ እንጂ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ዳብሮ የሚያበቃ አይደለም ። ስለዚህ ተማሪው በየጊዜው በተለያዩ የማዳመጥ ሁኔታዎች ውስጥ በበቂ ሁኔታ መሣተፍ እንዲችል ክሂሉን የሚያዳብሩ ለምምዶች ማቅረብና በየጊዜው ክሂሉን ማሳደግ ያስፈልጋል : : በአፍ መፍቻ ቋንቋም ቢሆን የማዳመጥ ክሂል ሙሉ በሙሉ ሊዳብር እንደማይችል በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማዳመጥ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ያበረዳሉ ። ጥናቶቹን በመከለስ እንደ ርበንና ሊንች እንዳበረረት:-

> ቋንቋውን በአፍ መፍቻነት በሚጠቀሙት ዘንድ እንኳ ቢሆን የማዳመጥ ክሂሎች ሁል ጊዜ ሙሉ በሙሉ ሊዳብሩ አይችሉም ። በአብዛኛው የዚህ ችግር ምክንያቶች መረጃዎችን አዳምጦ የመረዳት ወይም መረጃዎችን ተርጉሞ የመጠቀም ክሂሎች ናቸው ። / እንደሮበንና ሊንች፣ 1988:60 / ።

በአፍ መፍቻ ቋንቋም ሆነ በሌሎች ያለውን የማዳመጥ ችግር በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ክሂሉን ትኩረት ሰጥቶ በማስተማር ማስወገድ ይቻላል :: አዳምጦ የመረዳት ችሎታን መቶ ፐርሰንት ማድረስ ባይቻልም በማስተማር፣ ለተማሪው አስፈላጊ የሆኑትንና ሊጠቀምባቸው የሚችልባቸውን ችሎታዎች ማስጨበጥ ይቻላል :: /በራውንና ሌ፣ 1983/::

የማዳመጥ ክሂል በየጊዜው እየዳበረ የሚሄድ ነው ስለዚህ ለአፍ መፍቻ ቋንቋም ቢሆን የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር ለምምዶች መዘጋጀትና ተማሪው ትኩረት ሰጥቶ እንዲለማመድባቸው የማድረጉ አስፈላጊነት አጠያያቂ አይደለም::

## የማዳመጥ ይዘት ምርጫ

የማዳመጥን ክሂል በትምህርት ቤት የማስተማር ዋነኛ አላማ፣ ተማሪው የሚሰማውን ነገር የመረዳት ፣ የመተርጎም፣ የመገምገምና የራሱን ምላሽ መስጠት የሚያስችለውን ክሂል ለማስጨበጥ፣ በማዳመጥ ችሎታው እንዲተማመንና በህብረተሰቡ ውስጥ ማዳመጥን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲጠቀም ለማስቻል በልዩ ልዩ የማዳመጥ አውዶችና የማዳመጥ ዓይነቶች ተግባራዊ ልምምድ መስጠት ነው :: በዚህም መሠረት የማዳመጥ ልምምዶችን በምናዘጋጅበት ጊዜ ተማሪዎች የሚጠቀሙበትን በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን የማዳመጥ ሁኔታና ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ የማዳመጥ ችግሮችን ከግምት ማስገባት ይኖርብናል ::

ኧር፣ በተለያዩ የማዳመጥ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ለማዳመጥ ትምህርት የሚሆኑ ይዘቶችን ማዘጋጀት እንደሚቻል ተጠቀማለች ተማሪዎች በህብረተሰቡ ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን የማዳመጥ ሁኔታ እንዲለማመዱ ከተፈለገ በነዚህ የማዳመጥ ሁኔታዎች ላይ የሚታዩ ዋና ዋና ባህርያትን ያካተተ ልምምድ ሊቀርብላቸው ይገባል :: ይኸውም :-

በህብረተሰቡ ውስጥ ስናዳምጥ:-

1. የምናዳምጥበት አላማ ይኖረናል፣ ስለምናዳምጠው ነገር ይዘት አስቀድመን እንገምታለን ::
2. ለምንሰማው ነገር ወዲያውኑ ምላሽ እንሰጣለን ::
3. የምናዳምጠውን ሰው እናያለን ::
4. የምንሰማውን ነገር ትርጉም የሚጠቁሙ አንዳንድ አካባቢያዊ መገለጫዎች ይኖራሉ ::
5. የሚሰማው ነገር አጠር አጠር ባሉ ምልልሶች የተከፋፈለ ይሆናል ::

6. አብዛኛው ምልልስ ያልታቀደ ምልልስ ነው ፡፡ ስለዚህ ከመደበኛ ንግግር በድግግሞሽ፣ በንግግር ድንቁነት ባህሪው፣ ንግግሩ በግልጽ እንዳይሰማ እንቅፋት በሚሆኑ ሁኔታዎችና በመደመጥ ባህሪው ይለያል ፡፡ /ኧር፣ 1984፡ 3—10/

የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር ይዘቶች ሲመረጡና የትምህርት ልምዶች ሲዘጋጁ ከላይ የተጠቀሱትን የማዳመጥ ሁኔታ ባህርያት በተለያዩ አውዶች አካቶ በማቀረብ ተማሪውን በህብረተሰቡ ውስጥ ከሚያጋጥሙት የማዳመጥ ሁኔታ ባህርያት ጋር ማለማመዱና በየማዳመጡ ሁኔታዎች ውስጥ በብቃት የሚያዳምጥ በትን ችሎታ ማስጨበጥ ይጠቅማል ፡፡

ለተማሪዎቹ የሚቀርቡ የማዳመጥ ይዘቶች ተማሪውን በተለያዩ የማዳመጥ ዓይነቶች የሚያለማምዱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ክሂሉን በማዳበር ሂደት የትኛው የማዳመጥ አይነት ይበልጥ ሊተኮርበትና ብዙ ልምምድ ሊቀርብበት ያስፈልጋል ለማለው ጥያቄ የተማሪዎችን ፍላጎት ማወቅን ይጠይቃል፡፡ ተማሪዎቹ ብዙ ጊዜ ሊገለገሉበት የሚያስፈልጋቸውን የማዳመጥ አይነት ለይቶ በማወቅ በዚያ ላይ የተመሠረተ ይዘት ማቅረብ ያስፈልጋል ፡፡

የማዳመጥን ክሂል በሚያዳብሩ ይዘቶች ውስጥ የተለያዩ የማዳመጥ ዓይነቶች ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ለማህበራዊ ምልልስ ማዳመጥና ለመረጃ መሸት ማዳመጥ ናቸው ፡፡/አንደርሰንና ሊንች ፣ 1988፤ ሪቻርድስ፣ 1990፤ ሮስት ፣ 1990/፡፡

ለማህበራዊ ምልልስ ማዳመጥ አላማው በቋንቋ ማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ የተናጋሪውን የመልእክት አቀራረብ መለየት ሲሆን፣ በምልልሱ ተሳታፊዎች መሀከል መግባባትን መፍጠር ላይ ያተኩራል ፡፡

ለመረጃ መሸት ማዳመጥ አላማው አዲስ መረጃን ማግኘት ሲሆን የሚተላለፈውን መልእክት በትክክል አዳምጦ መረዳት ላይ ያተኩራል ፡፡ በዚህ የማዳመጥ አይነት የሚቀርበው ነገር የትርጉም ግልጽነትና ቀጥተኛነት እንዲኖረው ይጠበቅበታል ፡፡/ሪቻርድስ ፣ 1990/፡፡

በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማዳመጥን ትምህርት ይዘት በተመለከተ ፣ ተማሪው የማህበራዊ ምልልስ ክሂሎችን በተለያዩ የማዳመጥ ሁኔታዎች በህብረተሰቡ ውስጥ ለማዳበር አይሎ ስራ ስለሆነ በትምህርት ቤት በይበልጥ ሊተኮርባቸው የሚገባው የመረጃ መሸት ክሂሎች ላይ መሆን አለበት ፡፡/አንደርሰንና ሊንች፣ 1988/፡፡

የማዳመጥ ክሂል በጥሩ ሁኔታ ሊዳብር የሚችለው አጠቃላይ አዳምጦ የመረዳት ችሎታንና ንኡሳን የማዳመጥ ክሂሎችን የሚያለማምዱ ይዘቶች በተቀናጀ መልክ ሲቀርቡ ነው ። ለተማሪው ሊቀርቡለት ስለሚገቡ የማዳመጥ ንኡሳን ክሂሎች በተመለከተ በርካታ ጸሀፍት የተለያዩ ዝርዝሮችን አመልክተዋል ። ከነዚህም መሀከል ፤

መንቢ ፤ 1978 ፤ ሀርመር ፤ 1983 ፤ ሊውስና ሂል ፤ 1986 ፤ ሪክሰን ፤ 1986 ፤ እና ሮስት ፤ 1990 ይገኙበታል ።

- ከረዥም ንግግር አበይ ሀሳብ ወይም ጭብጥ ማውጣት ፤
- የንግግሩን ተከታታይ ክፍሎች አስቀድሞ መገመት ፤
- ተጨባጭ እውነትንና የግል አስተያየትን መለየት ፤
- ተናጋሪው ሀሳብ ለማስተዋወቅ ፤ ርእስን ለመቀየር ፤ ለትኩረት ፤ ነጥቦችን ለማብራራትና ለማስፋፋት ፤ ተቃራኒ ሀሳቦችን ለመግለጽ የሚገለገልባቸውን ነጥቦች መገንዘብ ፤
- ለተናጋሪው ተገቢውን መልስ ማዘጋጀት ፤
- ተናጋሪው የሚሰጠውን መረጃ ስሜትን መገንዘብ ፤
- በንግግሩ ውስጥ የማይታወቁ ቃላትን ትርጉም ከአገባባቸው መረዳት ፤
- የተናጋሪውን አላማ መረዳት ፤
- የተደመጠውን ነገር ቀደም ብሎ ስለጉዳዩ ካለእውቀት ጋር ማገናዘብ ፤
- የተወሰኑ ዝርዝር ጉዳዮችን መረዳት ፤
- በግልጽ የተነገሩ መረጃዎችን አዳምጦ መረዳት ፤
- በግልጽ ያልተነገሩ መረጃዎችን ከአነጋገሩ መረዳት ፤
- የማይጠቅሙ መረጃዎችንና ድግግሞሽ በመለየት አሳጥሮ ማቅረብ ፤
- መረጃዎችን አዳምጦ ወደ ግራፍ ፤ ሠንጠረዥ ወይም ካርታ መተርጎም ፤
- ያዳመጡትን በራሳቸው አባባል ማቅረብ ፤
- ከሚያዳምጡት ውስጥ ፍሬ ሀሳቡን ለይቶ ማስታወሻ መያዝ ፤
- ከሚያዳምጡት ውስጥ ምክንያትና ውጤትን መለየት ፤
- ስለሚደመጠው ነገር አጠቃላይ ግንዛቤ መውሰድ የሚሉት ጸሀፍት

ከጠቀሟቸው የማዳመጥ ንኡሳን ክሂሎች መሀከል የሚገኙ ናቸው ።

በተማሪው ፍላጎትና ችሎታ ላይ ተመስርተው የሚመረጡት የማዳመጥ ንኡሳን ክሂሎችን የሚመለከቱ ይዘቶች በንግግር ወይም በምንባብ አውዶች ውስጥ በመካተት ተማሪው ክሂሎቹን እንዲያዳብርባቸው የሚያስችሉ ለምምዶች

የማዳመጥ ክሂል የሚዳብረው ልምምዱ በማድረግ ነው ፡፡ ተማሪው የሚደመጥ ነገር ስለቀረበለት ብቻ ያዳምጣል ማለት አይቻልም፡፡ ካዳመጠው ነገር አንዱ አይነት ምላሽ —የቃል ወይም የተግባር መስጠት አለበት ፡፡ አዳምጦ መረዳቱም ሊረጋገጥ የሚችለው በዚህ መንገዱ ነው ፡፡

ለተማሪው የሚቀርበው የማዳመጥ ተግባር ተማሪውን ሊያሳትፍ የሚችል መሆን ይኖርበታል ፡፡ ለዚህም የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር በሚቀርቡ ይዘቶች ውስጥ ተማሪው አዳምጦ የሚፈጽማቸው ተግባሮች ቢታቀፉ ጥሩ ነው ፡፡ አንደ ሸር አባባል የማዳመጥ ልምምዶች የበለጠ ውጤታማ የሚሆኑት በተግባር ላይ ሲመሰረቱ ነው ፡፡ ለተማሪው የሚቀርበው የማዳመጥ ተግባር ፡—

- አስቀድሞ የታቀደ አላማ ያለው ፣
- ተከታታይ የተማሪውን ትኩረትና የሚጠይቅ ፣
- ተማሪውን የሚያነቃቃ
- አንዱ አይነት ውጤት የሚያስገኝ ፣
- ተማሪው ሊያከናውነው የሚችል ፣
- ተማሪው /በቃል ወይም በተግባር /መልስ የሚሰጥበት መሆን አለበት /ሸር ፣1984: 25—29 /

የማዳመጥን ክሂል የሚያዳብሩ ልምምዶች ተማሪው የራሱን የማዳመጥ ዘዴ እንዲቀይስ የሚያለማምዱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ የማዳመጥ ዘዴዎች የሚደመጠውን ነገር በቀላሉና በትክክል ለመረዳት የሚያስችሉ መንገዶች ናቸው ፡፡ የማዳመጥ ዘዴዎች በማህበራዊ ምልልስ የማዳመጥ ሁኔታ ውስጥ፣ ስላዳመጡት ጉዳይ ማብራሪያ ለመጠየቅና በትክክል ማዳመጥን ለማረጋገጥ የምንጠቀምባቸው መንገዶች ሲሆኑ፤ በመረጃ መሻት የማዳመጥ ሁኔታዎች ውስጥ ደግሞ የተደመጠው መረጃ ቀደም ሲል ከሚታወቀው የተለየና አዲስ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የምንጠቀምባቸው መንገዶች ናቸው ፡፡/ርስት፣1990/

የማዳመጥ ዘዴዎች የማዳመጥን ተግባር ቀላል እንዲሆን ይረዳሉ ፡፡ ከማዳመጥ ዘዴዎች ሌላ በክፍል ውስጥ የማዳመጥ ልምምዶች ሲከናወኑ ተማሪው የማዳመጥ ተግባሮችን በቀላሉ እንዲያከናውን በቅድመ—ማዳመጥ፣ እያደመጡና በድህረ—ማዳመጥ የሚከናወኑ ተግባሮችን ከፋፍሎ ማቅረቡ ይረዳል፡፡በዚህም መሠረት ለተማሪው የሚደመጠውን ነገር ከማቅረቡ በፊት ቅድመ ማዳመጥ መመሪያዎችን መስጠት፣ የሚደመጠውን ጉዳይ ርዕስ ማስተዋወቅ፣ ከርእሱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የተወሰኑ መሪ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ በሚያዳምጥበት ጊዜ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ማሳወቅ የመሳሰሉት ፣ ለተማሪው በሚያዳምጥበት ወቅት ምን መፈጸም እንዳለበት ፣ የትኛው መረጃ ላይ ማተኮር እንደሚገባው በአጠቃላይ [illegible] በቀላሉ አዳምጦ

መረዳት ይችላሉ :: የማዳመጥ ትምህርት ይዘቶች በቅድመ—ማዳመጥ ፣ በአያዳመጡና ፣ በድህረ—ማዳመጥ ተግባሮች ተከፋፍለው ሲቀርቡ ትምህርቱ የተቀላጠፈና ውጤታማ ይሆናል ::

## የማዳመጥ ይዘት ቅንብር

ማንኛውም ለትምህርት የሚቀርብ ይዘት ቅንብርን በተመለከተ ተከታታይነትን፣ ተለጣጣቂነትንና አንድነትን ጠብቆ፣ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከግልጽ ወደ ውስብስብ እያደገ በሚሄድ ቅደም ተከተል መቀረብ ይኖርበታል :: በዚህ መሠረት ለተማሪው የሚቀርቡ የማዳመጥ ክሂሉን የሚያዳብሩ ይዘቶችም ከቀላል ወደ ከባድ ከግልጽ ወደ ውስብስብ እያደጉ የተማሪውን የማዳመጥ ክሂል ከጊዜ ወደጊዜ የበለጠ እያዳበሩ የሚሄዱ መሆን አለባቸው :: አንደርሰንና ሊንች የማዳመጥ ትምህርት ይዘት አቀርቦትን በተመለከተ:—

> ተማሪዎች በጣም ከባድና ውስብስብ ወደ ሆኑ ለምምዱ ከመገባታቸው በፊት ቀላል በሆኑ ለምምዶች ጥሩ ውጤት ማምጣትና መበረታታት ይኖርባቸዋል ይላሉ ::/አንደርሰንና ሊንች፣ 1988:44/

አንደርሰንና ሊንች ማዳመጥን ቀላል ወይም ከባድ ከሚያደርጉ ምክንያቶች መሀል የሚከተሉት ይገኛሉ ይላሉ ::

1. የሚደመጠው የቋንቋ አይነት
2. የሚደመጥበት አላማ ወይም ተግባር
3. የሚደመጥበት አውድ/አንደርሰንና ሊንች፣ 1988:46/

እንደነ አንደርሰን አባባል የሚደመጠው የቋንቋ አይነት ሲባል በሚደመጠው ምንባብ ወይም ንግግር ውስጥ ያለው የቋንቋ አቀርቦት ሁኔታ እንዴት እንደሆነ ያሳያል ::ይህም በሚደመጠው ምንባብ ወይም ንግግር ውስጥ መረጃዎች የተቀናበሩበትን መንገድ ፣ ከሚደመጠው ጉዳይ ጋር አዳማጭ ያለውን የተውወቀ መጠን ፣ የሚደመጠውን ነገር የግልጽነት ደረጃና የይዘት አይነት ያመለክታል:: የሚደመጠው የቋንቋ አይነት አዳምጦ የመረዳት ሁኔታን ከባድ ወይም ቀላል ያደርጋል ::

በማዳመጥ የሚፈጸሙ ተግባሮች ባህሪ ማዳመጥን ቀላል ወይም ከባድ ያደርገዋል ሲባል፣ የ[illegible] የማዳመጥ ተግባሮች ለተማሪው የተለያዩ የክብደት ደረጃ ያሏቸውን ለምምዶች ይዘው እንደሚቀርቡ ያሳያል ::ለምሳሌ [illegible]

ተከተለ ማስቀመጥ/ ካዳመጡ በኋላ ተፈላጊውን መረጃ መርጦ ከሚፈጸሙ ተግባሮች /ምሳሌ:ዋናውን ሀሳብ አሳጥሮ ማቅረብ/ይልቅ ቀላል ናቸው::እነዚህ ደግሞ በተራቸው በስሜታዊና በተጨባጭ አስተያየቶች መሀከል ያለውን ልዩነት መገንዘብን ከሚጠይቅ የማዳመጥ ተግባር ይልቅ ቀላል ናቸው ::

የማዳመጥበት አውዱ ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን ይይዛል :— የሚዳመጠው ጉዳይ የመረጃ ብዛትና የማዳመጥ ሂደት የሚፈጀው ጊዜ ናቸው ::

ማዳመጥን ቀላል ወይም ከባድ ሊያደርጉ የሚችሉ ምክንያቶችን ስንመረምር በይበልጥ ማተኮር ያለብን በሚደመጠው ጉዳይ የቋንቋ አቀርቦት ባህሪና በማዳመጥ የሚፈጸሙ ተግባሮች ባህሪ የክብደት ደረጃ ላይ ነው በማለት አንደርሰንና ሊንች አበክረው ያሳስባሉ ::
/አንደርሰንና ሊንች ፣ 1988/::

ከላይ የተዘረዘሩትን ማዳመጥን ቀላል ወይም ከባድ የሚያሰኙ ምክንያቶችን እንደመመዘኛ በመጠቀም፣ ለተማሪው የሚቀርቡ የማዳመጥ ክሂሎን የሚያዳብሩ ይዘቶችን የክብደት ደረጃቸውን የጠበቁና ከተማሪው ችሎታ ጋር የሚመጣጠኑ አድርጎ መምረጥና ማቀናበር ይቻላል ::

.../28

ADDIS ABABA UNIVERS
ILS LIBRARY

## ምዕራፍ 3 :- የአጠናን ዘዴ

### 3.1 ይዘቶችን መለየት ፣ መተንተንና መገምገም

ይህ ጥናት የይዘት ትንተና ጥናት ዘዴን በመከተል በ1984 ዓ.ም በታተመው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር ተመርጠው የቀረቡ የትምህርት ይዘቶችን ለይቶ በማውጣት ይዘቶቹ ክሂሉን ከማዳበርና የተማሪዎችን ፍላጎት ከማሟላት አንጻር ያላቸውን ብቃት በማጥናት ተንትኖና ገምግሞ አቅርቧል ::

ቦርግና ጋል /1989/ ከይዘት ትንተና ጥናት አላማዎች አንዱ ስለ ሚጠናው ጉዳይ ገላጭ መረጃ መስጠት መሆኑን ይጠቁማሉ :: ይህ ጥናት የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶችን በተመለከተ ገላጭ መረጃ ለመስጠት ይሞክራል :: ለዚህም ይዘቶቹን በመለየትና በመመደብ ስለማዳመጥ ትምህርትና ስለ ቋንቋ መርሐ ትምህርት በቀረቡ ንድፈ ሀሳቦችና በመጠይቆች አማካይነት በተገኘ መረጃ ላይ በመመስረት ይዘቶቹን ለመተንተንና ለመገምገም ሞክሯል ::

በዚህ የይዘት ትንተና ላይ ባተኮረ ጥናት ውስጥ የመጠይቆችን ምላሽ ለመተንተን የገላጭ የምርምር ዘዴ አሰራርም በጥምር ጥቅም ላይ ውሏል ::

ይዘቶቹ ከመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ተለይተው የተመረጡት በሁለት መንገዶች ነው ::ይኸውም: -1ኛ/በቋንቋው ትምህርት አጠቃላይ አላማ ሥር " የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ያዳብራሉ " ተብሎ የተገለጸውን አላማ ከግቡ ያደርሳሉ ተብለው የተመረጡ ይዘቶችን በመለየትና፣ 2ኛ/ለሌሎች የቋንቋ ትምህርት አላማዎች ከተመረጡት ይዘቶች መሀል አገረ መንገዳቸውን የማዳመጥን ክሂል የዳሰሱትን ይዘቶች በመለየት ነው :: የመጀመሪያዎቹ ይዘቶች በቀጥታ ክሂሉን ትኩረት ሰጥቶ ለማዳበር የተመረጡ ሲሆኑ ፣ ሁለተኞቹ ግን ማዳመጥ ለሌሎች ክሂሎች በተመረጡ ይዘቶች ውስጥ ሲዳበር የምናይባቸው ናቸው ::

በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ከላይ በተገለጹት በሁለቱም መንገዶች የቀረቡት ይዘቶች ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑ ናሙና ከመምረጥ ይልቅ ሁሉንም ይዘቶች ለመተንተንና ለመገምገም ተሞክሯል::

### 3.2 መጠይቆችን ማዘጋጀት

ጥናቱ የሚካሄድባቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ምን ያህል የተማሪውን ፍላጎት ያሟላሉ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እንዲቻል በተማሪዎች ፣ በመምህራንና በመርሀ ትምህርት አዘጋጆች የሚሞሉ ሶስት ዓይነት መጠይቆች

ተዘጋጅተው በነርሱም አማካይነት መረጃ ተሰበሰቧል ::

በሶስቱም መጠይቆች ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች በተቻለ መጠን ወደ ማዳመጥ ክሂል ያተኮሩ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል :: የተማሪው መጠይቅ የተማሪውን የተማሪውን ፆታ፣ ቋንቋውን የሚማርበትን አላማ ፤ ለትምህርቱ አቀራረብ ያለውን ዝንባሌ፣ የቋንቋ አጠቃቀሙንና የማዳመጥ ችሎታውን የሚዳስሱ ጥ ጥያቄዎችን ይዟል ፤ የመምህሩ መጠይቅ የመምህሩን ፆታ፣ የቋንቋው መምህር በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የማዳመጥን ክሂል በተመለከተ በቀረቡት ዝርዝር አላማዎችና ይዘቶች ላይ የሚኖረውን አስተያየት፣ ክሂሉን ለማዳበር የሚጠቀማቸውን ይዘቶችና የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ የሚያመለከቱ ጥያቄዎችን ይዟል ፤ የመርሀ ትምህርት ባለሙያው መጠይቅ ከያዛቸው ጥያቄዎች ውስጥ መርሀ ትምህርቱ ሲዘጋጅ መሠረት ያደረገው ምን እንደሆነ፣ የተማሪዎች ፍላጎት መጠናት አለመጠናቱን፣ አማርኛ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በስንተኛ ቋንቋነት እንደሚሰጥ፣ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የማዳመጥ ክሂልን የተመለከቱ ዝርዝር አላማዎችና ይዘቶችን ብቃት የሚጠይቁ ይገኛሉ ::
/ ስለጠቀሳሹ መረጃ አባሪ 1 2 ና 3 ን ይመለከቷል /::

ከመጠይቆች የተገኙ መረጃዎች በገላጭ የትንተና ስልት ከተተነተኑ በኋላ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ከቀረቡት ይዘቶች ጋር በማነጻጸር ይዘቶቹ ምን ያህል የተማሪውን ፍላጎት እንዳሟሉና የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር ምን ያህል ብቁ መሆናቸውን ለማገናዘብ ተሞክሯል ::

በትምህርት ቤቱና በኅብረተሰቡ ውስጥ ምልከታዎችን በማድረግ ለፍላ- ጎትና አሰሳው ተጨማሪ መረጃዎችን ማግኘት እንደሚቻል ቢታመነበትም ካለው የጊዜ እጥረት የተነሣ የተቀናበረና ስርአት ያለው ምልከታ ለማድረግ አልተቻለም ::

## 3.3 ናሙና መምረጥና መጠይቁን ማስሞላት

የማዳመጥን ክሂል በቀጥታ እንዲያዳብሩ የተመረጡትም ሆኑ በተዘዋዋሪ ክሂሉን የሚዳስሱት ይዘቶች ቁጥራቸው አነስተኛ ስለሆነ ለጥናቱ ሁሉም ተወስደዋል :: ቀጥሎ የቀረበው ሠንጠረዥ ጥናቱ ያተኮረባቸውን ይዘቶች ያሳያል:-
ሠንጠረዥ : 1 የማዳመጥን ክሂል በቀጥታና በተዘዋዋሪ ለማዳበር በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች ::/ለጠቀሳሹ መረጃ አባሪ 4 ን ይመለከቷል/

.../30

ሠንጠረዥ፡ 1 የ'.ዓመ. ክሂሎ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ለማዳበር በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች ::

| የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ለማዳበር የተመረጡ | ገጽ | ሌሎች ክሂሎችን ለማዳበር የተመረጡ | ገጽ |
|---|---|---|---|
| የውይይት ስርአት | 22 | በጭብጥና በስሜታዊ አስተያየት መካከል ያለው ልዩነት | 65 |
| የክርክር ስርአት | 23 | | |
| የጭውውት ስርአት | 24 | ፍሬ ሃሳቦችን በማስታወሻ መያዝ | 66 |
| የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት | 60 | አንድ ርእስ ጉዳይ በራስ አባባል ማቅረብ | 66 |

ለፍሻጉት አሰካ የተዘጋጁ መጠይቆችን ጥናቱ የሚመለከታቸው የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ፣ መምህራንና የመርሀ ትምህርት አዘጋጆች እንዲሞሉት ተመርጠዋል ::

መጠይቁን እንዲሞሉ የተመረጡ ተማሪዎችን ፊ.ተመለከተ ናሙና የተወሰደው በመጀመሪያ በአዲስ አበባ የሚገኙ ሃያ ዘጠኝ የመንግሥት፣ የህዝብና የግል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ዝርዝር በፊደል ተራ ቅደም ተከተላቸው በመመዝገብና በሰባተኛው ተራ ቁጥር ላይ የተመዘገበውን ት/ቤት በመምረጥ በእኩል ዕደል በሚ የናሙና አወሳሰድ ስልት አራት ት/ቤቶች ለጥናቱ ተመርጠዋል ::

እነርሱም :— 1. ቦሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
2. አየር ጤና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
3. ከፍተኛ 12 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
4. ዳግማዊ ምኒልክ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

ናቸው :: እነዚህ በአዲስ አበባ ከሚገኙ ሃያ ዘጠኝ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች 13.7 °/.ቱን ይይዛሉ ::/ት/ ቤቶቹን በፊደል ተራ ቅደም ተከተላቸው መሠረት የሚያሳይ ዝርዝር በአባሪ 7 ይመለከቷል/::

በናሙና ት/ቤቶች ከሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ ከእያንዳንዱ ት/ቤት ሰባ አምስት ተማሪዎችን በጠቅላላው ሦስት መቶ ተማሪዎችን፣ ከየክፍሉ በግምታዊ የናሙና አወሳሰድ ስልት በመምረጥና በአንድ ክፍል ውስጥ በመሰብሰብ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል :: ተማሪዎቹ መጠይቁን በሚሞሉበት ሰዓት በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል:: በናሙና ት/ቤቶች ከሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መሀከል መጠይቁ በተሰራጨበት ወቅትና ቀደም ሲል የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህር የሆኑና የነበሩ ሁሉም የመምህሩን መጠ

[illegible]

ሞልተዋል:: ለመርሀ ትምህርት ባለሙያው የተዘጋጀውን መጠይቅ በስርአተ ትምህርትና መምሪያ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት ቡድን አባላት ከሆኑ አራት ባለሙያዎች መሀከል ሦስት ሲሞሉ፣ አንደኛው በሥራ ብዛት ምክንያት መጠይቁን ሊሞሉ አልቻሉም ::

## ምዕራፍ 4 : ጥናቱና ውጤቱ

### 4.1 የይዘት ትንተናና ግምገማ ውጤት

የቋንቋ ክሂሎች በተናጠል ትኩረት ተሰጥቷቸውና አንዱ ከሌላው ጋር በመቀናጀት ሊዳበሩ ይችላሉ :: በዚህ የይዘት ትንተናና ግምገማ ጥናት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥ ክሂል፣ ክሂሉን ለማዳበር ሆን ተብለው በተመረጡት ይዘቶችና እንዲሁም ሌሎች ክሂሎችን ለማዳበር ተመርጠው ነገር ግን የማዳመጥን ክሂል አግረ መንገዳቸውን ለማዳበር በሞከሩት ይዘቶች አማካይነት ምን ያህል በብቃት ሊዳበር እንደሚችል እናያለን ::


በዚህ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ በእያንዳንዱ አጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት አላማ ሥር የቀረቡትን ይዘቶች ብዛት ስንመለከት የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ለማዳበር የቀረቡት ይዘቶች ቁጥር ከሁሉም አነስተኛ ነው ::

ሠንጠረዥ 2 ይህንኑ ያመለክታል::

ሠንጠረዥ 2 : በአጠቃላይ አላማው ሥር የቀረቡ የይዘቶች ብዛት

| አጠቃላይ አላማ | የይዘት ብዛት | |
|---|---|---|
| | ብዛት | % |
| ማዳመጥና መናገር | 4 | 7.5 |
| ማንበብ | 12 | 22.6 |
| መጻፍ | 19 | 35.8 |
| ሥነ ልሣን | 13 | 24.5 |
| ሥነ ጽሁፍ | 5 | 9.4 |

የማዳመጥና የመናገርን ክሂሎች ለማዳበር በተመረጡት ይዘቶች ብዛትና በሌሎች መሀከል ሰፊ ልዩነት ይታያል ። በይዘት ብዛት ከፍተኛው 35.8% ሲሆን ፣ ዝቅተኛው 7.5 % ለማዳመጥና ለመናገር ክሂሎች የቀረቡት ይዘቶች ናቸው ። ቀጥሎ የቀረበው መስመራዊ ግራፍ በአጠቃላይ አሳማው ሥር የቀረቡት ይዘቶች ከአማካይ የይዘቶች ቁጥር ወደላይና ወደታች ምን ያህል እንደሚርቁ ያሳያል ።




ግራፍ 1 ፡ የይዘቶችን ስርጭት የሚያሣይ መስመራዊ ግራፍ ፡

በየአሳማው ስር የቀረቡት ይዘቶች ስርጭት እንደሚያሳየን ለማዳመጥና ለመናገር ክሂሎች የተሰጠው ትኩረት ከሌሎች ክሂሎች የመጨረሻውንና ዝቅተኛውን ደረጃ ይዞና ከአማካዩ በታች ርቆ ነው ያለው ።

በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በሁለቱም ሴሚስተሮች ሆነ ተብሎ ክሂሉን ለማዳበር የቀረቡ አራት ይዘቶች ሲኖሩ ፣ ሌሎች ክሂሎችን እንዲያዳብሩ ተመርጠው እግረመንገዳቸውን ማዳመጥን ለማዳበር የሞከሩ ሦስት ይዘቶች አሉ ::

የሚከተለው ሰንጠረዥ በየሴሚስተሩ የቀረቡትን የማዳመጥ ይዘቶች በዝርዝር ያሳያል ::

ሰንጠረዥ 3 ፡ በየሴሚስተሩ የቀረቡ የማዳመጥ ይዘቶች

| ሴሚስተር | የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ለማዳበር የተመረጡ | ገጽ | ሌሎች ክሂሎችን ለማዳበር የተመረጡ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|
| አንደኛ ሴሚስተር | የውይይት ስርአት<br>የክርክር ስርአት<br>የጭውውት ስርአት | 22<br>23<br>24 | | |
| ሁለተኛ ሴሚስተር | የመንስኤና የውጤት ግንኙነት | 60 | በጭብጥና በስሜታዊ እስተያየት መካከል ያለው ልዩነት<br>ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝ አንድን ርእስ ጉዳይ በራስ አባባል ማቅረብ | 65<br>66 |

ከላይ በሰንጠረዥ የተመለከቱትን ይዘቶች ክሂሉን የማዳበር ብቃታቸውን ከማየታችን በፊት ለግንዛቤ እንዲረዳ የመርሀ ትምህርቱን አጠቃላይ መልክ መመልከቱ ጠቃሚ ነው ። ምክንያቱም ስለይዘት ስንናገር ይዘቱ የተመረጠለትን አላማ፣ ይዘቱ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ የሚጠቁሙን የመማር ማስተማር ስራ ክንውንን እንዲሁም ይዘቱ በተማሪዎቹ ተግባራዊ መሆኑ የሚረጋገጥበትን የግምገማ ክፍል ባናነካ አንቀርምና ነው ። / የመርሀ ትምህርቱን አጠቃላይ መልክ የሚያሳየውን ሠንጠረዥ በአባሪ 4 ይመለከቷል / ።

"<u>የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ አላማ</u>" የሚለው የመርሀ ትምህርቱ አካል፣ የቋንቋው ትምህርት ለተማሪው ምን ምን የቋንቋ ክሂሎችንና እውቀቶችን ለማስጨበጥ እንደታቀደ አጠቃላይ በሆነ መልኩ ያሳያል ። በዚህም መሠረት የሚከተሉት አጠቃላይ አላማዎች ቀርበዋል ፦

1. የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ያዳብራል ፤
2. የማንበብ ክሂልን ያዳብራል ፤
3. የመጻፍ ክሂልን ያዳብራል ፤
4. የስነ ልሣን እውቀትን ያዳብራል ፤
5. የስነ ጽሁፍ እውቀትን ያዳብራል ።

"<u>ዝርዝር አላማ</u>" በአጠቃላይ አላማው ስር የተገለጹት አጠቃላይ ክሂሎችና እውቀቶች እያንዳንዳቸው በዝርዝር ክሂሎችና እውቀቶች ተከፋፍለው የሚቀርቡበት ክፍል ነው ። ለምሳሌ "የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ያዳብራል" ለሚለው አጠቃላይ አላማ ፣ "ተጠየቃዊ አስተሳሰብን ያዳብራሉ" ፣ "የተወሰነን ሀሳብ በራስ አባባል የማቅረብ ዘዴን ያዳብራሉ" የሚሉ ዝርዝር አላማዎች ቀርበዋል ። የዝርዝር አላማው መገለጽ በተወሰነ የክፍል ደረጃ በየአጠቃላይ አላማው አንጻር ትኩረት የሚሰጥባቸውና ተማሪው እንዲያዳብራቸው የሚፈለጉትን ክሂሎች የትኞቹ እንደሆኑ ለይቶ ለማመልከት ይረዳል ።

"<u>ይዘት</u>" በዝርዝር አላማው ተለይተው የተጠቀሱት አላማዎች ወደ ቋንቋ ትምህርትነት የሚተረጎሙባቸው ይዘቶች የሚቀርቡበት ክፍል ነው ። ለምሳሌ ተጠየቃዊ አስተሳሰብን ለማዳበር የተመረጡት የትምህርት ይዘቶች 1. የውይይት ስርአት ፤ 2. የክርክር ስርአት፤ 3. የጭውውት ስርአት ናቸው ። ተማሪው በመወያየት፣ በመከራከርና ጭውውት በማድረግ ተጠያቃዊ አስተሳሰብን ያዳብራል ማለት ነው ።

• <u>የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ስራ ክንውን</u>፡ አንዱን ክሂል ለተማሪው ለማስጨበጥ በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ልምምዶችን ይዟል ። በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡት የክፍል ውስጥ ልምምዶች ለናሙና ያህል መሆናቸውንና መምህሩ በዚህ መልክ ሌሎች ተጨማሪ ልምምዶችን ማቀረብ እንደሚኖርበት ተገልጿል ። በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሥራ ክንውን ሥር የሚቀርቡ ልምምዶች በይዘቱ የቀረበውን የቋንቋ አካል ምን ማለት እንደሆነና የትኛውን ክሂል እንደሚያዳብር ይተረጉማሉ ።

• <u>ግምገማ</u> ፡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሥራ ክንውን ሥር የቀረቡትን ልምምዶች በማከናወን ተረዳጊውን አውቀት ወይም ክሂል ጨብጠው እንደሆነ የሚታይበት ክፍል ነው ። በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡት የግምገማ ነጥቦች ለናሙና ያህል መሆናቸውንና መምህሩ እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ አዘጋጅቶ መጠቀም እንደሚችል ተገልጿል ።

የመርሀ ትምህርቱ አንዱ አካል ከሌላው ጋር የተሳሰረ፣ አንዱ ሌላውን የሚተረጉምና አንዱ በአንዱ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ስለይዘቱ ስንናገር ሌሎችን የመርሀ ትምህርቱን አካሎችም ማንሳታችን የግድ ነው ። በዚህ መሠረት የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡትን ይዘቶች ለማየት አስቀድሞ ይዘቶቹ የተመረጡባቸውን አላማና ዝርዝር አላማዎች ጠቀለል ባለ መልክ እናያቸዋለን ።
/ ይህ ጥናት ያተኮረበትን የመርሀ ትምህርት ክፍል አባሪ 5 ላይ ይመለከቷል/ ።

የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ አላማ፡ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ያዳብራል፤ በሚል የማዳመጥ ክሂል ከመናገር ክሂል ጋር ተዳብሎ ቀርቧል ። ሌሎች ክሂሎች ለምሳሌ የማንበብ ክሂልና የመጻፍ ክሂል እያንዳንዳቸው ራሳቸውን ችለው በተናጠል አላማ ሲነደፍላቸው የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች ግን በአላማ ደረጃ በአንድነት የቀረቡበት ምክንያት ግልጽ አይደለም ። ወይም ምክንያት አልቀረበበትም ። ብዙ ጊዜ በገሃዱ አለም የማዳመጥ ተግባር ከመናገር ጋር ተያይዞ የሚገኝ ነው ። በቃላዊ ተግባቦት በአብዛኛው ሁኔታዎች ውስጥ ተናጋሪና አድማጭ ይኖራል፤ የተናጋሪውና የአድማጩ ድርሻ ይቀያየራል ፣ ማለት አድማጭ የነበረው ተናጋሪ፣ ተናጋሪ የነበረው ደግሞ በተራው አድማጭ ይሆናል ። ስለዚህ ክሂሎች ተዳብለው መቅረባቸው ለተማሪው ሁለቱም ክሂሎች እኩል በአንዴ ጊዜ ያስፈልጉታል በማለ ይሆን ? ሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች በአላማ፣ በዝርዝር አላማና በይዘት ምርጫ ደረጃ በተናጠል ሲቀርቡ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች ግን በአንድነት የቀረቡበት ምክንያት በመርሀ ትምህርቱ ላይ አልተገለጸም ። የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በአጠቃላይ አላማና በዝርዝር አላማ ሥር እያንዳንዳቸው ራሳቸው·

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ችሎቱ ቢቀርቡ የተሻለ ይሆናል ። ምክንያቱም በእያንዳንዱ ክሂል አንጻር ሊዳበሩ የሚገባቸውን ተፈላጊዎችን ንኡሳን ክሂሎች በግልጽ ለይቶ ለማስቀመጥና ትኩረት ሰጥቶ ለማለማመድ እንዲቻል ነው ። ቋንቋን በማስተማር ሂደት የቋንቋ ክሂሎች በአንድነትና በተናጠል ሊዳበሩ ይችላሉ ። በአንድ ክሂል ላይ ማተኮር ወይም አንዱን ክሂል ማዳበር ማለት ሌሎችን ክሂሎች በፍጹም አለማገባት ማለት አይደለም ።

እያንዳንዱ ክሂል በተናጠልና በጋራ ሊዳበር ይችላል፣/አንደርውድ፣ 1989/። በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሥራ ከንውን ላይ አራቱ የቋንቋ ክሂሎች በአንድ ላይ ተቀናጅተው ሊቀርቡ ይችላሉ ።በአላማ ፣ በዝርዝር አላማና በይዘት ምርጫ ላይ ግን እያንዳንዱ ክሂል በተናጠል ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ።

የቋንቋ ክሂሎች አንዱ በሌላው ውስጥ የሚገኙ፣ እርስ በርስ የተሳሰሩ ቢሆኑም እንኳ አንዱ ክሂል ትኩረት ሰጥቶ ለማዳበር ፣ የተፈለገውን ያህል ዳብሮም እንደሆነ ለመከታተል ክሂሎችን ነጣጥሎ ማየቱ አስፈላጊ ነው ። ማዳመጥን በተመለከተ፣ ከተማሪው የሚጠበቀውን የማዳመጥ ችሎታ ለመወሰን ፣ በተለያዩ የማዳመጥ አይነቶች ለማለማመድና የተለያዩ የማዳመጥ ዘዴዎችን ለተማሪው ለማስጨበጥ የሚያስችሉ ይዘቶችን ለመቀረጽ የሚቻለው ክሂሉን ከሌሎች ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ ከማቅረብ በተጨማሪ በተናጠልም ትኩረት ሲሰጠው ነው ።

" <u>ዝርዝር አላማ</u> "

ለማዳመጥና ለመናገር ክሂሎች አንዱ ዓይነት ዝርዝር አላማዎች ቀርበዋል ። የትኛው ዝርዝር አላማ ለየትኛው ክሂል እንደሆነ ተለይቶ አልተገለጸም ። በአንደኛ ሴሚስተር አንዱ ዝርዝር አላማ ብቻ:- ተጠየቃዊ አስተሳሰብን ያዳብራሉ' ተብሎ ቀርቧል ፤ በየትኛው ክሂል አንጻር እንደሚከናወን ግልጽ አይደለም ። ከዚህም በላይ እንዲዳበር የተፈለገው ክሂል ሳይሆን <u>አስተሳሰብ</u> ነው ። በሁለተኛ ሴሚስተርም እንዲሁ አንዱ ዝርዝር አላማ ብቻ ቀርቧል ። 'የተወሰነን ሀሳብ በራስ አባባል የማቅረብ ዘዴን ያዳብራሉ' ይላል ። በዚህ ዝርዝር አላማ እንዲዳበር የሚፈለገው ችሎታ በራስ አባባል የማቅረብ ዘዴ ነው ።ይህም አገላለጹ እንደሚያስረዳው ትኩረቱ የመናገር/በራስ አባባል የሚቀርበው በጽሑፍ ከሆነም የመጻፍ/ክሂል ላይ ነው ። በእርግጥ በራስ አባባል ለማቅረብ አስቀድሞ ማዳመጥን ወይም ማንበብን ይጠይቃል ። ሆኖም ግን ከላይ የቀረበው ዝርዝር አላማ አቀራረብ እንደሚያመለክተው የማዳመጥን ወይም የማንበብን ክሂል ለማዳበር ታቅዷል፣ ወይም የማዳመጥ ክሂል ላይ

ያተኰራል ብሎ ለመደምደም ያዳግታል ::

በአላማ ደረጃ የማዳመጥ ክሂል ከመናገር ክሂል ጋር ተዳብሎ በመቀረቡ ዝርዝር አላማ ሲነደፍም ተለይቶ ትኩረት ሳያገኝ ቀርቷል::ወደ ይዘቱ ስንመጣ ከላይ እንደተገለጸው ይዘቱ በዝርዝር አላማው የቀረቡት ጉዳዮች ወደ ቋንቋ ትምህርትነት የሚተረጎሙበት ክፍል ነው :: በዝርዝር አላማዎቹ ላይ የታየው የማዳመጥ ክሂል ትኩረት ማጣት በይዘት ምርጫው ላይ ምን ያህል ተ ተንጸባርቆ እንደሆነ በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን ::

## 1: <u>የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር ሆን ብለው የተመረጡ ይዘቶች</u>

1.1 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተጠየቃዊ አስተሳሰብን ለማዳበር በተመረጡት ይዘቶች የሚከተሉትን ልምምዶች እንዲያከናውኑ ይጠበቃል :-

### <u>የውይይት ስርአት</u>

ተማሪዎቹ በተወሰነ ርእስ ላይ ከተለያዩ ቦታዎች ሀሳብ አሰባስበው በመምጣት በቡድን በቡድን ሆነው ይወያያሉ፤ አንዱ ቡድን ሲወያይ ሌላው ያዳምጣል ፤ ተራቸውን ጠብቀው ይናገራሉ ፤ በንግግር ብቻ ለማቀረብ የማያመቹ ሀሳቦችን በስዕላዊ መገለጫዎች አስደግፈው ያቀርባሉ፤ የውይይትን ፍሬ ነገር የማሳለፍና የመጣል ስርአትን ይለማመዳሉ ::

- በዚህ ልምምድ ሊዳበር የሚችል የማዳመጥ ንኡስ ክሂል=ለተናጋሪው ተገቢውን መልስ የማዘጋጀት ፤ ተጨባጭ እውነትንና የግል አስተያየትን መለየት ::

### <u>የክርክር ስርአት</u>

በዚህ ይዘት ተማሪዎቹ ስላደመጡት ክርክር በምክንያት የተደገፈ አስተያየት መስጠትን፤ አንዱን ርእስ በመደገፍ ወይም በመቃወም መከራከርን፤ በተሰጣቸው ርእስ በአንዱ ወቅት ተዘጋጅተውበት በሌላ ጊዜ ደግሞ ሳይዘጋጁበት መከራከርን፤ ተቃዋሚው ክፍል ከሚያቀርበው ሀሳብ መከራከሪያ ነጥብ መገኘትን ይለማመዳሉ ::

- በዚህ ልምምድ ሊዳበሩ የሚችሉ የማዳመጥ ንኡሳን ክሂሎች =የተደመጠውን ነገር ቀደም ብሎ ስለጉዳዩ ካለ እውቀት ጋር ማገናዘብ ፤ ተጨባጭ እውነትንና የግል አስተያየትን መለየት፤ ለተናጋሪው ተገቢውን መልስ ማዘጋጀት ::

<u>የጭውውት ስርአት</u>

በዚህ ይዘት ተማሪዎች በሬዲዮና በቴሌቭዥን ከሚሰሟቸው ጭውውቶች መሀከል ጠቃሚ ናቸው ብለው የሚያምኑባቸውን መርጠው ለክፍል ጓደኞቻቸው ፕሮግራም አቀራረቢያቸን መስለው ያቀርባሉ ፤ ቁም ነገር አዘል ጭውውት ያደርጋሉ ::

- በዚህ ለምምዱ ሊዳበር የሚችል የማዳመጥ ንኡስ ክሂል=ለተናጋሪው ተገቢውን መልስ ማዘጋጀት ::

1.2: የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የተወሰነን ሀሳብ በራስ አባባል የማቀረብ ዘዴን ለማዳበር በተመረጠው ይዘት የሚከተሉትን ተግ ባሮች ያከናውናሉ ::—

<u>የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት</u>

በዚህ ይዘት ተማሪዎች የአንዱን ድርጊት መንስኤ ካዳመጡ በኋላ ውጤቱ ሊሆኑ የሚችሉትን በመገመት ይናገራሉ ፤ ስለተፈጸመ ድርጊት አዳምጠው የድርጊቱን መንስኤ ይገምታሉ ፤ የመንስኤና የውጤትን ግንኙነትና ልዩነት ያውቃሉ ::

- በዚህ ለምምዱ ሊዳበር የሚችል የማዳመጥ ንኡስ ክሂል = የንግ ግሩን ተከታታይ ክፍሎች አስቀድሞ የመገመት ችሎታ ::

2. <u>ሌሎች ክሂሎችን ለማዳበር የተመረጡ ይዘቶች</u>

እነዚህ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡት ዋና አላማ የመጻፍን ክሂል ለማዳበር ሆኖ ሣለ አገረ መንገዳቸውን የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የሚከሩ ይዘቶች ናቸው ::

<u>በጭብጥና በስሜታዊ አስተያየት መካከል ያለው ልዩነት</u>

በዚህ ይዘት ተማሪዎች በሚያዳምጡት ንግግር ውስጥ ተጨባጭ ሀቅ የሆኑ ነገሮችንና የተናጋሪውን የግል አስተያየቶች ለይተው ያዳምጣሉ :: ሀቅ ነው ወይም የግል አስተያየት ነው ያሉበትን ምክንያት ይናገራሉ ::

- በዚህ ለምምዱ የሚዳብሩ ንኡሳን የማዳመጥ ክሂሎች=ስለሚደመጠው ነገር አጠቃሳይ ግንዛቤ መውሰድ፣ ተናጋሪው የሚሰጠውን መረጃ ስሚቱን መገንዘብ፣ የተደመጠውን ነገር ቀደም ብሎ ስለ ጉዳዩ ካለ እውቀት ጋር ማገናዘብ፣ ተጨባጭ እውነትንና የግል አስተያየትን መለየት ::

## ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝ

በዚህ ይዘት ለተማሪዎች የሚያዳምጡት ምንባብ ይቀርብላቸዋል:: ካደመጡት ያገኙትን ፍሬ ሀሳብ በማስታወሻ ይዘው ለክፍል ጓደኞቻቸው ያሰማሉ ፤ በሬዲዮና በቴሌቭዥን ያዳመጡትን ዜና ዋና ዋና ሀሳብ ማስታወሻ በመያዝ ለክፍል ጓደኞቻቸው ያሰማሉ ::

- በዚህ ለምምዱ ሊዳብሩ የሚችሉ የማዳመጥ ንኡሳን ክሂሎች = ከሚያዳምጡት ውስጥ ፍሬ ሀሳቡን ለይቶ ማስታወሻ መያዝ፣ ከሚደመጠው ረዥም ንግግር አቢይ ሀሳብ ወይም ጭብጥ ማውጣት

## አንዱን ርእስ ጉዳይ በራስ አባባል ማቅረብ

በዚህ ይዘት ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን ውይይት በማዳመጥ በውይይቱ ውስጥ የቀረበውን ሀሳብ በራሳቸው አባባል ያቀርባሉ ::

- በዚህ ለምምዱ ሊዳብሩ የሚችሉ የማዳመጥ ንኡሳን ክሂሎች= ያዳመጡትን በራስ አባባል የማቅረብ ዘዴ፣ ስለሚደመጠው ነገር አጠቃሳይ ግንዛቤ መውሰድ፣ የሚጠቀሙ መረጃዎችንና ድግግሞሽን መለየት ፣ ከረዥም ንግግር አቢይ ሀሳብ ወይም ጭብጥ ማውጣት ::

የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ያዳብራሉ ተብለው የተመረጡትን አራት ይዘቶችም ሆነ ሌሎች ክሂሎችን ለማዳበር ተመርጠው እግረ መንገዳቸውን የማዳመጥን ክሂል የዳሰሱትን ይዘቶች ስንመረምር ለእያንዳንዱ ንኡስ ክሂል ትኩረት ሰጥተው በግልጽና በዝርዝር ባያቀርቡም ከሞላ ጎደል ከላይ የተዘረዘሩትን የማዳመጥ ንኡሳን ክሂሎች ሊያዳብሩ እንደተፈለገ ይዘቱ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ በሚጠቁመው የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሥራ ከንውን በሚለው የመርሀ ትምህርቱ ክፍል ከቀረቡ ዝርዝር ነገሮች ለመረዳት ተችሏል ::

ከላይ በቀረቡት ይዘቶች የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር ታቅዷል? የሚለውን ጥያቄ ስናነሳ ይዘቶቹ በተተረጐሙበት የመማር ማስተማር ሥራ ከገውን ላይ ሁለት አይነት ነገሮች ይታያሉ :: እነርሱም :-

1. ይዘቱን በተመለከተ አስፈላጊውን እውቀት ማስጨበጥና
2. ክሂሉን በልምምዱ ማዳበር ናቸው ::

አስፈላጊውን እውቀት ማስጨበጥን በተመለከተ ስለውይይት፣ክርክርና ጭውውት ስርአቶች፣ ስለመንስኤና ውጤት ግንኙነትና ልዩነት፣"ማሳወቅ" "ማስተማር"፣ "ማስገንዘብ"በሚሉ አንቀጾች የተገለጹ በይዘቱ ስለቀረበው ጉዳይ እውቀት የሚያስገኙ ዝርዝር ነገሮች ቀርበዋል:: እነዚህ እውቀቶች ክሂሉን ለማዳበር በሚከናወን ተግባራዊ ልምምድ ላይ ጠቀሜታ አላቸው :: ለክፍሉ በተዘጋጀው የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የውይይት፣ የክርክር፣ ወዘተ ... መምሪያዎች ተብለው የቀረቡትን ስናይ ግን የትምህርቱ ትኩረት የመናገር ክሂል ላይ እንጂ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር አለመሆኑን እንገነዘባለን :: በውይይቶች ፣ በክርክሮች፣ ወዘተ...እንዴት ማዳመጥ እንዳለብትና ለዚህም የሚረዱትን ንኡሳን የማዳመጥ ክሂሎች እንዲለማመዱ አይጠቁምም::/ አባሪ 6ን ይመለከቷል/::

ከላይ በይዘቶቹ አማካይነት ሊዳበሩ ይችላሉ የተባሉት የማዳመጥ ንኡሳን ክሂሎች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በግልጽና በዝርዝር አለመቅረባቸውና በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ስራ ከገውን ስር በቃላት ታጅበውና ተደባብሰው የትኛውን ክሂል ማዳበር እንደተፈለገ ለመለየት አሻሚ በሆነ መንገድ ተጽፈው መገኘታቸውን አይተናል :: ተማሪዎቹ ይወያያሉ፣ ይከራከራሉ፣ ጭውውት ያደርጋሉ ፣ ወዘተ ... ሲሉ በውይይቱ ፣ በክርክሩና በጭውውቱ ጊዜ የሚተኮርባቸው የማዳመጥ ዋና ንኡሳን ክሂሎች የትኞቹ እንደሆኑ በይዘቱ ላይ በግልጽ አልተነገረም :: መርሀ ትምህርቱን ተንተርሶ የትምህርት መረጃዎችን እንደመማሪያ መጽሀፍት ያሉትን የሚያዘጋጁ ባለሙያ ወይም ትምህ ርቱን ለተማሪዎቹ የሚያስተላልፍ እያንዳንዱ መምህር በግልጽ ያልተጠቀሰውን የትምህርት ይዘት በተለያየ መንገድ ሊተረጉመው ይችላል :: ከዚህም የተነሳ እያንዳንዱ መምህር የተለያዩ የትኩረት አቅጣጫን ይዞ ያስተምራል ማለት ነው:: የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች በአጠቃላይ አላማ፣ በዝርዝር አላማና በይዘት አመራረጥ ረገድ በአንድ ላይ መቅረባቸው ደግሞ ለዚህ አይነት የትኩረት አቅጣጫ መለያየት ተጨማሪ አስተዋጽኦ አለው ::

.../42

በዝግጅቱ ጸሀፍት ቅኝት እንዳየነው የማዳመጥን ክሂሎ በሚያዳብሩ ይዘቶች ውስጥ የተለያዩ የማዳመጥ አይነቶች ሊቀርቡ ይችላሉ :: ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ ለማህበራዊ ምልልስ ማዳመጥና ለመረጃ መሻት ማዳመጥ ናቸው:: ከላይ በዝርዝር ያየናቸው ይዘቶች ከጭውውት ስርአት በስተቀር ሁሉም በመረጃ መሻት የማዳመጥ አይነት ላይ ያተኩሩ ናቸው :: ይህ ሁኔታ አንደርሰንና ሊንች/1988/ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማዳመጥን ትምህርት ይዘት በተመለከተ ተማሪው የማህበራዊ ምልልስ ክሂሎችን ለማዳበር በህብረሰቡ ውስጥ ሰፊ እድል ስላለው ፣ በትምህርት ቤት በይበልጥ ሊተኮርባቸው የሚገባው የመረጃ መሻት ክሂሎች ላይ ነው :: በማለት ከሰነዘሩት ሀሳብ ጋር ይስማማል::

የቋንቋ ትምህርት ይዘትን ስናነሳ ሌላው ሊታይ የሚገባው ጉዳይ የይዘት ቅንብር ነው :: የይዘት ቅንብር ፣ የይዘት ተከታታይነትን፣ ተለጣጣቂነትንና አንድነትን ይመለከታል ::በዘጠነኛ ክፍል መርሀ ትምህርት ውስጥ ያለውን የማዳመጥ ክሂሎ የይዘት ቅንብር ስንመለከት ተከታታይነትንና ተለጣጣቂነትን በተመለከተ በሁለቱም ሴሚስተሮች የቀረቡት ይዘቶች አንዱ በሌላው ላይ ተመስርቶ በየጊዜው እያደገ በሚሄድ ቅደም ተከተል አልቀረቡም:: በማዳመጥ የሚፈጸሙ ተግባሮች ማዳመጥን ቀላል ወይም ከባድ እንደሚያደርጉት አንደርሰንና ሊንች ሲያስረዱ :- ወዲያውኑ ምላሽ የሚሹ ተግባሮች፣ካዳመጡ በኋላ ተፈላጊውን መረጃ መርጦ ከሚፈጸሙ ተግባሮች ይልቅ ቀላል ናቸው ፤ እነዚህ ደግሞ በተራቸው በስሜታዊና በተጨባጭ አስተያየቶች መሀከል ያለውን ልዩነት መገንዘብን ከሚጠይቅ የማዳመጥ ተግባር ይልቅ ቀላል ናቸው ይላሉ :: /አንደርሰንና ሊንች 1988/ በዚህ መሠረት በአንደኛው ሴሚስተር በቀረቡት ይዘቶች የሚፈጸሙትን የማዳመጥ ተግባሮች ስንመለከት፣ በሦስተኛው ይዘት /የጭውውት ስርአት /የቀረበው ተግባር :- ለተናጋሪው ተገቢውን መልስ ማዘጋጀት—ወዲያው ምላሽ የሚሻ ተግባር ነው ፣ በአንደኛውና በሁለተኛው ይዘቶች /የውይይት ስርአት፣ የክርክር ስርአት በቀደም ተከተል/ ከሚፈጸሙ ተግባሮች መሀከል ተጨባጭ እውነትንና የግል አስተያየትን መለየት፣ የሚደመጠውን ነገር ቀደም ብሎ ስለጉዳዩ ካለ እውቀት ጋር ማገናዘብ የሚሉ ይገኙበታል ::

በሦስተኛው ይዘት ከሚፈጸመው የማዳመጥ ተግባር ይልቅ በአንደኛውና በሁለተኛው ይዘቶች የሚፈጸሙት የማዳመጥ ተግባራት የሚደመጠውን ነገር መሮምሮ ከሌሎች ካልተነገሩ ሁኔታዎች ጋር አገናዝቦ መረዳትን ስለሚጠይቁ ከባዱ ናቸው :: በሁለተኛ ሴሚስተር በቀረበው ይዘት የሚፈጸመው የማዳመጥ ተግባር :- የንግግሩን ተከታታይ ክፍሎች አስቀድሞ መገመት ተጨባጭ በሆኑ ነገሮች ላይ የተመሠረተ ልምምዱ ቢሆን ፣ በአንደኛው ሴሚስተር ከምናገኘው —ተጨባጭ

እውነትንና የግል አስተያየትን መለየት ከሚለው የተናጋሪውን አስተሳሰብ መገንዘብን ከሚሻ የማዳመጥ ተግባር ይልቅ ቀላል ነው :: በዚህ መሠረት በአንዱ ሲሚስተር ውስጥም ሆነ በተከታታይ ሲሚስተሮች የቀረቡት የማዳመጥ ይዘቶች ደረጃ በደረጃ ከቀላል ወደ ከባዱ እያደጉ የሚሄዱ አይደሉም :: ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት በሌለበት ሁኔታም ስለይዘት አንድነት መናገር አይቻልም፤ ምክንያቱም አንድነት ከተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ይገኛልና ነው ::

ካጠቃላይ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የተመረጡት ይዘቶች የሚከተሉት ጠንካራና ደካማ ጎኖች ታይተውባቸዋል::

ደካማ ጎኖች :-

1. ሌሎቹን ክሂሎች ለማዳበር ከተመረጡት ይዘቶች ጋር ሲነጻጸሩ በቁጥር በጣም አነስተኛ ናቸው ለየአሳማው የተመረጡት ይዘቶች ብዛት አማካይ 10.6ሲሆን የማዳመጥ ይዘቶቹ ብዛት 4 ወይም ከጠቅላላው በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ከቀረቡት ይዘቶች 7.5 % ብቻ ነው ::

2. በየሲሚስተሩ ተመጣጣኝ አቀርቦት አይታይም፤ ለዚህም በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የተሰጠ ምክንያት የለም:: በአንደኛው ሲሚስተር ሦስት ይዘቶች ተመርጠው ሲቀርቡ ከሁለተኛው ሲሚስተር አንድ ይዘት ብቻ ተመርጦ ቀርቧል ::

3. በይዘቶቹ የተኛውን ክሂል ለማዳበር እንደተፈለገ በግልጽና በዝርዝር አልተጠቀመም ፤ ለምሳሌ 'የውይይት ስርአት' ሲል በዚህ ይዘት አንጻር ሊቀርቡባቸው የሚገቡ አጠቃላይና ንኡሳን የማዳመጥ ክሂሎች የትኞቹ እንደሆኑ አልተጠቀመም ::

4. ግልጽነት ይጎድላቸዋል፤ አሻሚ ትርጉም ይሰጣሉ:: ለዚህም ምክንያቶቹ

   - በአጠቃላይ አላማና በዝርዝር አላማ ስር የማዳመጥ ክሂል ከመናገር ክሂል ጋር ተዳብሎ መቅረቡ ፤

   - ይዘቶቹ ሆኑ በይዘቶቹ አንጻር የቀረቡት ለምምዶች የተገለጹበት ቋንቋ ፤ ናቸው ::

. /124

5. የክብደት ደረጃቸውን ጠብቀው እያደጉ የሚሄዱ ልምምዶች አልቀረበባቸውም ፤

- በአንደኛውና በሁለተኛው ይዘቶች ከቀረቡት ልምምዶች ይልቅ በሶስተኛው ይዘት የቀረበው በጣም ቀላል ነው ፤ በአንደኛው ሴሚስተር የቀረቡ ልምምዶች በሁለተኛው ሴሚስተር ከቀረበው የከበዱ ናቸው ::

<u>ጠንካራ ጎን</u> :-

1. ገለጻነት በጎደለው ሁኔታ በቃላት ተጨበሰበሰው ቢገኙም አንዳንዱ የማዳመጥ ዋናና ንኡሳን ክሂሎችን ለማዳበር ሞክረዋል:- ምሳሌ :- ተጨባጭ እውነትንና የግል አስተያየትን መለየት ፣ ለተናጋሪው ተገቢውን መልስ ማዘጋጀት ፣ ወዘተ ...

2. በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለማዳመጥ ትምህርት ይበልጥ ሊተኮርባቸው በሚገቡ የይዘት አይነቶች ላይ በይበልጥ አተኩረዋል:-ለምሳሌ፡- ለመረጃ መሻት ማዳመጥ::

4.2 <u>የመጠይቆች ምላሽ</u>

የዘመነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ሲዘጋጅ የተማሪዎችን ችሎታና ፍላጎት በማጥናት በዚያ ላይ ተመስርቶ ስለመዘጋጀቱ የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት አዘጋጆች ምላሽ ከቃለ ጉዳይ በተማሪው ፍላጎትና ችሎታ ላይ መመስረቱን ቢጠቁም በመርሀ ትምህርቱ መግቢያ ላይ የመርሀ ትምህርቱ አዘጋጃጀት በጥናት ላይ ያለ ተመሠረተ መሆኑ ተገልጿል ::
/ ትምህርት ሚኒስቴር የአማርኛ ቋንቋ ሲለበስ፣ ዘመነኛ ክፍል፣ 1984/ ::

መርሀ ትምህርቱ የዚህ ክፍል ተማሪዎች አንድን የቋንቋ ትምህርት ይዘት ከዚህ እስከዚህ ድረስ ሊማሩ ይችላሉ በሚል ግምት ላይ ተመስርቶ ነው የተዘጋጀው :: ለዚህም በየክፍሉ የሚቀርቡ ይዘቶችን የሚያመለክት የትምህርት ይዘቶች ሠሌዳ /ፍሰው ቻርት/ በማዘጋጀት ፣ ለየክፍሉ የሚሆኑ መርሀ ትምህርቶች ሲዘጋጁ ይዘቶቹ ከዚያ ላይ ይመረጧሉ :: እንደመርሀ ትምህርት ባለሙያዎቹ አባባል የዘመነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን ለመምረጥ የተጠቀሙበት የትምህርት ይዘቶች ሠሌዳ በ1972 ዓ/ም የተዘጋጀ ነው :: በሰሌዳው ላይ እንደሚታየው በዘመነኛ ክፍል የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን እንዲያዳብሩ የተመረጡት ይዘቶች በአንደኛው ሲሚስቴር የቀረቡት /የውይይት ስርአት፣ የክርክር ስርአት፣ የጭውውት ስርአት/ ይዘቶች ለተማሪው መስጠት የሚጀምሩት ከሁለተኛ ክፍል ጀምሮ ነው ፣ በሁለተኛው ሲሚስቴር የቀረበው /የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት/ይዘት ለተማሪው መስጠት የሚጀምረው ከሰበተኛው ክፍል ጀምሮ ነው :: ዘመነኛ ክፍል ሲደርስ ተማሪው ቀደም ባሉት ክፍሎች የይዘቶቹን መምሪያ፣ ፍች ወይም ደንብ እያወቀና እየተለማመደባቸው እንደመጡና እዚህ ክፍል ሲደርስ የይዘቶቹን መምሪያ፣ ፍች ወይም ደንብ የማሳወቅ ሁኔታ አብቅቶ የይዘት ለምምዱ ብቻ እንደሚቀጥል ይገልጻል :: በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የሚታየው
በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የሚታየው ሁኔታ ግን ከዚህ የተለየ ነው :: "የውይይት ስርአት" የክርክር ስርአት" ፣ "የጭውውት ስርአት" የሚሉት አገላለጾች ይዘቶቹ ለዘመነኛ ክፍል

ተማሪዎች ገና በመምሪያና በፍች ደረጃ እንደሚቀርቡ ያሳያሉ ። በዚህም በ ተጨማሪ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥም መምሪያዎች ቀርበዋል ። መርሀ ትምህርቱ ሲዘጋጅ ለይዘት ምርጫ መሠረት አድርጉታል የተገለውን የትምህርት ይዘቶች ሠሌዳ አሠራር አንጻ ለለ ተከ ተለም ።

በዚህ አይነት መንገድ ተመርጠው የቀረቡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ከ ተማሪው ችሎታና ፍላጎት ጋር ምን ያህል ሊጣጣሙ እንደሚችሉ ለማየት በ ተማሪው ፣ በ ቋንቋ መምህሩና በመርሀ ትምህርት ባለሙያው የ ሚሞሉ መጠይቆች በማዘጋጀት መረጃ ለመሰብሰብ ተሞክሯል ። በመጠይቆቹ አማካይነት የተገኙ መረጃዎች ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል ።

### 4.2.1. ከ ተማሪው መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

ሠንጠረዥ 4:- የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ

| አፍ መፍቻ ቋንቋ | ብዛት | % |
|---|---|---|
| አማርኛ | 278 | 92.6 |
| ኦሮምኛ | 12 | 4.0 |
| ትግርኛ | 5 | 1.6 |
| ሌሎች | 5 | 1.6 |

ሠንጠረዥ 5:- የተማሪዎች ዕድሜ

| ዕድሜ | ብዛት | % |
|---|---|---|
| 13 አመትና በታች | 31 | 10.3 |
| ከ14-16 ዓመት | 222 | 74.0 |
| ከ17-19 " | 47 | 15.6 |
| 20 ዓመትና በታች | – | – |

ሠንጠረዥ 6፡ የተማሪዎቹ ጾታ

| ጾታ | ብዛት | % |
|---|---|---|
| ወንድ | 125 | 41.6 |
| ሴት | 175 | 58.3 |

በዘጠነኛ ክፍል የምናገኛቸው ተማሪዎች አብዛኛው /92.6 %/ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ ሲሆን ፤ 7.2 % አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚችሉ ናቸው ፡፡ አማርኛ በሁለተኛ ቋንቋቸው ከሆኑት መካከል 4 % በኦሮምኛ ፤ 1.6 % በትግርኛ ፤ 1.6 % በአረብኛ፣ በጉራጌኛ፣ በሃዲይኛና በስልጥኛ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ናቸው ፡፡

ተማሪዎች ለትምህርት የቀረበላቸውን ቋንቋ ለአፍ መፍቻነት ወይም በሁለተኛ ቋንቋነት የሚያውቁት መሆኑን ለይቶ ማወቅ የትምህርት ይዘትን በመምረጥ ረገድ ቋንቋው ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ በያቸ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶችና የሚቸገሩባቸውን የቋንቋ ክፍሎች በይዘቱ ውስጥ ለማካተትና በቂ ልምምድ ለማቅረብ ያስችላል ፡፡

በዚህ ክፍል ከሚገኙ ተማሪዎች 41.6 %ወንዶች ሲሆኑ 58. 3 %ሴቶች ናቸው ፡፡ አብዛኛው ተማሪዎች / 74 % / ከ14–16 ዓመት ሲሆኑ፣ 15.6 % ከ17–19 ዓመት ፤ 10.3 % 13 ዓመትና ከዚያ በታች ናቸው ፡፡ የተማሪዎችን ዓራ ማወቅ ተማሪዎች በተወሰነ የዕድሜ ክልልና የጾታ ሁኔታ ሊኖራቸው የሚችለውን ዝንባሌ በመገመት የትምህርቱን ይዘት ከዝንባሌያቸው ጋር የተስማማ አድርጎ ለመምረጥ ይረዳል ፡፡

...// 48

ማስታወሻ ፡- ከዚህ በኋላ በሚቀርቡ ሠንጠረዦች ውስጥ የመለሱትን የምርጫ ደረጃ የሚያሳዩ ቁጥሮች ትርጉም እንደየጥያቄው አቀራረብ የሚከተሉትን ይመስላል ::

5 = በጣም ከፍተኛ / በጣም በከፍተኛ ደረጃ
4 = ከፍተኛ / በከፍተኛ ደረጃ
3 = መካከለኛ /በመካከለኛ ደረጃ
2 = ዝቅተኛ / በዝቅተኛ ደረጃ
1 = በጣም ዝቅተኛ / በጣም በዝቅተኛ ደረጃ
0 = ምንም /ምንም ጥቅም አይሰጥም
x = መልስ ያልሰጡ

ወይም

4 = ሁሉ ጊዜ
3 = ብዙ ጊዜ
2 = በመጠኑ
1 = አንዳንድ ጊዜ
0 = በፍጹም
x = መልስ ያልሰጡ

ጥያቄ 1 ፡ አማርኛን የሚማሩበት አላማ ፡-
ሠንጠረዥ 7 'የማኅመጥን ከሌላ ማኅበር ለሚለው አላማ
የተሰጠ ምላሽ ነው ፡-

| ምርጫ | ብዛት | % |
|---|---|---|
| 5 | 173 | 57.6 |
| 4 | 63 | 21.0 |
| 3 | 47 | 15.6 |
| 2 | 5 | 1.6 |
| 1 | 5 | 1.6 |
| 0 | 3 | 1.0 |
| x | 4 | 1.3 |

አማርኛን የሚማሩበትን አላማ እንዲያመለክቱ ከተሰጣቸው ዝርዝር ውስጥ "አዳምጦ የመረዳት ችሎታን ማዳበር" የሚለው አላማ 57.6 % በጣም በከፍተኛ ሁኔታ አላማችን ይገልጻል ሲሉ ፣ 21 % በከፍተኛ ሁኔታ ፣ 15.6 % በመካከለኛ ሁኔታ አላማችን ይገልጻል ብለዋል ። "የማዳመጥ ችሎታችን ማዳበር ዷን ዷውን የምማርበት አላማዬ አይደለም" ያሉት 1 % ብቻ ናቸው ።

2. የሚከተሉትን የማዳመጥ ተግባራት ምን ያህል ታዘወትራለህ /ሽ

ሠንጠረዥ 8:- ተማሪዎች የሚያዘወትሯቸው የማዳመጥ ተግባራት:-

| ምርጫ | የጥያቄው ቁጥር | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2.1 | | 2.2 | | 2.3 | | 2.4 | | 2.5 | | 2.6 | | 2.7 | | 2.8 | |
| | በዛት | % | በዛት | % | በዛት | % | በዛት | % | በዛት | % | በዛት | % | በዛት | % | በዛት | % |
| 4 | 93 | 31.0 | 192 | 64.0 | 128 | 42.6 | 54 | 18.0 | 68 | 22.6 | 96 | 32.0 | 67 | 29.0 | 121 | 40.3 |
| 3 | 70 | 23.3 | 68 | 22.6 | 78 | 26.0 | 47 | 15.6 | 49 | 16.3 | 60 | 20.0 | 69 | 23.0 | 77 | 25.6 |
| 2 | 91 | 30.3 | 27 | 9.0 | 61 | 20.3 | 65 | 21.6 | 65 | 21.6 | 59 | 19.6 | 47 | 15.6 | 61 | 20.3 |
| 1 | 36 | 12.0 | 8 | 2.6 | 18 | 6.0 | 82 | 27.3 | 81 | 27.0 | 59 | 19.6 | 68 | 22.6 | 30 | 10.0 |
| 0 | 7 | 2.3 | 3 | 1.0 | 9 | 3.0 | 38 | 12.6 | 29 | 9.6 | 10 | 3.3 | 20 | 6.6 | 6 | 2.0 |
| x | 3 | 1.0 | 2 | 0.6 | 6 | 2.0 | 14 | 4.6 | 8 | 2.6 | 16 | 5.3 | 9 | 3.0 | 5 | 1.6 |

የተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም ማወቅ በትምህርት ቤት በሚቀርብላቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘት ውስጥ ከተማሪዎች ልምድ ጋር የሚጣጣም ከትምህርት ቤት ውጭ ጥቅም ላይ ሊያውሉት የሚችሉትን ይዘት ለመምረጥ ይረዳል ። በዚህ መሠረት የዚህ ክፍል ተማሪዎች አዘ ወትረው የሚፈጽሟቸውን የማዳመጥ ተግባራት ተጠይቀው የሚከተሉትን መልሶች ሰጥተዋል ።

2.1 — የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን 31 % ሁልጊዜ ፣ 23.3 % ብዙ ጊዜ ፣ 30.3 % በመጠኑ ፣ 12 % አንዳንድ ጊዜ እናዳምጣለን ሲሉ ፣ 2.3 % በፍጹም እናዳምጥም ብለዋል ።

2.2 — በክፍል ውስጥ መምህሩ የሚነግሯቸውን የአሰራር መመሪያ ፣ 64.0 % ሁልጊዜ ፣ 22.6 % ብዙ ጊዜ ፣ 9 % በመጠኑ ፣ 2.6 % አንዳንድ ጊዜ እናዳምጣለን ሲሉ ፣ 1 % በፍጹም አናዳምጥም ብለዋል ።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

2.3 – በአማርኛ ቋንቋ የሚሰጡ የሌሎች ትምህርቶችን ገለጻ 42.6 % ሁል ጊዜ ፣ 26 % ብዙ ጊዜ ፣ 20.3 % በመጠኑ ፣ አንዳንድ ጊዜ እናዳምጣለን ሲሉ፣ 3 % በፍጹም እናዳምጥም ብለዋል ::

2.4 – በስልክ የሚተላለፉ መልእክቶችን 18 % ሁል ጊዜ ፣ 15.6 % ብዙ ጊዜ ፣ 21.6 % በመጠኑ 27.3 % አንዳንድ ጊዜ እናዳምጣለን ሲሉ፣ 12.6 % በፍጹም እናዳምጥም ብለዋል ::

2.5 – ውይይቶችን ማዳመጥ ለሚለው 22.6 % ሁልጊዜ ፣ 16.3 % ብዙ ጊዜ፣ 21.6 % በመጠኑ፣ 27 % አንዳንድ ጊዜ እናዳምጣለን ሲሉ ፣ 9.6 % በፍጹም እናዳምጥም ብለዋል ::

2.6 – የሌሎችን ጭውውት ማዳመጥ ለሚለው 32 % ሁልጊዜ ፣ 20 % ብዙ ጊዜ፣ 19.6 % በመጠኑ፣ 19.6 % አንዳንድ ጊዜ ፣ እናዳምጣለን ሲሉ 3.3 % በፍጹም እናዳምጥም ብለዋል ::

2.7 – በድምጽ ማጉያ የሚነገሩ ማስታወቂያዎችን 29 % ሁልጊዜ ፣ 23 % ብዙ ጊዜ፣ 15.6 % በመጠኑ፣ 22.6 % አንዳንድ ጊዜ እናዳምጣለን ሲሉ ፣ 6.6 % በፍጹም እናዳምጥም ብለዋል ::

2.8 – በቃል የሚቀርቡ ጥያቄዎችን 40.3 % ሁልጊዜ ፣ 25.6 % ብዙ ጊዜ፣ 20.3 % በመጠኑ፣ 10 % አንዳንድ ጊዜ እናዳምጣለን ሲሉ ፣ 2 % በፍጹም እናዳምጥም ብለዋል ::

3. በክፍል ውስጥ የምታደምጠው ጉዳይ እንዴት ቢቀርብልህ ተመርጧለህ ?

ሠንጠረዥ 9 :- የማደመጥ ጉዳይ የአቀራረብ ዝንባሌ

| ምርጫ | ብዛት | % |
|---|---|---|
| መምህሩ ቢያነቡት /ቢናገሩት | 222 | 74.0 |
| ተማሪው ቢያነበው /ቢናገረው | 17 | 5.6 |
| በካሴት ተቀድቶ ቢቀርብ | 50 | 16.6 |
| መልስ ያሰበጡ | 11 | 3.6 |

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እንዲያዳምጡ የሚቀርብላቸውን ምንባብ ወይም ንግግር እንዴት ቢቀርብላቸው እንደሚመርጡ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ 74. % "መምህሩ ቢያቀርቡት"፣ 16.6 %" በካሴት ተቀድቶ ቢቀርብ"፣ 5.6 " ተማሪዎች ቢያቀርቡት" በማለት መልሰዋል ::

4. የሌሎችን ሰዎች ንግግር ስታዳምጥ /ጪ የሚከተሉት ችግሮች ላንተ/ ቺ ችግር የሚሆኑብትን ደረጃ አመልክት / ቺ :-

ሠንጠረዥ 10 :- የተማሪዎች የማዳመጥ ችግር

| ምርጫ | የ ጥ ያ ቄ ው ቁ ጥ ር | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 4.1 | | 4.2 | | 4.3 | | 4.4 | | 4.5 | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 75 | 25.0 | 55 | 18.3 | 63 | 21.0 | 39 | 13.0 | 46 | 15.3 |
| 4 | 38 | 12.6 | 37 | 12.3 | 39 | 13.0 | 60 | 20.0 | 31 | 10.3 |
| 3 | 70 | 23.3 | 69 | 23.0 | 59 | 19.6 | 55 | 18.3 | 65 | 21.6 |
| 2 | 40 | 13.3 | 73 | 24.3 | 62 | 20.6 | 56 | 18.6 | 58 | 19.3 |
| 1 | 69 | 23.0 | 62 | 20.6 | 63 | 21.0 | 82 | 27.3 | 95 | 31.6 |
| × | 8 | 2.6 | 4 | 1.3 | 14 | 4.6 | 8 | 2.6 | 5 | 1.6 |

ተማሪዎች የማዳመጥ ችግር ካለባቸው ለችግሩ ምክንያት የሆኑትን እንዲጠቁሙ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ መሠረት :-

4.1 ÷ የንግግሩን ድምጸት ለይቶ ለማወቅ ፣ 25 % በጣም ከፍተኛ 12.6 % ከፍተኛ፣ 23.3 % መካከለኛ ፣ 13.3 % ዝቅተኛ ፣ 23 % በጣም ዝቅተኛ ችግር ነው በማለት መልሰዋል ፣

4.2 — በቋንቋ ውስጥ የሚላሉና የሚጠብቁ ድምጾችን ለይቶ ለማወቅ 18.3 % በጣም ከፍተኛ ፣ 12.3 % ከፍተኛ ፣ 23 % መካከለኛ 24.3 ዝቅተኛ ፣ 20.6 % በጣም ዝቅተኛ ችግር ነው በማለት መልሰዋል ::

4.3 — የቋንቋውን ባለቤቶች ባህል ለማወቅ 21 % በጣም ከፍተኛ ፣ 13 % ከፍተኛ ፣ 19.6 % መካከለኛ ፣ 20.6 % ዝቅተኛ፣ 21 % በጣም ዝቅተኛ ችግር ነው ብለዋል ::

4.4 – የተናጋሪውን ስሜት አለመረዳት 13 % በጣም ከፍተኛ ፣ 20 % ከፍተኛ 18.3 %. መካከለኛ ፣ 18.6 % ዝቅተኛ፣ 27.3 % በጣም ዝቅተኛ ችግር ነው ብለዋል::

4.5 – ፍሬ ነገሩን ለይቶ ማዳመጥ አለመቻል– 15.3 % በጣም ከፍተኛ፣ 10.3 % ከፍተኛ ፣ 21.6 %. መካከለኛ 19.3 % ዝቅተኛ፣ 31.6 % በጣም ዝቅተኛ ችግር ነው በማለት ወስነዋል::

..// 54

በጥያቄ ቁጥሮች ከ5.1–5.3 ፣ 5.7 ና 5.9 የቀረቡት ጥያቄዎች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የሌሉ ይዘቶች በመሆናቸው እዚህ ለትንተና አላስፈለገም ::

በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡት ይዘቶች ለተማሪዎቹ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆኑ ለማወቅ ተጠይቀው በሁሉም ይዘቶች አብዛኞቹ ተማሪዎች / ከ16 % – 50.3 % ድረስ / " በመካከለኛ ደረጃ ያስፈልገናል " ከሚለው እንስቶ " በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ያስፈልገናል " እስከሚለው ድረስ ባሉት መለቦች ውስጥ ይገኛሉ ፤ ከ2.6 – 11 % የሚደርሱ ተማሪዎች ይዘቶች " ዝቅተኛ " ና " በጣም ዝቅተኛ " በሆነ ደረጃ ያስፈልጉናል በማለት መልሰዋል ::

6. ከምታዳምጠው/ጪው ውስጥ ምን ያህሉን በእርግጠኝነት ታዳምጣለህ /ጪለሽ ?

ሠንጠረዥ 12 :– በማዳመጥ ችሎታ የመተማመን መጠን

| ምርጫ | ብዛት | % |
|---|---|---|
| ከ20 % በታች | 21 | 7.0 |
| ከ21 – 40 % | 36 | 12.0 |
| ከ41 – 60 %. | 71 | 23.6 |
| ከ61 – 80 % | 97 | 32.3 |
| ከ80 % በላይ | 71 | 23.6 |
| መልስ ያልሰጡ | 4 | 1.3 |

ተማሪዎቹ በየምክንያቱ ከሚያዳምጡት ውስጥ ምን ያህሉን በእርግጠኝነት እንደሚያዳምጡ ተጠይቀው 23.6 % ከ80 % በላይ፣ 32.3 % ከ61 – 80 %፣ 23.6 % ከ41–60 % ፣ 12 % ከ21 – 40 %፣ 7 % ከ20 % በታች በሆነ እርግጠኝነት እናዳ ምጣለን ብለዋል ። በዚህ መሠረት አብዛኞቹ ተማሪዎች /79.6 %/ ከ40 % በላይ በሆነ እርግጠኝነት ሲያዳምጡ ፣ ከ40 % በታች በሆነ እርግጠኝነት የሚያዳምጡ ተማሪዎች ቁጥር /19 % / ከግምት የሚገባና የማዳመጥ ልምዱ በብዛት ማቀረብ እንደሚያበረልግ የሚጠቁም ነው ።

7. በቋንቋ ክሂሎች በተጠቀም /ሚ/ ችሎታህ /ሽ/ ምን ያህል ነው ?

ሠንጠረዥ 13 :- በቋንቋ ክሂሎች የመጠቀም ችሎታ

| ምርጫ | የጥያቄው ቁጥር | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 7.1 | | 7.2 | | 7.3 | | 7.4 | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 100 | 36.6 | 56 | 18.6 | 105 | 35.0 | 95 | 31.6 |
| 4 | 89 | 29.6 | 78 | 26.0 | 109 | 36.0 | 68 | 22.6 |
| 3 | 79 | 26.3 | 107 | 35.6 | 59 | 19.6 | 72 | 24.0 |
| 2 | 9 | 3.0 | 37 | 12.3 | 20 | 6.6 | 40 | 13.3 |
| 1 | 11 | 3.6 | 19 | 6.3 | 4 | 1.3 | 22 | 7.3 |
| × | 2 | 0.6 | 3 | 1.0 | 3 | 1.0 | 3 | 1.0 |

በአማርኛ ቋንቋ በሚጠቀሙበት ጊዜ በአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ምን ያህል ችሎታ እንዳላቸው ተጠይቀው በሰጡት መልስ አዳምጦ የመረዳት ችሎታን /7.1/ በተመለከተ 36.6 % በጣም ከፍተኛ ፣ 29.6 % ከፍተኛ ፣ 26.3 % መካከለኛ ችሎታ አለን ሲሉ 3 % ና 3.6 % በቅደም ተከተል ችሎታችን ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ነው በማለት መልሰዋል ።

...// 57

8. በቋንቋው በምትጠቀም /ሚ በት ጊዜ የሚከተሉት ክሂሎች ለአንተ /ቺ/ ጠቀሜታቸው ምን ያህል ነው ?

ሠንጠረዥ 14:— የክሂሎች መዳበር የሚያስገኘው ጠቀሜታ መጠን :—

| ምርጫ | የ ጥ ያ ቄ ው ቁ ጥ ር | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 8.1 | | 8.2 | | 8.3 | | 8.4 | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 217 | 72.3 | 145 | 48.3 | 191 | 63.6 | 184 | 61.3 |
| 4 | 56 | 18.6 | 81 | 27.0 | 57 | 19.0 | 60 | 20.0 |
| 3 | 19 | 6.3 | 54 | 18.0 | 40 | 13.3 | 33 | 11.0 |
| 2 | 2 | 0.6 | 11 | 3.6 | 3 | 1.0 | 10 | 3.3 |
| 1 | 1 | 0.3 | 3 | 1.0 | 1 | 0.3 | 3 | 1.0 |
| 0 | 3 | 1.0 | 1 | 0.3 | 3 | 1.0 | 5 | 1.6 |
| x | 2 | 0.6 | 5 | 1.6 | 5 | 1.6 | 5 | 1.6 |

በቋንቋው በሚጠቀሙበት ጊዜ በአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ምን ያህል እንደሚጠቀሙ ተጠይቀው ፤ የማዳመጥን ክሂል /8.1/ በተመለከተ 72.3 % በጣም ከፍተኛ ፤ 18.6 % ከፍተኛ ፤ 6.3 % በመካከለኛ ደረጃ ክሂሉ ይጠቅመናል ብለዋል :: የክሂሉ ጠቀሜታ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ነው ያሉት 0.6 % ና 0.3 % በቅደም ተከተል ሲሆኑ ፤ 1 % ክሂሉ ምንም አይጠቅመንም ብለዋል :: አብዛኞቹ ተማሪዎች / 90.9 % / ክሂሉ በጣም እንደሚጠቅማቸው ነው ያመለከቱት ::በዚህ መሠረት የማዳመጥ ክሂል ለተማሪው በሚሰጠው ከፍተኛ ጠቀሜታ አንጻር በበቂ ሁኔታ ትኩረት ተሰጥቶት ሊዳበር ይገባል፡

...//58

5. በሚከተሉት ይዘቶች ክፍሎች/ን ማኅበር በሀብረተሰቡ ውስጥና በትምህርት ቤት ለማጥናት ምን ያህል ያበረታታሃል/ሻ/ል?

ሠንጠረዥ 11 :- የማጥናት ይዘቶች ጠቀሜታ

| | የ ጥ ያ ቄ ው ቁ ጥ ር | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5.4 | | 5.5 | | 5.6 | | 5.8 | | 5.10 | | 5.11 | | 5.12 | |
| ምርጫ | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 118 | 39.3 | 127 | 42.3 | 134 | 44.6 | 91 | 30.3 | 95 | 31.6 | 151 | 50.3 | 83 | 27.3 |
| 4 | 80 | 26.6 | 73 | 24.3 | 67 | 22.3 | 78 | 26.0 | 87 | 29.0 | 56 | 18.6 | 81 | 27.0 |
| 3 | 58 | 19.3 | 48 | 16.0 | 54 | 18.0 | 77 | 25.6 | 77 | 25.6 | 66 | 22.0 | 58 | 19.3 |
| 2 | 32 | 10.6 | 23 | 7.6 | 24 | 8.0 | 29 | 9.6 | 29 | 9.6 | 16 | 5.3 | 33 | 11.0 |
| 1 | 9 | 3.0 | 27 | 9.0 | 15 | 5.0 | 19 | 6.3 | 16 | 5.3 | 8 | 2.6 | 18 | 6.0 |
| x | 3 | 1.0 | 2 | 0.6 | 6 | 2.0 | 6 | 2.0 | 7 | 2.3 | 11 | 3.6 | 4 | 1.3 |

..// 55

10. በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ማዳመጥ የምትፈልገው/ጊው የምንባብ ወይም የንግግር ርእስ ስለምን የሚናገር ቢሆን ይሻላል?
ሠንጠረዥ 15 የተማሪዎች ዝንባሌ:- የሚዳመጥ ጉዳይ:-

| | የጥያቄ ቁጥር | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 10.1 | | 10.2 | | 10.3 | | 10.4 | | 10.5 | | 10.6 | | 10.7 | | 10.8 | | 10.9 | |
| ምርጫ | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 186 | 62.0 | 207 | 69.0 | 95 | 31.6 | 134 | 44.6 | 200 | 66.6 | 143 | 47.6 | 49 | 15.3 | 180 | 60_0 | 193 | 64.3 |
| 4 | 58 | 19.0 | 62 | 20.6 | 31 | 10.3 | 70 | 23.3 | 53 | 17.6 | 74 | 24.6 | 19 | 6.3 | 37 | 12.3 | 40 | 13.3 |
| 3 | 38 | 12.6 | 15 | 5.0 | 45 | 15.0 | 62 | 20.6 | 24 | 8.0 | 30 | 10.0 | 24 | 8.0 | 23 | 7.6 | 29 | 9.6 |
| 2 | 36 | 2.0 | 6 | 2.0 | 46 | 15.3 | 24 | 8.0 | 11 | 3.6 | 24 | 8.0 | 39 | 13.0 | 21 | 7.0 | 12 | 4.0 |
| 1 | 8 | 2.6 | 7 | 2.3 | 75 | 25.0 | 5 | 1.6 | 7 | 2.3 | 23 | 7.6 | 161 | 53.6 | 37 | 12.3 | 17 | 5.6 |
| × | 4 | 1.3 | 3 | 1.0 | 8 | 2.6 | 5 | 2.6 | 5 | 1.6 | 6 | 2.0 | 8 | 2.6 | 2 | 0.6 | 9 | 3.0 |

..// 59

የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር የሚቀርቡ ይዘቶችን ከዝንባሌያቸው ጋር የሚጣጣምና ስሜታቸው የሚስብ ፣ እንዲያዳምጡ የሚያነቃቃ እንዲሆን ተማሪዎቹ ለማዳመጥ በሚቀርብላቸው ምንባብ ወይም ንግግር ውስጥ እንዴት ያሉ ጉዳዮች ቢቀርብላቸው እንደሚወዱ ተጠይቀው ሲመልሱ፣ በጣም በከፍተኛ ደረጃ ከመረጧቸው ርእሶች ውስጥ 69 % ስለትምህርት፣ 66.6 % ስለጤና ፣ 64.3 % ስለቤተሰብ ፣ 62 % ስለሀገር፣ 60 % ስለ ሃይማኖት፣ 47.6 % ሣይንስ ነክ 44.6 % ስለ ጓደኝነት ፣ 31.6 % ስለፍቅር ፣ 16.3 % ስለ ፖለቲካ የሚናገሩ ርእሶችን እንመርጣለን ብለዋል ። በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ከመረጧቸው ርእሶች መሀከል 53.6 % ስለፖለቲካ ፣ 25 % ስለፍቅር፣ 12.3 % ስለ ሃይማኖት፣ 7.6 % ሳይንስ ነክ ፣ 5.6 % ስለቤተሰብ 2.3 % ስለትምህርት ፣ 2.3 % ስለጤና፣ 2.6 % ስለሀገር ፣ 1.6 % ስለጓደኝነት የሚናገሩ ርእሶችን በማለት መልሰዋል ።

የተማሪዎችን በጣም ከፍተኛ ምርጫና በጣም ዝቅተኛ ምርጫ ስንመለከት ተማሪዎች በጣም በከፍተኛ ደረጃ ማዳመጥ እንፈልጋለን ካሏቸው ርእሶች መሀከል ፖለቲካ ዝቅተኛውን ቁጥር / 16.3 % / ሲይዝ ፣ ትምህርት ከፍተኛውን ቁጥር /69. % / ይዟል ። በጣም ዝቅተኛ ምርጫቸን ናቸው ካሏቸው መካከል ደግሞ ፖለቲካ ከፍተኛውን ቁጥር 53.6 % / ሲይዝ ፣ ጓደኝነት የሚለው ርእስ ዝቅተኛውን ቁጥር / 1.6 %/ ይዟል ።

11. በሚከተሉት የማዳመጥ ችሎታን በሚመለከቱ ዓ.ነገሮች አማካይነት ችሎታህ/ሽ/ ምን ያህል እንደሆነ አመልክት :—

ሠንጠረዥ 16 የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ

| የ ጥ ያ ቄ ው ቁ ጥ ር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 11.1 | | 11.2 | | 11.3 | | 11.4 | | 11.5 | | 11.6 | | 11.7 | | 11.8 | | 11.9 | | 11.10 | |
| ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 80 | 26.6 | 83 | 27.6 | 71 | 23.6 | 56 | 18.6 | 59 | 19.6 | 59 | 19.6 | 88 | 29.3 | 116 | 38.6 | 113 | 37.6 | 96 | 32.0 |
| 75 | 25.0 | 123 | 41.0 | 109 | 36.3 | 88 | 29.3 | 65 | 21.6 | 80 | 26.6 | 89 | 29.66 | 77 | 25.66 | 101 | 33.6 | 107 | 35.6 |
| 88 | 29.3 | 268 | 22.6 | 95 | 31.6 | 93 | 31.0 | 93 | 31.0 | 81 | 27.0 | 91 | 30.3 | 65 | 21.6 | 57 | 19.0 | 63 | 21.0 |
| 24 | 8.0 | 14 | 4.6 | 12 | 4.0 | 38 | 12.6 | 48 | 16.0 | 44 | 14.6 | 15 | 5.0 | 18 | 6.0 | 11 | 3.6 | 11 | 3.6 |
| 16 | 5.3 | 5 | 1.6 | 4 | 1.3 | 12 | 4.0 | 25 | 8.3 | 25 | 8.3 | 9 | 3.0 | 6 | 2.0 | 8 | 2.6 | 1 | 0.3 |
| 17 | 5.6 | 7 | 2.3 | 9 | 3.0 | 13 | 4.3 | 10 | 3.3 | 11 | 3.6 | 8 | 2.6 | 18 | 6.0 | 10 | 3.3 | 22 | 7.3 |

ከሠንጠረዥ 16 የቀጠለ

| የ ጥ ያ ቄ ው ቁ ጥ ር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 11.11 | | 11.12 | | 11.13 | | 11.14 | | 11.15 | | 11.16 | | 11.17 | | 11.18 | | 11.19 | | 11.20 | |
| ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 115 | 38.3 | 74 | 24.6 | 95 | 31.6 | 88 | 29.3 | 108 | 36.0 | 89 | 29.6 | 45 | 15.0 | 80 | 26.6 | 60 | 20.0 | 120 | 40.0 |
| 87 | 29.0 | 107 | 35.6 | 111 | 37.0 | 89 | 29.6 | 99 | 33.0 | 86 | 28.6 | 55 | 18.3 | 86 | 28.6 | 80 | 26.6 | 80 | 26.6 |
| 49 | 16.3 | 67 | 22.3 | 56 | 18.6 | 91 | 30.3 | 60 | 20.0 | 75 | 25.0 | 107 | 35.6 | 77 | 25.6 | 98 | 32.6 | 64 | 21.3 |
| 21 | 7.0 | 28 | 9.3 | 23 | 7.6 | 15 | 5.0 | 18 | 6.0 | 25 | 8.3 | 49 | 16.3 | 32 | 10.6 | 39 | 13.0 | 18 | 6.0 |
| 7 | 2.3 | 7 | 2.3 | 7 | 2.3 | 9 | 3.0 | 7 | 2.3 | 20 | 6.6 | 37 | 12.3 | 13 | 4.3 | 19 | 6.3 | 14 | 4.6 |
| 21 | 7.0 | 17 | 5.6 | 8 | 2.6 | 8 | 2.6 | 8 | 2.6 | 5 | 1.6 | 7 | 2.3 | 12 | 4.0 | 4 | 1.3 | 4 | 1.3 |

..// 61

በጥያቄ 11 ላይ ለቀረቡት ሃያ የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ ጥያቄዎች የተሰጡት መልሶች በአንድነት ታይተዋል ። በዚህም መሠረት አያንዳንዱ ጥያቄ አምስት መቶ ምላሽ ስለሚኖረው በጠቅላላ በድምት ሺህ ምላሾች ይኖራሉ ።

የሚከተለው ሠንጠረዥ የምላሾቹን አማካይ ውጤት ያሳያል ።

ሠንጠረዥ 17 :- የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ ማጠቃለያ

| ምርጫ | የጥያቄው ቁጥር ከ 11.1 — 11.20 | |
|---|---|---|
| | አማካይ | % |
| 5 | 84.75 | 28.25 |
| 4 | 90.15 | 30.05 |
| 3 | 76.25 | 25.4 |
| 2 | 25.35 | 8.4 |
| 1 | 12.5 | 4.1 |
| × | 11.0 | 3.6 |

የተማሪዎችን አጠቃላይ የማዳመጥ ችሎታ ለመገመት በተለያዩ የማዳመጥ ንዑሳን ክሂሎች ያላቸውን ችሎታ እንዲያመለክቱ ለቀረቡላቸው ጥያቄ ተማሪዎች በሰጧቸው መልሶች 28.25 % በጣም ከፍተኛ ችሎታ፣ 30.05 % ከፍተኛ ችሎታ ፣ 25.4 % መካከለኛ ችሎታ ፣ 8.4 %. ዝቅተኛ ችሎታ ፣ 4.1 % በጣም ዝቅተኛ ችሎታ እንዳላቸው አመለከተዋል ። አብዛኞቹ ተማሪዎች / 83.7 % / መካከለኛ ችሎታና ከዛ በላይ አጠቃላይ የማዳመጥ የችሎታ ደረጃ እንዳላቸው ነው ያመለከቱት ።

## 4.2.2 ከመምህሩ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

መምህራን የተማሪዎቻቸውን የቋንቋ ችግር አስመልክቶ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ምክንያት የሚታይ ችግር እንዳለባቸው ተጠይቀው 85 % ቱ ተማሪዎቻቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ምክንያት የሚታይ የቋንቋ ችግር አለባቸው ሲሉ 15 % ቱ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ምክንያት የተለያየ የቋንቋ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች እንዳላጋጠሟቸው ገልጸዋል ::

የተማሪዎች መጠይቅ ምላሽ እንደሚያሣየው 92.6 % አፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ ነው :: ከመምህሩ መጠይቅ በተገኘው ምላሽ ላይ 85 % መምህራን አጋጥሞናል ያሉት የተማሪዎቻቸው የቋንቋ ችግር ምክንያት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሳይሆን ሌሎች ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ :: እሉ የጠቀሱት የቋንቋ ችግሮች የሥነ ልሣን ችሎታን የተመለከቱ ናቸው :: ለምሣሌ ቃላትን በትክክል ያለመናገር፣ ድምጾችን በአማርኛ ስርአት አለመጥራት፣ በንግግርና በጽሁፍ የሰዋሰው ሕግ አለመጠበቅ ወዘተ ... የሚሉ ይገኙባቸዋል ::

ሠንጠረዥ 18 :- የተማሪዎች የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጾች የመረዳት ሁኔታ በመምህራን ምዘና

| የችሎታ ደረጃ | ብዛት | % |
|---|---|---|
| በሚገባ ይረዳሉ | 5 | 25 |
| በመካከለኛ ደረጃ ይረዳሉ | 11 | 55 |
| በዝቅተኛ ደረጃ ይረዳሉ | 2 | 10 |
| በጭራሽ አይረዱም | – | – |
| አስተያየት የለኝም | – | – |
| መልስ ያልሰጡ | 2 | 10 |

የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጾች ማወቅ በኅብረተሰቡ ውስጥ ለማዳመጥ በጣም አስፈላጊ ነው ። ይህን በተመለከተ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ችሎታ አን ሲጠቁሙ ተጠይቀው 26 % በሚገባ ይረዳሉ ፣ 55 % በመካከለኛ ደረጃ ይረዳሉ ፣ 10 % በዝቅተኛ ደረጃ ይረዳሉ በማለት መልሰዋል ። አብዛኞቹ መምህራን /55 % / ተማሪዎቻቸው የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጾች በመረዳት ረገድ ችሎታቸው መካከለኛ እንደሆነ ነው የገለጹት ። በዚህ መሠረት የዚህ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂሎታቸውን ለማዳበር በሚቀርቡላቸው ይዘቶች ውስጥ የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጾች አዳምጠው ለመረዳት የሚያስችሏቸው ልምምዶችን የማቅረብ አስፈላጊነትን ሊጠቁም ይችላል ።

ሠንጠረዥ 19 :- <u>መምህራን ትኩረት ሰጥተው የሚያስተምሩት ክሂል ።</u>

| የትኩረት ደረጃ | ክ ሂ ሎ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ማዳመጥ | | መናገር | | ማንበብ | | መጻፍ | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1ኛ | 14 | 70 | 4 | 20 | 3 | 15 | 5 | 25 |
| 2ኛ | 1 | 5 | 11 | 55 | 4 | 20 | 2 | 10 |
| 3ኛ | 2 | 10 | 2 | 10 | 8 | 40 | 7 | 35 |
| 4ኛ | 3 | 15 | 3 | 15 | 5 | 25 | 6 | 30 |

መምህራን የዚህ ክፍል ተማሪዎችን የቋንቋ ክሂል በማዳበር ረገድ የበለጠ ትኩረት የሚሰጡት ለየትኛው ክሂል እንደሆነ ተጠይቀው በ1ኛ ደረጃ ትኩረት ከሚሰጧቸው ክሂሎች መሀከል 70 % ለማዳመጥ ፣ 20 % ለመናገር 15 % ለማንበብ ፣ 25 % ለመጻፍ ክሂል ትኩረት የሚሰጡ መሆኑን አመልክተዋል ። የማዳመጥን ክሂል በተመለከተ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መሀከል 70 % በአንደኛ ደረጃ ፣ 5 % በሁለተኛ ደረጃ ፣ 10 % በሶስተኛ ደረጃ ፣ 15 % በአራተኛ ደረጃ ትኩረት እንሰጣለን ብለዋል ።

ለማዳመጥ ክሂል የሰጡትን የትኩረት ደረጃ አስመልክቶ ምክንያታቸውን ተጠይቀው የተለያዩ ምክንያቶችን ሰጥተዋል ። ከነዚህም ውስጥ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር ከፍተኛ ትኩረት እንሰጣለን ያሉት / በ1ኛና በ2ኛ ደረጃ የመረጡት/ ከሰጧቸው ምክንያቶች :-

...//64

- ተማሪዎች የማዳመጥን ክሂል ካሳደጉ በሌሎች ክሂሎች የመጠቀም ችሎታቸው የተሟላ ስለማይሆን ፤
- የተነገረውን በማዳመጥ አዳምጠው በመናገር ክሂሉን ሊጠቀሙበት ስለሚችሉ፤ በሌሎቹ ክሂሎች ግን ለምበዛም አይጠቀሙም ፤
- ማስታወሻ ለመውሰድና ምንባቦችን አዳምጦ መልመጃ ለመሥራት ስለሚጠቅማቸው፤
- የማዳመጥ ክሂላቸው በሚገባ ያልዳበረ ስለሆነና መዳበር ስላለበት፤
- ተማሪዎች ካላዳመጡ ሊናገሩ፣ ሊያነቡ ወይም ሊጽፉ ስለማይችሉ፤
- የማዳመጥ ችሎታቸው ከፍተኛ ካልሆነ ምንባቡን አዳምጠው መረዳት ስለማይችሉ፤ የሚሉ ይገኙበታል ::

ለክሂሉ በሦስተኛና በአራተኛ ደረጃ ትኩረት እንሰጣለን ያሉ መምህራን ካቀረቧቸው ምክንያቶች መሀከል የሚከተሉት ይገኙበታል:-

- በመልመጃው የቀረቡት የማዳመጥ መለማመጃዎች እጅግ አነስተኛ ስለሆኑ፤
- የማዳመጥ ዕድሉ ሰፊ ስለሆነ ከሌሎች ክሂሎች በተጓዳኝ ሁኔታ ላይ ይገኛል በሚል ፤
- ተማሪዎች በሌሎቹ ክሂሎች ፍላጎታቸው አነስተኛ ስለሚሆን በነሱ ላይ አተኩራለሁ፤
- ለተማሪዎች በመንገር ይልቅ እራሳቸው እንዲመረምሩ ለማድረግ ነው በማለት መልሰዋል ::

ሠንጠረዥ 20 የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የተመረጡ ዝርዝር ዓላማዎች ብዛት

| ምርጫ | የጥያቄው ቁጥር 6.2 | | የጥያቄው ቁጥር 6.3 | |
|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 1 | 5 | 1 | 5 |
| 4 | 5 | 25 | 11 | 55 |
| 3 | 8 | 40 | 3 | 15 |
| 2 | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] |
| 1 | - | - | 1 | [illegible] |

በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ለማዳበር የተነደፉት ዝርዝር አላማዎች በጥያቄ ቁጥር 6.2 እና 6.3 ላይ የተገለጹት ብቻ ስለሆኑ እዚህ ለትንተና የቀረቡትም እነዚሁ ብቻ ናቸው ::

መምህራን በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ለማዳበር የተመረጡ ዝርዝር አላማዎች የተማሪዎቻቸውን ፍላጎት ምን ያህል እንደሚያሟሉ እንዲያመለክቱ ተጠይቀው ፤ " ተጠየቃዊ አስተሳሰብን ማዳበር " የሚለውን ዝርዝር አላማ 5 %. በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ፤ 25 % በከፍተኛ ደረጃ ፤ 40 % በመካከለኛ ደረጃ ፤ 30 % በዝቅተኛ ደረጃ ፤ ያሟላል በማለት መልሰዋል ::

" የተወሰነ ሀሳብን በራስ አባባል የማቅረብ ዘዴ " የሚለውን ዝርዝር አላማ 5 %. በጣም በከፍተኛ ደረጃ ፤ 55 % በከፍተኛ ደረጃ ፤ 15 % በመካከለኛ ደረጃ 20 % በዝቅተኛ ደረጃ 5 % በጣም በዝቅተኛ ደረጃ የተማሪዎችን ፍላጎት ያሟላል ብለዋል :: " ተጠያቃዊ አስተሳሰብን ማዳበር " የሚለው ዝርዝር አላማ በአብዛኞቹ መምህራን በመካከለኛ ደረጃ የተማሪዎችን ፍላጎት ያሟላል ተብሎ ሲጠቆም በከፍተኛና በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ያሟላል ያሉና በዝቅተኛ ደረጃ ያሟላል ያሉ መምህራን ቁጥር እኩል / 30 % / ነው :: የተወሰነ ሃሳብን በራስ አባባል የማቅረብ ዘዴ የሚለውን ዝርዝር አላማ አብዛኞቹ መምህራን /55 %/ በከፍተኛ ደረጃ የተማሪዎችን ፍላጎት ያሟላል ሲሉ ፤ 25 %መምህራን የተማሪዎችን ፍላጎት በዝቅተኛና በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ነው የሚያሟላው ብለዋል ::

ሠንጠረዥ 21 የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የተመረጡ ይዘቶች ብቃት

| | የ ጥ ያ ቄ ው ቁ ጥ ር | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 8.4 | | 8.5 | | 8.6 | | 8.8 | | 8.10 | | 8.11 | | 8.12 | |
| ምርጫ | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 2 | 10 | 3 | 15 | 4 | 20 | 2 | 10 | 1 | 5 | 4 | 20 | 3 | 15 |
| 4 | 11 | 55 | 9 | 45 | 6 | 30 | 4 | 20 | 9 | 45 | 8 | 40 | 6 | 30 |
| 3 | 3 | 15 | 6 | 30 | 5 | 25 | 7 | 35 | 7 | 35 | 4 | 20 | 55 | 25 |
| 2 | 3 | 15 | 2 | 10 | — | — | 4 | 20 | 2 | 10 | 3 | 15 | 3 | 15 |
| 1 | — | — | — | — | 2 | 10 | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 5 | 2 | 10 |
| × | 1 | 5 | — | — | 1 | 5 | 2 | 10 | — | — | — | — | 1 | 5 |

በጥያቄ ቁጥሮች ከ8.1–8.3፣ 8.7 ና 8.9 የቀረቡት ጉዳዮች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የሌሉ ይዘቶች በመሆናቸው እዚሁ ለትንተና አላስፈለገም ::

በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የማዳመጥን ክሂሉ ለማዳበር የቀረቡት ይዘቶች የተማሪዎቻቸውን የማዳመጥ ክሂል የማዳበር ብቃታቸውን እንዲገልጹ ተጠይቀው ፣ " የውይይት ሥርአት " 10 % በጣም ከፍተኛ ፣ 55 %፣ 75 % መካከለኛ ፣ 15 % ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ክሂሉን የማዳበር ብቃት አለው ሲሉ ፣ የጭውውት ስርአት 15 % በጣም ከፍተኛ ፣ 45 % ከፍተኛ ፣ 30 % መካከለኛ ፣ 10 % ዝቅተኛ ክሂሉን የማዳበር ብቃት አለው ብለዋል :: የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት የሚለው ይዘት 10 % በጣም ከፍተኛ፣ 20 % ከፍተኛ ፣ 35 % . መካከለኛ ፣ 20 % ዝቅተኛ ፣ 5 % በጣም ዝቅተኛ ክሂሉን የማዳበር ብቃት አለው ብለዋል ::

በጭብጥና በስሜታዊ አስተያየት መካከል ያለው ልዩነት 5 % በጣም ከፍተኛ 45 % ከፍተኛ ፣ 35 % መካከለኛ ፣ 10 % ዝቅተኛ ፣ 5 % በጣም ዝቅተኛ ክሂሉን የማዳበር ብቃት አለው ብለዋል ፍሬ ሃሳቦችን በማስታወሻ መያዝ 20 %በጣም ከፍተኛ 40 %ከፍተኛ ፣ 20 % መካከለኛ፣ 15 %፣ ዝቅተኛ 5 % በጣም ዝቅተኛ ክሂሎችን የማዳበር ብቃት አለው ብለዋል:: አንዱን ርእስ ጉዳይ በራስ አባባል ማቅረብ 15 % በጣም ከፍተኛ ፣ 30 % ከፍተኛ ፣ 25 % መካከለኛ ፣ 15 % ዝቅተኛ ፣ 10 % በጣም ዝቅተኛ ፣ ክሂሉን የማዳበር ብቃት አለው ብለዋል ::

መካከለኛ የብቃት ደረጃና ከዚያ በላይ ብቃት አላቸው የተባሉት ይዘቶች ውይይት 80 %፣ጭውውት 90 % ፣ ክርክር 75 % ፣ የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት 65 % ፣ የጭብጥና በስሜታዊ አስተያየት መካከል ያለው ልዩነት 85 %፣ፍሬ ሃሳብን በማስታወሻ መያዝ 80 %፣አንዱ ርዕስ ጉዳይ በራስ አባባል ማቅረብ 70 % ሲሆኑ ፣ እነዚህን ይዘቶች ክሂሉን የማዳበር ብቃታቸው ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ነው ያሉ መምህራን በዛት ከአማካይ እስከ በጣም ከፍተኛ ብቃት አለው ካሉት መምህራን በጣም ያነሰ ነው ::

ሠንጠረዥ 22 የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ መገመቻ በመምህራን ምዘና

| | የጥያቄው ቁጥር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 9.1 | | 9.2 | | 9.3 | | 9.4 | | 9.5 | | 9.6 | | 9.7 | | 9.8 | | 9.9 | | 9.10 | |
| ምርጫ | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 2 | 10 | 3 | 15 | — | — | 1 | 5 | 1 | 5 | — | — | 1 | 5 | 1 | 5 | — | — | — | — |
| 4 | 5 | 25 | 5 | 25 | 7 | 35 | 2 | 10 | 2 | 10 | 5 | 25 | 5 | 25 | 5 | 25 | 6 | 30 | 8 | 40 |
| 3 | 12 | 60 | 9 | 45 | 8 | 40 | 14 | 70 | 13' | 65 | 7 | 35 | 7 | 35 | 9 | 45 | 5 | 25 | 7 | 35 |
| 2 | 1 | 5 | 3 | 15 | 5 | 25 | 3 | 15 | 4 | 20 | 5 | 25 | 7 | 35 | 4 | 20 | 7 | 35 | 5 | 25 |
| 1 | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | 2 | 10 | — | — | 1 | 5 | 1 | 5 | — | — |
| x | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | 1 | 5 | — | — | — | — | — | — | — | — |

ከሠንጠረዥ 22 የቀጠለ

| | የጥያቄው ቁጥር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 9.11 | | 9.12 | | 9.13 | | 9.14 | | 9.15 | | 9.16 | | 9.17 | | 9.18 | | 9.19 | | 9.20 | |
| ምርጫ | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 2 | 10 | — | — | 2 | 10 | — | — | 1 | 5 | — | — | — | — | — | — | — | — | 1 | 5 |
| 4 | 12 | 60 | 4 | 20 | 5 | 25 | 3 | 15 | 4 | 20 | 3 | 15 | 4 | 20 | 6 | 30 | 5 | 25 | 5 | 25 |
| 3 | 4 | 20 | 10 | 50 | 6 | 30 | 8 | 40 | 12 | 60 | 10 | 50 | 5 | 25 | 7 | 35 | 4 | 20 | 8 | 40 |
| 2 | 2 | 10 | 5 | 25 | 6 | 30 | 7 | 35 | 3 | 15 | 7 | 35 | 6 | 30 | 7 | 35 | 6 | 30 | 4 | 20 |
| 1 | — | — | 1 | 5 | 1 | 5 | 2 | 10 | — | — | — | — | 5 | 25 | — | — | 5 | 25 | 2 | 10 |
| x | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — |

በጥያቄ ቁጥር 9 ላይ ለቀረቡ ሃያ የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች በአንድነት ታይተዋል :: በዚህም መሠረት እያንዳንዱ ጥያቄ ሃያ ምላሽ ስለሚኖረው በጠቅላላው አራት መቶ ምላሾች ይኖራሉ :: የሚከተለው ሠንጠረዥ የዚህን ምላሽ አማካይ ውጤት ያሳያል :-

ሠንጠረዥ 23 የተማሪዎች የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ በመምህራን ምዘና-ማጠቃለያ

| | የጥያቄው ቁጥር | |
|---|---|---|
| | ከ9.1 — 9.2 | |
| ምርጫ | አማካይ | % |
| 5 | 0.8 | 4.0 |
| 4 | 5.05 | 25.25 |
| 3 | 8.25 | 41.25 |
| 2 | 4.85 | 24.25 |
| 1 | 1.0 | 5.0 |
| × | 0.05 | 0.25 |

መምህራን " ተማሪዎች በሚከተሉት የማዳመጥ ንዑሳን ክሂሎች ምን ያህል ችሎታ አላቸው ? " ብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ ከሰጡት መልስ 4 % በጣም ከፍተኛ ፣ 25.25 % ከፍተኛ ፣ 41.25 መካከለኛ ፣ 24.25 % ዝቅተኛ ፣ 5 % በጣም ዝቅተኛ ችሎታ እንዳላቸው ጠቁመዋል ፣ ተማሪዎቹ በጣም ከፍተኛ ችሎታ እንዳላቸውና ችሎታቸው በጣም ዝቅተኛ መሆኑን የሚያሳዩ መልሶች ብዛት በጣም አነስተኛ ነው :: አብዛኛዎቹ መምህራን የተማሪዎቻቸው የማዳመጥ ችሎታ መካከለኛ መሆኑን ሲያመለክቱ ፣ ከፍተኛና ዝቅተኛ ነው ያሉትም ቁጥራቸው ተቀራራቢ ነው ::

ሠንጠረዥ 24 የተማሪዎች አዳምጦ የመረዳት መጠን በመምህራን ምዘና

| ምርጫ | ብዛት | % |
|---|---|---|
| ከ20 % በታች | 1 | 5 |
| ከ21 –40 % | 5 | 25 |
| ከ41 –60 % | 9 | 45 |
| ከ61 – 80 % | 3 | 15 |
| ከ80 % በላይ | 2 | 10 |

መምህራን፣ ተማሪዎቻቸው እንዲያዳምጡ ከሚቀርብላቸው ጉዳይ ውስጥ ምን ያህሉን እንደሚያዳምጡ እንዲጠቁሙ ተጠይቀው ሲመልሱ ፣ 5 % ተማሪ ዎቻቸው ከ20 % በታች እንደሚያዳምጡ፣ 25 % ተማሪዎቻቸው ከ21–40 % እንደሚያዳምጡ ፣ 45 % ተማሪዎቻቸው ከ41–60 % እንደሚያዳምጡ፣ 15 % ተማሪዎቻቸው ከ61–80 % እንደሚያዳምጡ ፣ 10 % ተማሪዎ ቻቸው ከ80 % በላይ እንደሚያዳምጡ ገልጸዋል :: አብዛኛዎቹ መምህራን /70 %/ ተማሪዎቻቸው ከሚቀርብላቸው ውስጥ ከ40 % በላይ የሆነውን አዳምጠው እንደሚረዱ ሲገልጹ ፣ 30 %ቱ ተማሪዎቻቸው ከሚቀርብላቸው የሚዳመጥ ጉዳይ ውስጥ አዳምጠው የሚረዱት ከ40 % ያነሰ መሆኑን ገልጸዋል :: የተማሪዎቹ አዳምጠው የመረዳት ችሎታ ከ40 % ያነሰ ነው ያሉ መምህራን ቁጥር / 30 %/ከግምት የሚገባ ነው :: ስለሆነም የተማሪዎችን አዳምጦ የመረዳት ችሎታ የሚያዳብሩ በርካታ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ሊቀርቡ ያሻሉ ::

ሠንጠረዥ 25 በአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ችሎታ ለሌሎች ትምህርቶች ያለው ጠቀሜታ

| | የ ጥ ያ ቄ ው ቁ ጥር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 41.1 | | 11.2 | | 11.3 | | 11.4 | | 11.5 | | 11.6 | | 11.7 | | 11.8 | | 11.9 | | 11.10 | | 11.11 | | 11.12 | |
| ምርጫ | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 8 | 40 | 4 | 20 | 1 | 5 | 1 | 5 | — | — | — | — | 1 | 5 | — | — | 4 | 20 | 1 | 5 | 1 | 5 | 2 | 10 |
| 4 | 7 | 35 | 2 | 10 | 1 | 5 | 3 | 15 | 2 | 10 | 3 | 15 | 6 | 30 | 5 | 25 | 6 | 30 | 8 | 40 | 4 | 20 | 12 | 60 |
| 3 | 3 | 15 | 6 | 30 | 6 | 30 | 5 | 25 | 5 | 25 | 5 | 25 | 10 | 50 | 9 | 45 | 5 | 25 | 7 | 35 | 7 | 35 | 1 | 5 |
| 2 | 1 | 5 | 6 | 30 | 6 | 30 | 8 | 40 | 7 | 35 | 6 | 30 | 1 | 5 | 4 | 20 | 4 | 20 | 2 | 10 | 7 | 35 | 4 | 20 |
| 1 | — | — | 1 | 5 | 4 | 20 | 2 | 10 | 5 | 25 | 5 | 25 | 1 | 5 | 1 | 5 | — | — | 1 | 5 | 1 | 5 | — | — |
| 0 | — | — | — | — | 1 | 5 | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — |
| × | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 1 | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 5 |

..// 72

ADDIS ABABA UNIV... ILS LIBRA...

"ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክሂሎታቸውን ማዳበራቸው ሌሎች ትምህርቶችን ለመከታተል ምን ያህል ይጠቅማቸዋል ?" ብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራን በሰጡት መልስ መካከለኛና ከዚ በላይ ጠቀሜታ አለው ባሉት ውስጥ 90 % ለአማርኛ ፣ 60 % ለእንግሊዝኛ፣40 % ለሂሳብ ፣ 45 % ለባዮሎጂ፣ 35 % ለፊዚክስ ፣ 40 % ለኬሚስትሪ፣35 % ለታሪክ ፣ 70% ለጂኦግራፊ፣ 75 % ለስርሻ ፣ 80 % ለባልትና፣ 55 % ለምርት ቴክኖሎጂ፣ 75 % ለስፖርት ትምህርቶች ይጠቅማል ብለዋል ። ጠቀሜታው ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ነው ከተባሉት ውስጥ ለሂሳብ ፣ ለባዮሎጂ፣ ለኬሚስትሪና ለፊዚክስ የሚሉት መልሶች ከፍተኛውን ቁጥር / ከ50 – 60 % ይዘዋል ። ይህም የሚያሳየው በአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል መዳበር ከቁጥር ጋር የተያያዙና የማይገናኙ ትምህርቶችን ለመከታተል ከሚሰጠው ጠቀሜታ ይልቅ ለሌሎች ትምህርቶች የሚሰጠው ጠቀሜታ እንደሚበልጥ ነው ።

### 4.2.3: ከመርሀ ትምህርት ባለሙያው መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

ለመርሀ ትምህርት ባለሙያው የተዘጋጀውን መጠይቅ ሰባት የአማርኛ ትምህርት ኤክስፐርቶች ሞልተዋል ። ከነዚህ ሁለቱ አፍ መፍቻቸው አማርኛ ሲሆን፣ አንዱ አፍ መፍቻው አማርኛና አሮምኛ ነው ። ሰባቱም ወንዶች ሲሆኑ የትምህርት ደረጃቸው ቢኤና ከቢኤ በላይ ናቸው ። የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርትንና የመማሪያ መጽሐፍትን በማዘጋጀት ሥራ ላይ ከሰባት እስከ [illegible] አመት የቆዩ ናቸው ።

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚሰጠው በበንተኛ ቋንቋነት እንደሆነ ተጠይቀው ሁለቱ "በአፍ መፍቻ ቋንቋነት ነው" ሲሉ አንዱ ግን "እንደ አንድ የትምህርት አይነት ነው የሚሰጠው" በማለት መልሰዋል ።

ለዘጠነኛ ክፍል የሚሆኑ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሲመረጡ በምን መመዘኛ እንደተመረጡ ተጠይቀው በሰጡት መልስ አንዱ "በተማሪዎች ችሎታ"፣ ሌላኛው "የበርአት ትምህርት አነዳደፍ መርሀ ላይ ተመስርቶ"፣ ሲሉ ሰባተኛው "ከሞላ ጎደል የተማሪው ፍላጎትና ችሎታ፣ ቋንቋው በት/ቤትና በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚሰጠው አገልግሎት፣ የቋንቋው ሥነ ልሣናዊ ባህሪ በመመዘኛነት ተወስደው ነው" ብለዋል ።

ሁለቱ ለክፍሉ የሚሆኑ መርሀ ትምህርትና የመማሪያ መጽሀፍት በአንዱ ቡድን /ፖነል/ እንደሚዘጋጅ ገለጸዋል ። እንጅ ግን ለዚህ ጥያቄ መልስ አለሰጡም ።

ለዘጠነኛ ክፍል በሚቀርበው የቋንቋ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ለሰጠው የሚገባውን የትኩረት ደረጃ በተመለከተ ሁለቱ በአንደኛ ደረጃ ሊተከርባቸው ይገባል ሲሉ ለዚህም የሰጡት ምክንያት፡—

1. የቋንቋ አካባቢያዊ መሠረት ማዳመጥ ስለሆነ ፤
2. በተግባራዊ እንቅስቃሴ በይበልጥ የሚሠራበት ንግግር በመሆኑ የማዳመጥ ክሂል ከዳበረ አያሌ ተግባሮችን ማከናወን ይቻላል ። የሚሉ ናቸው ።

ሠንጠረዥ 26 የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች የብቃት ደረጃ በመርሀ ትምህርት ባለሙያዎች ምዘና ፤

.../74

ሠንጠረዥ 26 የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች የብቃት ደረጃ በመርሀ ትምህርት ባለሙያዎች ምዘና።

| ምርጫ | የጥያቄው ቁጥር | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 6.4 | | 6.5 | | 6.6 | | 6.8 | | 6.10 | | 6.11 | | 6.12 | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 1 | 33.3 | 1 | 33.3 | 1 | 33.3 | – | | 1 | 33.3 | 1 | 33.3 | 1 | 33.3 |
| 4 | 1 | 33.3 | 1 | 66.6 | 1 | 33.3 | 2 | 66.6 | 1 | 33.3 | 1 | 33.3 | 1 | 33.3 |
| 3 | 1 | 33.3 | 1 | – | – | – | 1 | 33.3 | – | – | – | = | – | – |
| 2 | – | – | – | – | – | – | – | – | – | – | – | – | 1 | 33.3 |
| 1 | – | – | – | – | – | – | – | – | 1 | 33.3 | 1 | 33.3 | – | – |
| x | – | – | – | – | 1 | 33.3 | – | – | – | – | – | – | – | – |

በጥያቄ ቁጥሮች ከ6.1 – 6.3 ፣ 6.7 እና 6.9 የተገለጹት ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ያልቀረቡ ይዘቶች በመሆናቸውና እዚህ ለትንተናው በለማያስፈልጉ አልቀረቡም ::

በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በቀጥታ የማዳመጥን ክሂል እንዲያዳብሩ የቀረቡ ይዘቶች በመርሀ ትምህርት ባለሙያዎቹ ምዘና መሠረት ብቃት አሏቸው ተብለዋል :: አብዛኞቹ በከፍተኛ ደረጃና በጣም በከፍተኛ ደረጃ ብቁ ናቸው ተብለዋል :: በጥያቄ ቁጥሮች 6.10 ፣ 6.11 እና 6.12 የቀረቡ ይዘቶችን 33.3 % በከፍተኛ ደረጃ፣ 33.3 % በጣም በከፍተኛ ደረጃ ክሂሉን ያዳብራሉ ሲሉ ፣ 33.3 % በዝቅተኛና በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ነው ክሂሉን ሊያዳብሩ የሚችሉት ብለዋል :: ክሂሉን የማዳበር ብቃታቸው ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ነው የተባሉት ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ሌሎች ክሂሎችን ለማዳበር ተዘርጠው አግረመንገዳቸውን የማዳመጥን ክሂል ያዳብራሉ የተባሉ ይዘቶች ናቸው ::

4.3 :- <u>የመጠይቆች ምላሽ ትንተናና ንጽጽር</u>

ከተማሪው ከመምህሩና ከመርሀ ትምህርት ባለሙያው መጠይቆች በተገኘው መረጃ መሠረት:-

1. በዘጠነኛ ክፍል የምናገኛቸው ተማሪዎች አብዛኞቹ / 92.6 % / እፋቸውን በአማርኛ የፈቱ ናቸው ፣ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ 7.3 % ናቸው :: በጾታ ረገድ የሴቶቹ ቁጥር ከወንዶቹ በ16.6 % ይበልጣል :: የዚህ ክፍል ተማሪዎች አብዛኞቹ ዕድሜያቸው በ14–16 ዓመት ሲሆን ፣ ከ13 ዓመት በታችና ከ17 –19 ዓመት ዕድሜ የሆኑ ተማሪዎችም አሉ ::

የተማሪዎቹን ዳራ ማወቁ የምናቀርባቸውን የትምህርት ይዘት በንመርጥ ትምህርቱ በተማሪዎቹ ዳራ ጋር ተስማሚ እንደሆን ለማድረግ ይረዳል :: ለምሳሌ ተማሪዎች በተወሰነ የዕድሜ ክልል ሊኖራቸው የሚችለውን ዝንባሌ መገመት ይቻላል፣ ወይም ደግሞ ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች ካሉ የትምህርት ይዘት ሲመረጥ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ ምክንያት የሚፈጸሙ ስህተቶች ካሉ ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ይጠቁማል :: በዚህ መሠረት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር ይዘቶችን ስንመርጥ በወጣትነት የዕድሜ ክልል ለሚገኙ ተማሪዎች ሥነ ልቡና የሚስማሙና አፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ለሚማሩ ተማሪዎች የሚሆኑ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን መምረጥ እንደሚኖርብን መዘንጋት የለብንም ::

2. ተማሪዎቹ፣ ቋንቋውን ከሚማሩባቸው አላማዎች አንዱ አዳምጦ የመረዳት ችሎታቸውን ማዳበር መሆኑን ገልጸዋል ። 15.6 % በመካከለኛ ፣ 78.6 % በከፍተኛና በጣም በከፍተኛ ደረጃ አላማቸው መሆኑን ገልጸዋል ።ይህም ተማሪዎቹ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር በሚቀርቡ ትምህርቶች ላይ በጐ አመለካከትና ዝንባሌ እንደሚኖራቸው ይጠቁማል ።

3. የተማሪዎችን በትምህርት ቤትና በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉ የቋንቋ አጠቃቀማቸውን ሁኔታ ማወቅ ከተማሪዎቹ ልምድ ጋር የሚጣጣምና ሊጠቀሙበት የሚችሉትን የቋንቋ ትምህርት ይዘት ለመምረጥ ይረዳል ።በዚህ መሠረት ተማሪዎች፣ የሚያዘወትሯቸውን የማዳመጥ ተግባራትና የማዳመጥ ችግሮቻቸውን በጠቆሙት መሠረት በትምህርት ቤትም ሆነ በኅብረተሰቡ ውስጥ በተለያዩ የማዳመጥ ተግባራት ለምሳሌ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን፣ በክፍል ውስጥ ገለጻዎችን ፣ መመሪያዎችንና ጥያቄዎችን፣ በድምጽ ማጉያ የሚነገሩ ማስታወቂያዎችን፣ በስልክ የሚተላለፉ መልእክቶችን፣ ውይይቶችንና ጭውውቶችን እንደሚያዳምጡ ገልጸዋል ።በነዚህ የማዳመጥ ተግባራት በፍጹም አንጋ ተፍም ያሉ ተማሪዎች ‥በስልክ የሚተላለፍ መልእክቶችን‥ ማዳመጥ ከሚለው በስተቀር /12.6 %/ በሌሎቹ ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ ነው ።

በለዚህ በመረጃው ላይ የሚታየውን ልዩነት መሠረት አድርጎ በሁሉም የማዳመጥ ተግባራት ላይ የተመሠረተ ልምምድ በተለያየ መጠን ሊቀርብላቸው ይገባል ።

የማዳመጥ ችግሮቻቸውን በተመለከተ የማዳመጥ ችግሮች ይሆናሉ ተብለው በቀረቡላቸው አምስት ዝርዝሮች ውስጥ ‥ የንግግሩን ድምጸት ለይቶ አለማወቅ ‥ ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ የማዳመጥ ችግሬችን ነው ያሉትና፣ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ችግሬችን ነው ያሉት ቁጥራቸው በጣም ተቀራራቢ / 37.6 % ና 36.3% በተከታታይ / ነው ። በሌሎቹ የማዳመጥ ችግሮች ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ ችግር ነው ካሉት ይልቅ ዝቅተኛ በጣም ዝቅተኛ ችግር ነው ያሉት ተማሪዎች ቁጥር ይበልጣል ። የተማሪዎችን የማዳመጥ ችግር ለማስወገድ እንዲቻል የትምህርት ይዘት በሚመረጥበት ጊዜ የችግሩን ደረጃ መለያየት መሠረት በማድረግ የማዳመጥ ችግሮቻቸውን ከግምት ያስገባ ይዘት መምረጥ ይቻላል ።

4. በክፍል ውስጥ የሚቀርበውን የማዳመጥ ትምህርት አቀራረብ በተመለከተ ተማሪዎች የሚያዳምጡትን ነገር መምህሩ በንባብ ወይም በንግግር ቢያቀርብላቸው ይመርጣሉ። "በካሴት ተቀድቶ ቢቀርብ እንመርጣለን" ያሉ ተማሪዎች ቁጥርም ከግምት የሚገባ ነው። በመርሀ ትምህርቱ ላይ የቀረቡ የማዳመጥ ይዘቶች በክፍል ውስጥ ተግባራዊ የሚሆኑበት መንገድ በሚጠቀምበት ጊዜ የተማሪዎችን ዝንባሌ ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል።

5. በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር በቀጥታና በተዘዋዋሪ የቀረቡ ይዘቶች ለተማሪዎች በትምህርት ቤትም ሆነ በኅብረተሰቡ ውስጥ ለማዳመጥ ምን ያህል እንደሚጠቅሟቸውና ክሂሉን የማዳበር ብቃታቸው ምን ያህል እንደሆነ ከተማሪዎችና ከመምህራኖቻቸው የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በሁሉም ይዘቶች ተማሪዎች / ከ16–50.3 %/ በመካከለኛ ደረጃ፣ በከፍተኛ ደረጃና በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ያስፈልገናል ብለዋል ። ይዘቶቹ በዝቅተኛና በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ያስፈልገናል ያሉት ከ2.6 – 11 % የሚደርሱ ናቸው።

መምህራን ከ65–90 % ሁሉንም ይዘቶች በመካከለኛ ደረጃና ከዚያ በላይ ክሂሉን የማዳበር ብቃት እንዳላቸው ሲገልጹ፣ የመርሀ ትምህርት ባለሙያዎችም 66 % ና ከዚያ በላይ ይዘቶቹ በከፍተኛና በጣም በከፍተኛ ደረጃ ብቃት አላቸው ብለዋል ። ይዘቶቹ ብቃት ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ነው ያሉት መምህራን ከ5 %–25 % ይደርሳሉ። ይህ ቁጥር ከግምት የሚገባ በመሆኑ የይዘቶቹን ብቃት መመርመሩ አስፈላጊ ነው።

በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች በመምህራንም ሆነ በመርሀ ትምህርት ባለሙያዎች የተሰጠው ምላሽ ክሂሉን የማዳበር ብቃት እንዳላቸው ቢያሳይም ፣ መምህራን ከ5 % – 25 % የይዘቶቹ ብቃት ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ገልጸዋል፤ ከዚህም ጋር ተማሪዎች ከ2.6 – 11 % የሚደርሱ በትምህርት ቤትም ሆነ በኅብረተሰቡ ውስጥ ለማዳመጥ በይዘቶቹ አንጻር የሚያዳብሩት የማዳመጥ ክሂል ጠቀሜታው ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

6. በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ለማዳበር የተመረጡ ዝርዝር አላማዎቹ ምን ያህል የተማሪዎቻቸውን የማዳመጥ ፍላጎት እንደሚያሟሉ መምህራን በሰጡት ምላሽ ። ተጠየቃዊ ስለ ተከበበን ማዳበር ። የሚለውን ዝርዝር አላማ 70 % በመካከለኛ ደረጃና ከዚ በላይ የተማሪዎቹን ፍላጎት ያሟላል ሲሉ፣ 30 % በዝቅተኛ ደረጃ ያሟላል ብለዋል፤ ። የተወሰነን ሃሳብ በራስ አባባል የማቅረብ ዘዴ ። የሚለውን ዝርዝር አላማ 75 % በመካከለኛ ደረጃና ከዚ በላይ የተማሪዎቹን ፍላጎት ያሟላል ሲሉ ፣ 25 % በዝቅተኛና በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ያሟላል ብለዋል ።በሁሉም ዝርዝር አላማዎች በመካከለኛ ደረጃና ከዚያ በላይ ፍላጎታቸውን ያሟላል ያሉት መምህራን ቁጥር በርካታ ቢሆንም በዝቅተኛና በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ነው የተማሪዎቹን ፍላጎት የሚያሟላው ያሉት ቁጥርም / 30 % ና 25 % በቅደም ተከተል / ከግምት የሚገባ ነው ።

7. የተማሪዎቹን የማዳመጥ ችሎታ ለመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች እንደሚያመለክቱ :—

- በተማሪውና በመምህሩ መጠይቆች ላይ ተማሪዎች ከሚቀርብላቸው የማዳመጥ ጉዳይ ምን ያህሉን እንደሚያዳምጡ የሚያብየው መረጃ አብዛኞቹ ተማሪዎች ከመካከለኛ ደረጃ በላይ ቢያዳምጡም ከመካከለኛ ደረጃ በታች የሚያዳምጡት ቁጥርም ከግምት የሚገባ ነው ። በለዚህ በመርሀ ትምህርቱ ላይ ለተማሪዎቹ የማዳመጥ ክሂሎቸውን የሚያዳብሩ ይዘቶችና ስምምዶች ሊቀርቡላቸው ይገባል ።

- አብዛኞቹ ተማሪዎች / 66.2 % / በቋንቋው በሚጠቀሙ ጊዜ አዳምጦ የመረዳት ችሎታቸው ከመካከለኛ ደረጃ በላይ ነው ሲሉ ፣ 66.6 % ደግሞ ከመካከለኛ ደረጃ በታች መሆኑን አመለከተዋል ። የቀሩት /26.3 % / መካከለኛ የችሎታ ደረጃ እንዳላቸው ገለጸዋል፣ የኋለኛው መረጃ ከሁሉ በበቂ ሁኔታ ስለመዳበሩንና ተጨማሪ የማዳመጥ ስምምዶች እንደሚያስፈልጉ ይጠቁማል ።

- በተማሪውና በመምህሩ መጠይቆች ላይ የተማሪዎችን አጠቃላይ የማዳመጥ ችሎታ ለመገመት ለቀረቡት ጥያቄዎች በተሰጠው ምላሽ መሠረት አብዛኛቹ ተማሪዎች በተለያዩ የማዳመጥ ንኡሳን ክሂሎች ችሎታቸው መካከለኛና ከዚ በላይ ነው ። መምህራን ተማሪዎቻቸው 41.25 % መካከለኛ ፣ 29.25 %

ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ ችሎታ አላቸው ሲሉ ፣ ተማሪዎቹ 25.4 % መካከ ለኛ 58.30 % ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ ችሎታ አለን ብለዋል ::ከተማሪዎቹ 32.5 % ችሎታቸው ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ሲገልጹ፣ ከመምህራን 29.25 % የተማሪዎቻቸው የማዳመጥ ችሎታ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ገልጸዋል :: በዚህ መሠረት የዚህ ክፍል ተማሪዎች የተለያዩ የማዳመጥ ንኡሳን ክሂሎችን ያካተተ የትምህርት ይዘት ሊቀርብላቸው ይገባል ::

- በመምህሩ መጠይቅ ተማሪዎች የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጾች ምን ያህል እንደሚረዱ ለቀረበው ጥያቄ ከመምህራን 80 % ተማሪዎቻቸው የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጾች በመካከለኛ ደረጃና ከዚ በላይ እንደሚረዱ ገልጸዋል :: ተማሪዎቹ አብዛኛዎቹ አፋ ቸውን የፈቱት በአማርኛ ስለሆነ የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጽ በመረዳት ረገድ ያለባቸው ችግር መጠነኛ ነው :: ከመምህራን 10 % ተማሪዎቻቸው በባህላዊ አገላለጾች የሚረዱት በዝቅተኛ ደረጃ መሆኑን ገልጸዋል :: ተማሪዎቹ በበኩላ ቸው 53.6 % የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጾች አለማወቅ በሚያዳምጡበት ጊዜ ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች አንዱ መሆኑን ገልጸዋል ::

8. ተማሪዎች ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች በየትኛው የበለጠ እንደሚጠቀሙ በሰጡት ምላሽ የማዳመጥን ክሂል አስመልክቶ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች / 90.9 % / ክሂሉ በጣም እንደሚጠቀሙቸው ነው ያመለከቱት :: በዚህ መሠረት የማዳመጥ ክሂሉ ለተማሪው ከሚሰጠው ከፍተኛ ጠቀሜታ አንጻር በበቂ ሁኔታ ትኩረት ተሰጥቶት ሊዳበር ይገባል :: መምህራን ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መሀከል ለዚህ ክፍል ተማሪዎች ትኩረት ሰጥተው የሚያስተምሩት የትኛውን ክሂል እንደሆነ ሲያመለከቱ 70%. የማዳመጥን ክሂል በ1ኛ ደረጃ ትኩረት እንሰጠዋለን:: ለዚህም በሰጧቸው ምክን ያቶች ውስጥ የተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል በሚገባ ካልዳበረ፣ የማዳመጥ ክሂላ ቸው ካልዳበረ በሌሎች ክሂሎች የመጠቀም ችሎታቸው የተሟላ ስለማይሆን የሚሉ ይገኙበታል:: ለማዳመጥ ክሂሉ በሁለተኛና በአራተኛ ደረጃ ነው ትኩረት የምንሰጠው ያሉ መምህራን /25%/ ካቀረቧቸው ምክንያቶች ውስጥ በመልመኛ የቀረቡ የማዳመጥ ልምምዶች እጅግ አነስተኛ ስለሆኑ፣ የማዳመጥ አደራ በራ ስለሆነ ከሌሎች በተሻለ ሁኔታ ላይ ስለሚገኝ፣ የሚሉ ይገኙበታል::

የመርሀ ትምህርት ባለሙያዎች ለዘጠነኛ ክፍል በሚቀርበው የቋንቋ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥ ክሂሎ ከአራት የቋንቋ ክሂሎች መሀከል 66.6 % በአንደኛ ደረጃ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ሲሉ ለዚህም የሰጡት ምክንያት የቋንቋ አከባቢያዊ መሠረቱ ማዳመጥ ነው ፤ በተግባራዊ እንቅስቃሴ በይበልጥ የሚሰራበት ነገር በመሆኑ የማዳመጥ ክሂሎ ከዳበረ አያሌ ተግባሮችን ማከናወን ይቻላል የሚል ነው ። 33 % ማዳመጥ ከአራቱ ክሂሎች መሀከል በሶስተኛ ደረጃ ሊተኮርበት ይገባል ሲሉ ለዚህም የሰጡት ምክንያት የቋንቋ ክፍል በመሆኑ በዚህ ደረጃ ተማሪው በአብዛኛው አራሱ መናገርና መጻፍ አለበት የሚል ነው ።

ከተማሪዎች ፤ ከመምህራንና ከመርሀ ትምህርት ባለሙያዎች የተገኘው መረጃ በአመዛኙ የማዳመጥ ክሂሎ ለዚህ ክፍል ተማሪዎች በጣም ጠቃሚ እንደሆነና ከሌሎቹ ክሂሎች በበለጠ ትኩረት ተሰጥቶት ሊዳበር እንደሚገባ ያመለክታል ።

9. ተማሪዎች ማዳመጥ የሚወዱት እንዴት ያሉ ጉዳዮችን እንደሆነ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከቀረቡላቸው ምርጫዎች፡- ስለሀገር ፤ ስለትምህርት ፤ ስለፍቅር ፤ ስለጓደኝነት ፤ ስለጤና ፤ ሣይንስ ነክ ፤ ስለፖለቲካ ፤ ስለ ሃይማኖት ፤ ስለቤተሰብ ከሚሉ ርእሶች መሀከል ፖለቲካን በጣም ዝቅተኛ ምርጫቸውን ነው ያሉ 53.6% ሲሆኑ ሌሎቹን ርእሶች ከ31.6 % – 69 % የሚሆኑት በጣም በከፍተኛ ደረጃ መርጠዋል ። ዝርዝር መረጃውን በማየትና የተማሪዎቹን ዝንባሌ በማወቅ ለማዳመጥ ትምህርት በሚቀርቡላቸው ጽሁፎች ውስጥ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ከዝንባሌያቸው ጋር የሚስማማ ማድረግ ይቻላል ።

10. መምህራን ተማሪዎቻቸውን በአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂሎታቸውን ማዳበራቸው ሌሎች ትምህርቶችን ለመከታተል ምን ያህል እንደሚጠቅማቸው ሲገልጹ፤ ቁጥር ነክ ለሆኑና ለሣይንስ ትምህርቶች ጠቀሜታው ዝቅተኛ ነው ሲሉ ፤ ለሌሎቹ በአብዛኛው በቃላት ገለጻ ማድረግን ለሚፈልጉ ትምህርቶች በመካከለኛ ደረጃና ከዚያ በላይ ጥቅም ይሰጣል ብለዋል ። ከዚህም ጋር የዚህ ክፍል ተማሪዎች የእርሻና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርቶችን በአማርኛ ቋንቋ እንደሚማሩ ይታወቃል ።

...// 81

## ምዕራፍ 5:— ማጠቃለያና ጥቆማ

### 5.1 ማጠቃለያ

ማዳመጥ በኅብረተሰቡ ውስጥ በቋንቋ ለመግባባትም ሆነ በትምህርት መስክ ከፍተኛ ድርሻ አለው ። ስለዚህ የማዳመጥ ክሂል በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶት ሊዳበር ይገባል ። በተፈጥሮ የሚገኘው የማዳመጥ ችሎታ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥና የተለያዩ ጉዳዮችን ለማዳመጥ ብቻውን በቂ አይሆንም ። በአፍ መፍቻ ቋንቋም እንኳ ቢሆን አዳምጦ የመረዳት ችሎታ መቶ ፐርሰንት መድረስ እንደማይችል ምሁራን ይናገራሉ ። ነገር ግን ሆን ተብሎ ክሂሉን ለማዳበር በሚቀርቡ ልምምዶች አማካይነት የማዳመጥን ክሂል ከተፈለገው ደረጃ ለማድረስ ይቻላል ።

ማዳመጥ በትምህርትም ሆነ በሥራ መስክ እንዲሁም በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ካለው ከፍተኛ ድርሻ አንጻር እንደሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ራሱን ችሎ በተናጠልና እንዲሁም ከሌሎቹ ክሂሎች ጋር ተዳብሎ አላማ ተነድፎለትና ይዘት ተመርጦለት ሊዳበር የሚገባው ክሂል ነው ። የማዳመጥን ክሂል ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አዋህዶ በማቀረብ ለማዳበር ቢቻልም ትኩረት ለመስጠት ሲባል በአላማና በይዘት ደረጃ ራሱን ችሎ መቀረቡ የተሻለ ይሆናል ።

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር ምን ያህል ትኩረት እንደተሰጠውና ክሂሉን ያዳብራሉ ተብለው የተመረጡትን ይዘቶች ብቃት በተመለከትንበት ወቅት ከሚከተሉት የማጠቃለያ ነጥቦች ላይ ለመድረስ ተችሏል ።

1. የማዳመጥ ክሂል በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በአጠቃላይ አላማ፣ በዝርዝር አላማና በይዘት ደረጃ ከመናገር ክሂል ጋር ተዳብሎ ቀርቧል፣ ከዚህም ጋር ይዘቶቹ ግልጽ ባልሆኑና አሻሚ በሆነ መንገድ ስለተጻፉ በመርሀ ትምህርቱ ላይ ተንተርሶ ለሚያስተምር የቋንቋ መምህር ወይም የመማሪያ መጽሀፍት አዘጋጅ በየትኛው ክሂል ላይ ማተኮር እንደሚገባው በትክክል አያመለክትም ።

2. የማዳመጥ ክሂል በመናገር ክሂል ጋር ተደብሎ በቀረበበት ሁኔታም ለሁለቱም ክሂሎች በአንድነት የቀረቡት ይዘቶች ብዛት ለሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ከቀረቡት ይዘቶች ብዛት ጋር ሲነጻጸር እጅግ በጣም ጥቂት ናቸው ። በአጠቃላይ በዚህ ክፍል የማዳመጥ ክሂል በቂ ትኩረት አላገኘም ።

በተማሪዎች የፍላጎት አሰሳ ጥናት ላይ ከተማሪው ፣ ከመምህራና ከመርሀ ትምህርቱ ባለሙያው መጠይቆች የተገኘው መረጃ ለዚህ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል መዳበር በጣም አስፈላጊ መሆኑንና ከሌሎቹ ክሂሎች የበለጠ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ያሳያል ። በዚህ መሠረት በመርሀ ትምህርቱ ላይ የቀረቡት ይዘቶች ብዛት ከተማሪዎቹ ፍላጎት ጋር የሚመጣጠን አይደለም ። በጣም አነስተኛ ናቸው ።

3. በየሴሚስተሩ ተመጣጣኝ አቀርቦት አይታይም ፣ በአንደኛው ሴሚስተር ሰባት ይዘቶች ሲቀርቡ በሁለተኛው ሴሚስተር አንድ ይዘት ብቻ ተመርጦ ቀርቧል ።

4. የክብደት ደረጃቸውን በተመለከተ በአንደኛውና በሁለተኛው ይዘቶች ከቀረቡት ልምምዶች ይልቅ በሰባተኛው ይዘት የቀረበው በጣም ቀላል ነው ። በአንደኛው ሴሚስተር የቀረቡ ልምምዶች በሁለተኛው ሴሚስተር ከቀረበው የከበዱ ናቸው ። በይዘቶቹ አንጻር የቀረቡት ልምምዶች የክብደት ደረጃቸውን ያልጠበቁ ከቀላል ወደ ከባድ እያደጉ የማይሄዱ ልምምዶች ናቸው ።

5. በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ይዘቶቹ ገለጻነት በጐደለው ሁኔታ ቢጻፉም አንዳንዱ የማዳመጥ ዋና ንኡሳን ክሂሎችን ለማዳበር ሞክረዋል ። በዚህም በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማዳመጥ ትምህርት ይበልጥ ሊተኮርባቸው በሚገቡ ይዘት አይነቶች ማለትም ለመረጃ መሻት ማዳመጥ ላይ በይበልጥ አተኩረዋል ። በተማሪው መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሠረት የተማሪዎቹ አፍ መፍቻ ቋንቋ የአብዛኞቹ / 92.6 % / አማርኛ መሆኑ አይዘነጋም ።

...// 83

የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ገና ከመግቢያው እንደሚጠቁመው መርሀ ትምህርቱ ለዝግጅ መሠረት ያደረገው "በተወሰነ የክፍል ደረጃ ተማሪዎች ምን ሊማሩ ይገባቸዋል ?" የሚለውን ጥያቄ ነው ። በመሠረቱ የቋንቋ መርሀ ትምህርት ለዝግጅ መሠረት ማድረግ ያለበት የኅብረተሰቡን በተለይም የተማሪውን የቋንቋ ፍላጎት ነው ። "ተማሪው ቋንቋውን የሚማረው በቋንቋው ምን ለማድረግ ነው ?" "በኅብረተሰቡ ውስጥ ቋንቋው የሚኖረው ሚና ምንድነው ?" "ቋንቋውን ለመማር ምን ማድረግ አለባቸው ?" የሚሉትን ጥያቄዎች ይዘ ለነዚህ ጥያቄዎች ከሚሰጡ ምላሾች አንፃር ተስማሚው መርሀ ትምህርት ይዘጋጃል ። በመርሀ ትምህርት ዝግጅት ውስጥ ዋነኛው ጉዳይ ይዘት እንደሆነ የቋንቋው ትምህርት ምሁራን ይናገራሉ ። ለትምህርት የሚቀርበው ይዘት ሲመረጥ ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥናት ማድረግን ይጠይቃል ። በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የሚቀርቡ ይዘቶችን በመምረጥ ረገድ የተማሪው ዓላማ፣ ፍላጎትና ችሎታው፣ ቋንቋውን የሚማርበት አላማ ሊተኮርባቸው የሚገባ መሠረታዊ ነገሮች ናቸው ። በዚህ አንፃር የዘጠነኛ ክፍል መርሀ ትምህርት ለዝግጅ የተደረገ ጥናት በለመኖሩ የሚጠቁም ነገር የለም ። እንዲያውም በመርሀ ትምህርቱ መግቢያ ላይ መርሀ ትምህርቱ በጥናት ላይ ያልተመሠረተ መሆኑን ይገልጻል ።

የቋንቋ መርሀ ትምህርት ለዝግጅ ከሁሉም በላይ የይዘት ምርጫ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥናት ሊደረግ እንደሚገባ ከላይ ተገልጿል ። በሚደረገው ጥናት ውስጥም የተማሪዎችን ፍላጎት ና ችሎታ ማጥናት አንዱ ነው ። በዘጠነኛ መርሀ ትምህርት ውስጥ የቀረቡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ያለጥናት የተመረጡ መሆናቸው በመርሀ ትምህርቱ ላይ ተገልጿል ። ያለ ጥናት የቀረቡ ይዘቶች ደግሞ የተማሪውን ፍላጎት ምን ያህል ሊያሟሉ እንደሚችሉ በቀላሉ መገመት አያዳግትም ።

የማዳመጥን ክሂል በተመለከተ ክሂሉን በትምህርት ቤት የማስተማር አላማ ተማሪው የሚሰማውን ነገር የመረዳት የመተርጎም፣ የመገምገምና የራሱን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችለውን ክሂል ለማዳበር፣ በማዳመጥ ችሎታው እንዲተማመንና በኅብረተሰቡ ውስጥ ማዳመጥን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲጠቀም ለማስቻል በልዩ ልዩ የማዳመጥ አውዶችና የማዳመጥ አይነቶች ተግባራዊ ልምምድ መስጠት ነው ። በዚህም መሠረት የማዳመጥ ልምምዶች ለዝግጅ ተማሪዎች ሊጠቀ

ሙያቸውና ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ የማዳመጥ ሁኔታዎችንና ችግሮችን ከግምት ያስገቡ መሆን ይኖርባቸዋል ። በዘመነኛ ክፍል መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች ግን በጥናት ላይ ያልተመሠረቱ በመሆናቸው የተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም ፣ ለማዳመጥ የሚፈልጓቸውን ርእሰ ጉዳዮች፣ የሚዳመጥ ነገር የአቀራረብ ዝንባሌያቸውን፣ ማዳመጥ በተማሪዎች ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለውና በርካታ ለምምዶች እንደሚያስፈልጉ፣ ወዘተ. የመሳሰሉትን ከግምት ያላስገባ ዝግጅት ነው ።

የተማሪዎችን ፍላጐትና ችሎታ እንዲሁም የቋንቋ አጠቃቀም ከማዳመጥ ክሂል አንፃር ለማጥናት የተደረገው ሙከራ ውጤት እንደሚያሳየው በዘመነኛ ክፍል የምናገኛቸው ተማሪዎች አብዛኞቹ አማርኛ አፍ መፍቻቸው የሆኑ ናቸው ። ቋንቋውን ከሚማሩበት አላማቸው አንዱ አዳምጦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር ቢሆን አብዛኞቹ ተማሪዎች የማዳመጥ ችሎታቸው መካከለኛና ከዚያ በላይ ቢሆንም ችሎታቸው ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ የሆኑ ተማሪዎች ቁጥርም ከግምት የሚገባ ነው ። የመጠይቆቹ ምላሽ የተማሪዎችን ፍላጐት ችሎታና የቋንቋ አጠቃቀም በተመለከተ በርካታ ዝርዝር ሁኔታዎችን አመልክቷል ።ይህንንም " የመጠይቆች ምላሽ ትንተናና ንጽጽር "ከሚለው ክፍል / ገጽ 63 –67 / መመልከት ይቻላል ። በአጠቃላይ ግን ለዚሁ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል በትምህርትቤትም ሆነ በኅብረተሰቡ ውስጥ በጣም ጠቃሚ እንደሆነና ከሌሎቹ ክሂሎች በበለጠ ትኩረት ተሰጥቶት ሊዳበር እንደሚገባ ከመጠይቆቹ የተገኘው ምላሽ ያመለክታል ። ስለ ዚሁ በዘመነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል የሚያዳብሩ በርካታ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ከተማሪው ፍላጐት አንፃር ተመርጠው ለተማሪዎቹ የሚያስፈልጓቸውን የማዳመጥን አጠቃላይና ንዑሳን ክሂሎች በግልጽና በዝርዝር ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል ።

...// 85

## 5.2:- ጥቆማ፤

በዚህ በዘመነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር በቀረቡ ይዘቶች ላይ በተደረገ ጥናት በተገኘው ውጤት መሠረት የሚከተሉት የጥቆማ ነጥቦች ቀርበዋል ፡፡ ፡-

1. የማዳመጥን ክሂል መቶ ፐርሰንት ማዳረስ ባይቻልም በማስተማር ክሂሉን ለተፈለገው አላማ ማዳበር እንደሚቻልና ይህም ደግሞ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማዳመጥንም የሚመለከት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ፡፡
2. የማዳመጥ ክሂል በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውን ላይ ከሌሎቹ ክሂሎች ጋር ተዋህዶ ቢገኝም በአላማና በይዘት ምርጫ ደረጃ ግን በተናጠል ቢቀርብ ክሂሉን ትኩረት ሰጥቶ ለማዳበር ያስችላል ፡፡
3. ይዘቶቹ ሲጻፉ ሊዳብር የተፈለገውን ክሂል ገላጭ በሆነ መንገድ የሚያሳዩ ሆነው መጻፍ አለባቸው ፡፡ ትርጓሜቸው አሻሚ በሆነ መንገድ ከተጻፉ ከተፈለገው ግብ ማድረሳቸው አጠራጣሪ ነው ፡፡
4. ለዘመነኛ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥን ክሂል የሚያዳብሩ በርካታ ይዘቶች ሊቀርቡላቸው ይገባል ፡፡ ከፍላጎት አሰሳው የተገኘው ውጤት ይህንኑ ያመለክታል ፡፡
5. የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ከመመረጣቸው በፊት የተማሪዎችን ፍላጎት ማጥናት አስፈላጊ ነው ፡፡ ይህንንም ተማሪዎችን፤ መምህራንና የመርሀ ትምህርት አዘጋጆችን መጠይቆችን በማስሞላት ማከናወን ይቻላል ፡፡ ማንኛውም ትምህርት በአንድ አይነት ፍላጎት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የፍላጎት አሰሳ የማድረጉ አስፈላጊነት አጠያያቂ አይደለም ፡፡
6. የመርሀ ትምህርት አዘጋጆች ከተማሪዉና ከቋንቋ መምህራን ጋር በመተባበርና በመቀራረብ መሥራት አለባቸው ፡፡ የትምህርቱን ይዘት በተመለከተ በየጊዜው ከመምህራንም ሆነ ከተማሪዎች አስተያየት መሰብሰብ ተገቢውን ይዘት ለመምረጥ ይረዳል ፡፡
7. መርሀ ትምህርት በየጊዜው ለግምገማ መቅረብና የግምገማ ሃሳቦችን ሰብስቦና በየጊዜው የሚፈልቁ አዳዲስ የቋንቋና ቋንቋን የማስተማር ቲዮሪዎችን ተንተርሶ መሻሻልና መለወጥ የሚችል ሆኖ መቅረብ አለበት ፡፡

## የዋቢ መጻሕፍት ዝርዝር


Allen, J.P.B., 1984. "General Purpose language Teaching : A Variable focus Approach", General English Syllabus Design. ELT Documents 118. C.J. Brumfit (edt). Oxford : pergomon press Ltd. (pp.61-74.)

Anderson, A., and Tony L. 1988. Listening. Oxford: Oxford University Press.

Bhatia, Aban Tavadia. 1986. "Communicative Language Skills and ESP" ESP in Practices. Models and challenges for teachers. Peterson, pat Wilcox (edt.) English Language programs Division Bureau of Educational and Cultural Affairs United States Information Agency Washington, D.C. (pp. 10-15).

Borg, Walter R., and M. D, Gall. 1989. Educational Research: An Introduction. London: Longman Group UK Limited.

Brown, G., and J.Yule. 1983 Teaching the Spoken Language. Cambridge: Cambridge University Press.

Byrne, Donn. 1986. Teaching Oral English. London: Longman Group UK. Limited.

Dubin, Fraida and Elite Olshtain. 1986. Course Design: Developing Programs and Materials for Language Learning. Cambridge: Cambridge University Press.

Harmer, Jeremy. 1983 The Practice of English Language Teaching. London; Longman Group UK Limited.

Hutchinson, Tom, and Alan Waters. 1987 English for Specific Purpose: A Learning Centered Approach. Cambridge; Cambridge University Press.

Lewis, Michael and Jimmie Hill. 1986. Practical Techniques for Language Teaching. London: Biddles Ltd.

Littlewood, William. 1981. Communicative Language Techniques for Language Teaching. London: Biddles Ltd.

Munby, John. 1978. Communicative Syllabus Design. Cambridge: Cambridge University Press.

Richards, J.C. 1990. The Language Teaching Matrix Cambridge: Cambridge University Press.

Rixon, Shelagh. 1986 Developing Listening Skills. London: Mac millan Publishers Ltd.

Rost, Michael. 1990. Listening in Language Teaching. London: Longman Group UK Limited.

Stern, H.H. 1984 " Review and Discussion " General English Syllabus Design. ELT Documents 118. C.J. Brumfit (edt). Oxford: Pergamon Press Ltd. (pp. 5 - 12 ).

Tarone, Elanie, and George Yule. 1989. Focus on The Language Learner. Oxford University Press.

Tesfaye Shewaye, and Charles V. Taylor. 1976. " Language Curricula ", Language in Ethioia M.L. Bender, and others ( edts.) London: Oxford University Press. (pp. 371-399).

Tyler, Ralph. W. 1949. Basic Principles of Curriculum and Instruction. Chicago" The University of Chicago Press.

Underwood, Mary. 1989. Teaching Listening. London: Longman Group UK Limited.

Ur, Penny. 1984. Teaching Listening Comprehension. Cambridge: Cambridge University Press.

White, R.V. 1988. The ELT Curriculum. Cambridge: Basil Blackwell Inc.

Widdowwon, H.G. 1990. Aspects of Language Teaching. Oxford: Oxford University Press.

Yalden, Janice. 1987. Principles of Course Design for Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

ሰለሞን ደስታ፣ 1976፣ በአዲስ አበባ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ1975 ዓ/ም የተሰጡ የአማርኛ ፈተናዎች ግምገማ:: ለቢኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ::

ሰለሞን ገዛኸው ፤ 1978፤ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍት ግምገማ / ከ1966–1976/፤ ለቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ::

በስርአተ ትምህርት ሱፐርቪዥን መምሪያ የአማርኛ ትምህርት ቡድን፣ የአማርኛ ቋንቋ ስርአተ ትምህርት /ከ1–8 ክፍል / ፣ የተባዘ/ ::

ተሰፋዬ ሽዋዬ፣ 1982 ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማርኛን የማስተማሪያ አላማዎች ትንተና፣ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት ሲምፖዚየም የቀረበ :: / የተባዘ/ ::

ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1984 ፤ የአማርኛ መማሪያ ዘጠነኛ ክፍል ፣ ትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ::

_______________ ፣ 1984 ፤ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰው፣ ዘጠነኛ ክፍል፣ ትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ::

ይልማ ከበደና አሸቱ ከበደ ፤1982 ፣ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ስርአተ ትምህርት የአሁኑና ወደፊት መሆን የሚገባው፣ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት ሲምፖዚየም የቀረበ :: / የተባዘ/ ::

ደመቀ ብርሃነ ፤ 1973 ፤ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተናና የስርአተ ትምህርት/ ከ1969 – 1972 / ፣ ለቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፣ ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍል ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ::

ፈቃደ አዘዘ ፣ 1982 ፣ አንዳንድ ነጥቦች ስለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋ ትምህርት አላማዎች፣ ስለስርአተ ትምህርቶች፣ ስለመማሪያ መጽሀፍት እና ስለ ሥነጽሁፍ ሚና በቋንቋ ትምህርት /1940 – 1982 / ፣ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት ሲምፖ ዚየም የቀረበ :: / የተባዘ ::

# አ ባ ሪ ዎ ች

አባሪ 1

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት/ሲለበስ/ ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶችን ለመገምገምና ለመተንተን የተዘጋጀ መጠይቅ::

### የተማሪው መጠይቅ

**መግቢያ፣**

የዚህ መጠይቅ አላማ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶችን ተገቢነትና ብቃት ለመመርመር ለሚደረገው ጥናት የሚያገዝ መረጃ መሰብሰብ ነው::ጥናቱ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘትን በመምረጥና በመወሰን ሂደት ሊከተሏቸው የሚገቡ ደረጃዎችንና ሊዙርቧቸው የሚገቡ ነጥቦችን በማመልከት ረገድ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ይገመታል::

ይህ አላማ ከግቡ ሊደርስ የሚችለው የጉዳዩ ባለቤት የሆኑት ተማሪዎች በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጪ በሥራ መስክና በኅብረተሰቡ ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ምን ያህል እንደሚጠቀሙና በቋንቋው ያላቸውን የማዳመጥ ችሎታ በመግለጽ በዚህ ጥናት ሲሳተፉ ነው:: ስለዚህ አንተም በዚህ መጠይቅ ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና ካነበብህ በኋላ የምትስማማበትን መልስ በመስጠት እንድትተባበር እንጠይቃለ:: ስለትብብርህ በቅድሚያ እናመሰግናለን::

**ማስታወሻ፣**

- በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አስፈላጊ አይደለም
- የቀረቡት ጥያቄዎች በሙሉ በአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀምና ችሎታ ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን ተገንዝበህ የምትሰጣቸው መልሶችም የአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀምህን በትክክል የሚያሳዩ መሆን እንደሚገባቸው አስተውል::
- በተባእት ጾታ መጠቀሙ የተለመደ በመሆኑና በመጠይቁ ላይ የሚያመጣው ለውጥ እንደሌለ በማመን፣ በሁለቱም ጾታዎች ለመግለጽ ወቀከሩ ለተየበ እንዳያስቸ ገር በማለት ጥያቄዎቹ በተባእት ጾታ ብቻ ቀርበዋል::

1. **ግላዊ መረጃ**

የትምህርት ቤት ስም ____________________

የአፍ መፍቻ ቋንቋህ ____________________

ከአፍ መፍቻ ቋንቋህ ሌላ የምትችላቸው ቋንቋዎች __________

__________

ጾታ:- ወንድ [ ] ሴት [ ]

ዕድሜ:- 13 ዓመት ወይም በታች [ ]

ከ14- 16 ዓመት [ ]

ከ17-19 ዓመት [ ]

20 ዓመት ወይም በላይ [ ]

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ቸቸ ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ምርጫ ካሏቸው ከተሰጡት ምርጫዎች የምትስማማበትንመልስ የያዘው ፊደል ወይም ቁጥር በመክበብ ወይም ተስማሚውን ቁጥር በመጻፍ መልስ :: ምርጫ ለሌላቸው ጥያቄዎች ደግሞ በተወሰኑ አረፍተ ነገሮች መልስህን በመጻፍ መልስ::

1. የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች አማርኛ የምትማርበትን አላማህን የሚገልጹትን ደረጃ አመልከት:-

5 = በጣም ከፍተኛ
4 = ከፍተኛ
3 = መካከለኛ
2 = ዝቅተኛ
1 = በጣም ዝቅተኛ
0 = በፍጹም አይገልጽም

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1.1. በቋንቋው ሌሎች ትምህርቶችንመማር | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.2. በቋንቋው የመናገር ችሎታዬን ማዳበር | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.3. በቋንቋው የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ጉዳዮችን አዳምጦ የመረዳት ችሎታዬን ማዳበር | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.4. በቋንቋው የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ጽሁፎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማዳበር | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.5. ልዩ ልዩ ዓይነት ጽሁፎችን የመጻፍ ችሎታን ማዳበር | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.6. ቋንቋውን መማር ግዴታ ስለሆነ ብቻ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.7. ፈተና ለማለፍ ስለ ብቻ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

2. የሚከተሉትን የማዳመጥ ተግባራት ምን ያህል ታዘወትራለህ?

4 = ሁሉጊዜ
3 = ብዙ ጊዜ
2 = በመጠኑ
1 = አንዳንድ ጊዜ
0 = በፍጹም

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1. | በሬዲዮና በቴሌቭዥን የሚተላለፍ ፕሮግራሞችን ማዳመጥ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 2.2. | በክፍል ውስጥ መምህሩ የሚናገሯቸውን የፈተናዎችን ወይም የመልመጃዎችን የአሠራር መመሪያዎች ማዳመጥ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 2.3. | በአማርኛ ቋንቋ የሚሰጡ የሌሎች ትምህርቶችን ገለጻ ማዳመጥ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 2.4. | በስልክ የሚተላለፍ መልእክትን ማዳመጥ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 2.5. | ውይይቶችን ማዳመጥ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 2.6. | የሌሎችን ጭውውት ማዳመጥ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 2.7. | በድምፅ ማጉያ የሚነገሩ ማስታወቂያዎችን ማዳመጥ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 2.8. | በቃል የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ማዳመጥ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |

3. በክፍል ውስጥ የምታዳምጠው ጉዳይ አንዴት ቢቀርብልህ ትመርጣለህ?

ሀ. መምህሩ ቢያነቡት ወይም ቢናገሩት
ለ. ከተማሪዎች አንዱ ቢያነበው ወይም ቢናገረው
ሐ. በካሴት ተቀድቶ ቢቀርብ

4. የሚከተሉት የሌሎችን ንግግር በምታዳምጥበት ጊዜ ሃሳባቸውን በቀላሉ እንዳትረዳ የሚያደርጉ ችግሮች ናቸው ተብሎ ይገመታል:: ላንተ ችግር የሚሆኑበት ደረጃ ምን ያህል ነው?

5 = በጣም ከፍተኛ
4 = ከፍተኛ
3 = መካከለኛ
2 = ዝቅተኛ
1 = በጣም ዝቅተኛ

4.1. የንግግሩን ይዘት/የመስማማት፣የጥያቄ፣ የቁጣ፣ የትዕዛዝ፣ ወዘተ. መሆኑን/ ለይቶ አለማወቅ 5 4 3 2 1

4.2. በቋንቋው ውስጥ የሚሸሹና የሚጠበቁ ይዘቶችን ለይቶ አለማወቅ 5 4 3 2 1

4.3. የቋንቋውን ባለቤቶች ባህል አለማወቅ 5 4 3 2 1

4.4. የተናጋሪውን ስሜት አለመረዳት 5 4 3 2 1

4.5. ፍሬ ነገሩን ለይቶ ማዳመጥ አለመቻል 55 4 3 2 1

5. በትምህርት ቤትም ሆነ በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚነገረውን ለማዳመጥ የሚከተሉት የቋንቋ ችሎታዎች ለአንተ አስፈላጊ የሚሆኑበት ደረጃ ምን ያህል ነው?

5 = በጣም ከፍተኛ
4 = ከፍተኛ
3 = መካከለኛ
2 = ዝቅተኛ
1 = በጣም ዝቅተኛ

5.1. የቃላትን ቀጥተኛ ትርጉም ማወቅ 5 4 3 2 1

5.2. የቃላትን፣ የሀረጋትና የአረፍተ ነገርን ትርጉም ከአገባብ መረዳት 5 4 3 2 1

5.3. በግልጽ ያልተነገሩ መረጃዎችን ከአነጋገሩ መረዳት 5 4 3 2 1

5.4. የውይይት ስርአት ማወቅ 5 4 3 2 1

5.5. የክርክር ስርአት ማወቅ 5 4 3 2 1

5.6. የጭውውት ስርአት ማወቅ 5 4 3 2 1

5.7. ምስጢራዊ አነጋገሮች መገንዘብ፣ መተርጎምና በነርሱም መገልገል/ምሣሌ:- ቅኔ፣ዘይቤ፣ወዘተ/ 5 4 3 2 1

5.8. የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነትን ማወቅ 5 4 3 2 1

5.9. የሚያስፈልጉና የማያስፈልጉ ዝርዝር ሃሳቦችን መለየት 5 4 3 2 1

5.10. በጭብጥና በስሜታዊ አስተያየት መሀከል ያለውን ልዩነት ማወቅ 5 4 3 2 1

5.11. ፍሬ ሃሳቦችን በማስታወሻ መያዝ 5 4 3 2 1

5.12. አንዱን ርዕስ ጉዳይ አዳምጦ በራስ አባባል ማቅረብ 5 4 3 2 1

6. ከምታዳምጠው ውስጥ ምን ያህሉን በእርግጠኛነት ታዳምጣለህ?

ሀ. ከ20% በታች　　　ለ. ከ21–40%
ሐ. ከ41–60%　　　መ. ከ61–80%
ሠ. ከ80% በላይ

7. በአማርኛ ቋንቋ በምትጠቀምበት ጊዜ በሚከተሉት ክሂሎች ችሎታህ የቱን ያህል ነው?

5= በጣም ከፍተኛ
4= ከፍተኛ
3= መካከለኛ
2= ዝቅተኛ
1= በጣም ዝቅተኛ

7.1. በተለያዩ ሰዎች ስለተለያዩ ጉዳይ የሚደረጉ ንግግሮችን አዳምጦ መረዳት　5 4 3 2 1
7.2. በተለያዩ ርዕሶች ላይ ሃሳብ አሰባስቦ ንግግር ማድረግ　5 4 3 2 1
7.3. በተለያዩ ርዕሶች ለተለያዩ አላማ የተጻፉትን አንብቦ መረዳት　5 4 3 2 1
7.4. በተለያዩ ርዕሶች የድርሰት አጻጻፍ ስርአትን ተከትሎ መጻፍ　5 4 3 2 1

8. በአማርኛ ቋንቋ በምትጠቀምበት ጊዜ የሚከተሉት ክሂሎች ለአንተ ጠቀሜታቸው ምን ያህል ነው?

5 = በጣም ከፍተኛ
4 = ከፍተኛ
3 = መካከለኛ
2 = ዝቅተኛ
1 = በጣም ዝቅተኛ
0 = ምንም

8.1 ማዳመጥ　5 4 3 2 1
8.2 መናገር　5 4 3 2 1
8.3 ማንበብ　5 4 3 2 1
8.4 መጻፍ　5 4 3 2 1

9. አሁን ክፍል ከምትማራቸው የትምህርት ዓይነቶች የማስተማሪያ ቋንቋቸው አማርኛ የሆኑ ትምህርቶች ስንት ናቸው? ____

10. በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ማዳመጥ የምትፈልገው የምንባብ ወይም የንግግር ርዕስ ስለምን የሚናገር ቢሆን ይሻላል? የምርጫ ደረጃህን አመልክት

5 = በጣም ከፍተኛ
4 = ከፍተኛ
3 = መካከለኛ
2 = ዝቅተኛ
1 = በጣም ዝቅተኛ

| | | |
|---|---|---|
| 10.1 | ስለሀገር | 5 4 3 2 1 |
| 10.2 | ስለ ትምህርት | 5 4 3 2 1 |
| 10.3 | ስለ ፍቅር | 5 4 3 2 1 |
| 10.4 | ስለ ጀግንነት | 5 4 3 2 1 |
| 10.5 | ስለ ጤና | 5 4 3 2 1 |
| 10.6 | ሣይንስ ነክ | 5 4 3 2 1 |
| 10.7 | ስለ ፖለቲካ | 5 4 3 2 1 |
| 10.8 | ስለ ሃይማኖት | 5 4 3 2 1 |
| 10.9 | ስለ ቤተሰብ | 5 4 3 2 1 |

10.10 ሌሎች እዚህ ያልተጠቀሱ ካሉ ግለጽ:- ______________________

______________________________________________

11. ከዚህ በታች የማዳመጥ ችሎታን የሚያመለክቱ አረፍተ ነገሮች ቀርበዋል:: ከተሰጡት አምስት የችሎታ ደረጃዎች የአንተን ችሎታ የሚገልጸውን የአንዱን ቁጥር በመክበብ ችሎታህን አመልክት:: ጥያቄዎቹ ፈተና ስላልሆኑ ችሎታህን በትክክል ለመግለጽ ሞክር::

5 = በጣም ከፍተኛ
4 = ከፍተኛ
3 = መካከለኛ
2 = ዝቅተኛ
1 = በጣም ዝቅተኛ

| | | |
|---|---|---|
| 11.1 | የማታውቃቸውን ቃላትና ሀረጎች ትርጉም ከአገባባቸው የመረዳት ችሎታ | 5 4 3 2 1 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 11.2. በቃል የሚነገሩህን መመሪያዎች በቀላሉ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.3. በንባብ ወይም በንግግር ቀርቦ ከምታዳምጠው ውስጥ ዋናውንና ዝርዝር ሃሳቡን ለይተህ የመረዳት ችሎታ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.4. በተለያዩ ሰዋስዋዊ ቀንበር የሚቀርብልህን ሃሳብ አዳምጠህ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.5. በመደበኛና በኢመደበኛ ንግግር መካከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.6. በግራፍ፣ በሠንጠረዥ ወይም በካርታ የተደገፉ መረጃዎችን አዳምጦ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.7. ከምታዳምጠው ውስጥ ምክንያትንና ውጤትን ለይተህ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.8. የንግግር ቋንቋን ባህሪ ማወቅ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.9. የንግግሩን ድምጸት/የጥያቄ፣ የመገረም የመስማማት፣ የመቃወም፣ወዘተ መሆኑን/ አዳምጠህ መለየት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.10. የምታዳምጠውን ነገር አስቀድሞ ከምታውቀው ነገር ጋር ማገናዘብ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.11. በግልጽ የተነገሩ መረጃዎችን አዳምጠህ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.12. በንግግር ውስጥ በግልጽ ያልተነገሩ መረጃዎችን ከአነጋገሩ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.13. በንግግር ውስጥ ተናጋሪው የሚያተኩርባቸውን ነጥቦችና የንግግሩን አላማ ለይተህ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.14. ተናጋሪው በንግግሩ ወቅት ሃሳብ ለማስተዋወቅ ሃሳብ ለማዳበር፣ ከአንዱ ሃሳብ ወደሌላ ሃሳብ ለመሸጋገርና ሃሳቡን ለማጠቃለል የሚጠቀምባቸውን ነጥቦች ለይተህ መገንዘብ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.15. ከሚነገረው ውስጥ ጠቃሚውን መረጃ ለይተህ ማዳመጥ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

11.16. ከምታዳምጠው ውስጥ የማይጠቅሙ መረጃዎችንና
ድግግሞሽን በመለየት አሳጥረህ ማቅረብ 5 4 3 2 1

11.17. በንግግር የቀረበለህን መረጃ ወደ ግራፍ፣
ሠንጠረዥ ወይም ካርታ መተርጎም 5 4 3 2 1

11.18. ያዳመጥከውን በራስህ አባባል ማቅረብ 5 4 3 2 1

11.19. በምታዳምጠው ተከታታይ ንግግር ወይም
ምንባብ ውስጥ ወደፊት የሚነገረውን አስ
ቀድመህ የመገመት ችሎታ 5 4 3 2 1

11.20. ከምታዳምጠው ውስጥ ፍሬ ሃሳቡን በማስ
ታወሻ የመያዝ ችሎታ 5 4 3 2 1

..

አባሪ ፩

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
## የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መረሀ ትምህርት/ሲለበስ/ ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶችን ለመገምገምና ለመተንተን የተዘጋጀ መጠይቅ::

### የመምህሩ መጠይቅ

**መግቢያ**

የዚህ መጠይቅ አላማ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መረሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶችን ተገቢነትና ብቃት ለመመርመር ለሚደረገው ጥናት የሚያገዝ መረጃ መሰብሰብ ነው:: ጥናቱ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘትን በመምረጥና በመወሰን ሂደት ሊከተሏቸው የሚገቡ ደረጃዎችንና ሊተኩሩባቸው የሚገቡ ነጥቦችን በማመላከት ረገድ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ይገመታል::

የጥናቱ አላማ ግቡን ሊመታ የሚችለው የቋንቋው መምህራን በክፍል ውስጥ ቋንቋን በማስተማር ተግባር ላይ እያሉ በኀብረተሰቡ ውስጥ ያስተዋሏቸውን የተማሪዎቻቸውን የቋንቋ ፍላጎትና/ / ችሎታ በመግለጽና ከሙያቸው አንጻር የትምህርቱ ይዘት ምን መልክ ሊኖረው እንደሚገባ ሃሳባቸውን በመሰንዘር ቀና ትብብር ሲያደርጉ እንደሆነ ይታመናል::

ስለዚህ እርስዎም በዚህ መጠይቅ ላይ የሚሰነዝሩት አስተያየትና ለጥያቄዎቹ የሚሰጡት ምላሽ ለጥናቱ መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው በመገንዘብ መጠይቁን በመሙላት እንዲተባበሩ በትህትና እንጠይቃለን:: ስለትብብርዎ በቅድሚያ እናመሰግናለን::

**፩. ዳራዊ መረጃ**

የሚያስተምሩበት ት/ቤት ______________ ፣ የሚያስተምሩባቸው ክፍሎች ____
አፍ መፍቻ ቋንቋ ________________ ፣ ዕድሜ ____ ፣ ጾታ ________
የትምህርት ደረጃ ____________ ፣ በ9ኛ ክፍል አማርኛን በማስተማር ስንት
ዓመት ሰርተዋል ______________

II. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ምርጫ ላላቸው ከተሰጡት ምርጫዎች የሚስማሙ በትን መልስ የያዘውን ፊደል ወይም ቁጥር በመክበብ፣ ወይም በተሰማሚ ቁጥር በማመልከት ይመልሱ፤ ምርጫ ለሌላቸው ጥያቄዎች ደግሞ በተወሰኑ አረፍተ ነገ ሮች መልስዎን ይግለጹ::

1. በዘጠነኛ ክፍል ከሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ውስጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማ ርኛ ባለመሆኑ ምክንያት የተለየ የአማርኛ ቋንቋ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አጋጥሞዎታል?

   ሀ. አጋጥሞኛል ለ. አላጋጠመኝም

2. ለጥያቄ '1' መልስዎ አጋጥሞኛል ከሆነ የችግሩን ዓይነት ይግለጹ

   ________________________________________

3. ተማሪዎችዎ የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጾች/ለምሳሌ የጋብቻ፣ የወሊድ፣ የደስታ፣ የሀዘን፣ የበአላት፣ የዝምድና፣ ወዘተ ... ሁኔታዎች የሚገለጹባቸውን / በትክክል ይረዳሉ::

   ሀ. በሚገባ ይረዳሉ ለ. በመካከለኛ ደረጃ ይረዳሉ ሐ. በዝቅተኛ ደረጃ ይረዳሉ መ. በጭራሽ አይረዱም ሠ. አስተያየት የለኝም

4. ለዚህ ክፍል ተማሪዎች የበለጠ ትኩረት ሰጥተው የሚያስተምሩት ክሂል የትኛው ነው? 1ኛ ፣ 2ኛ ፣ 3ኛ ፣ 4ኛ እያሉ በደረጃ ያመልክቱ

   ___ የማዳመጥ ክሂል
   ___ የመናገር ክሂል
   ___ የማንበብ ክሂል
   ___ የመጻፍ ክሂል

5. በጥያቄ '4' ለማዳመጥ ክሂል የሰጡትን የትኩረት ደረጃ አስመልክቶ ምክንያቱን ቢገልጹ ________________________________________

   ________________________________________

6. የሚከተሉት የቋንቋ ትምህርት ዝርዝር አላማዎች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር የተነደፉ ናቸው:: በእርስዎ አመለካከት እነዚህ ዝርዝር አላማዎች የተማሪዎችዎን ፍላጎትና ችሎታ ምን ያህል ያሟላሉ?

   5 = በጣም ከፍተኛ ደረጃ
   4 = በከፍተኛ ደረጃ
   3 = በአማካይ ደረጃ
   2 = በዝቅተኛ ደረጃ
   1 = በጣም በዝቅተኛ ደረጃ

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6.1 | የቃላት ቶሉ፡ቻውን ማዳበር | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.2 | ተጠያቂ አስተሳሰብን ማዳበር | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.3 | የተወሰነን ሃሣብ በራስ አባባል የማቅረብ ዘዴን ማዳበር | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

7. እርስዎ ለዚህ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂሎቻቸውን ለማዳበር ምን ምን ስል ማዎችን ይነድፋሉ:- ______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

8. የሚከተሉት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የተመረጡ ናቸው በእርስዎ አመለካከት እነዚህ ይዘቶች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል የማዳበር ብቃታቸው ምን ያህል ነው?

5 = በጣም ከፍተኛ
4 = ከፍተኛ
3 = መካከለኛ
2 = ዝቅተኛ
1 = በጣም ዝቅተኛ

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8.1 | የቃላት ቀጥታ ትርጉም | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8.2 | የቃላትን፣ የሀረጋትና የአረፍተ ነገርን ትርጉም በአገባብ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8.3 | በግልጽ ያልተነገሩ መረጃዎችን ከአነጋገሩ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8.4 | የውይይት ስርዓት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8.5 | የጭውውት ስርአት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8.6 | የክርክር ስርዓት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8.7 | ምስጢራዊ አነጋገሮችን መገንዘብ፣ መተርጎምና በነርሱም መገልገል/ቅኔ፣ዘይቤ የቋንቋ ሥነውበት/ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8.8 | የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8.9 | የሚያስፈልጉና የማያስፈልጉ ዝርዝር ሃሣቦችን መለየት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

8.10 በጭብጥና በስሜታዊ አስተያየት መካከል ያለው ልዩነት

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 8.11 ፍሬ ሃሳቦችን በማስታወሻ መያዝ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8.12 አንድን ርዕስ ጉዳይ በራስ አባባል ማቅረብ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

8.13 ሌሎች እዚህ ያልተጠቀሱና አርስዎ የተማሪ ዎችዎን ፍላጎት ያሟላሉ ብለው የሚያምኑባቸው የማዳመጥን ክሂል የሚያዳብሩ ይዘቶች ካሉ አባክዎ ይግለጹ:- ____________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

9. የዚህ ክፍል ተማሪዎች ቀጥሎ ባቀረቡት የማዳመጥ ክሂሎች ምን ያህል ችሎታ አላቸው?

5 = በጣም ከፍተኛ
4 = ከፍተኛ
3 = መካከለኛ
2 = ዝቅተኛ
1 = በጣም ዝቅተኛ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 9.1 የማያውቋቸውን ቃላትና ሀረጋት ትርጉም ከአገባባቸው መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9.2 በቃል የሚነገሯቸውን መመሪያዎች በቀላሉ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9.3 በንባብ ወይም በንግግር ቀርቦላቸው ከሚያዳምጡት ውስጥ ዋናውንና ዝርዝር ሃሳቡን ለይተው መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9.4 በተለያየ ስዋስዋዊ ቅንብር የሚቀርብላቸውን ሃሳብ አዳምጠው መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9.5 በመደበኛና በኢመደበኛ ንግግር መካከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9.6 በግራፍ፣በሰንጠረዥ ወይም በካርታ የተደገፈ መረጃዎችን አዳምጠው መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9.7 ከሚያዳምጡት ውስጥ ምክንያትና ውጤትን መለየት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9.8 የንግግር ድንድን ባህሪ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9.9 የንግግሩን ድምጸት አዳምጠው መለየት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9.10 የሚያዳምጡትን ነገር አስቀድሞ ካላቸው ዕውቀት ጋር ማገናዘብ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9.11 በግልጽ የተነገሩ መረጃዎችን አዳምጠው መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

9.12 በንግግር ውስጥ በግልጽ ያልተነገሩ መረጃዎችን ከአነጋገሩ መረዳት 5 4 3 2 1

9.13 በንግግር ውስጥ ተናጋሪው የሚያተኩርባቸውን ነጥቦችና የንግግሩን አላማ መረዳት 5 4 3 2 1

9.14 ተናጋሪው በንግግሩ ወቅት ሃሳብ ለማስተዋወቅ፣ ሃሳብ ለማዳበር፣ ከአንዱ ሃሳብ ወደ ሌላ ሃሳብ ለመሸጋገርና ሃሳቡን ለማጠቃለል የሚጠቀምባቸውን ነጥቦች መለየት 5 4 3 2 1

9.15 ከሚነገረው ውስጥ ጠቃሚውን መረጃ ለይቶ ማዳመጥ 5 4 3 2 1

9.16 ከሚያዳምጡት ውስጥ የማይጠቅሙ መረጃዎችንና ድግግሞሽን መለየት አሳጥረው ማቅረብ 5 4 3 2 1

9.17 በንግግር የቀረበላቸውን መረጃ አዳምጠው ወደ ግራፍ፣ሠንጠረዥ ወይም ካርታ መተርጎም 5 4 3 2 1

9.18 ያዳመጡትን በራሳቸው አባባል ማቅረብ 5 4 3 2 1

9.19 በሚያዳምጡት ተከታታይ ንግግር ወይም ምንባብ ውስጥ ወደፊት የሚነገረውን አስቀድሞ መገመት 5 4 3 2 1

9.20 ከሚያዳምጡት ውስጥ ፍሬ ሃሳቡን ለይቶ ማስታወሻ መያዝ 5 4 3 2 1

9.21 እዚህ ያልተጠቀሱ የተማሪዎችዎን የማዳመጥ ችሎታ የሚያሳዩ መረጃዎች ካሉ እባክዎ ይግለጹ:— ____________________

____________________

____________________

____________________

10. በአጠቃላይ ተማሪዎችዎ እንዲያዳምጡ ከሚቀርብላቸው ውስጥ ምን ያህሉን አዳምጠው ይረዳሉ?

ሀ. ከ20% በታች ለ. ከ21–40% ሐ. ከ41–60%
መ. ከ61–80% ሠ. ከ80% በላይ

11. ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂሎቹን ማዳበራቸው በዚህ ክፍል የሚሰጡ ትምህርቶችን ለመከታተል የሚሰጠው ጥቅም ምን ያህል ነው?

5 = በጣም ከፍተኛ
4 = ከፍተኛ
3 = መካከለኛ
2 = [illegible]
1 = በጣም ዝቅተኛ
0 = ምንም ጥቅም አይሰጥም

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 11.1 | አማርኛ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.2 | እንግሊዝኛ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.3 | ሒሳብ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.4 | ባዮሎጂ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.5 | ፊዚክስ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.6 | ኬሚስትሪ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.7 | ታሪክ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.8 | ጂኦግራፊ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.9 | አርት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.10 | ባልትና/የኳ ዘዴ/ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.11 | የምርት ቴክኖሎጂ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.12 | እስፖርት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |

12. በ1984 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በአሁኑ ጊዜ እየተሰራበት ባለው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት በቀረቡት ይዘቶች ላይ ያለዎትን አጠቃላይ አስተያየት ቢገልጹ:- ____________________

____________________

____________________

____________________

አባሪ 3 — አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድሀረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት /ሲለበስ/ ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶችን ለመገምገምና ለመተንተን የተዘጋጀ መጠይቅ::

## የመርሀ ትምህርት ባለሙያዎች መጠይቅ

**መግቢያ፤**

የዚህ መጠይቅ አላማ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ የተማሪውን የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር የሚቀርብለትን የትምህርት ይዘት በተመለከተ በመርሀ ትምህርት ውስጥ የቀረቡት የትምህርት ይዘቶች በተማሪው የቋንቋ ፍላጎትና ችሎታ ላይ ተመስርተው የተመረጡ መሆን አለመሆናቸውንና ብቃታቸውን ለመፈተሽ ለሚደረገው ጥናት መረጃ መሰብሰብ ነው::

አላማው ግቡን ሊመታ የሚችለው ስርአተ ትምህርትና መርሀ ትምህርት በመንደፍ፣ የማስተማሪያ መጽሀፍትን በማዘጋጀትና በማስተማር ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች የቋንቋውን ትምህርት ይዘት በተመለከተ አስተያየታቸውን በመሰንዘር ቀና ትብብር ሲያደርጉ እንደሆነ ይታመናል:: በዚህም መሠረት እርስዎም በዚህ መጠይቅ ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሽ ለጥናቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው በመገንዘብ መጠይቁን በመሙላት እንዲተባበሩ በትህትና እንጠይቃለን:: ስለ ትብብርዎ በቅድሚያ እናመሰግናለን::

I. **ግላዊ መረጃ**

አፍ መፍቻ ቋንቋ ____________ የሥራ መደብ ____________

የትምህርት ደረጃ ____________ ሌላ ሥልጠና ____________

አሁን ባለበት የሥራ መስክ ስንት ዓመት ሰርተዋል ____________

II. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት ምርጫዎች የሚስማማዎትን መልስ የያዘውን ፊደል ወይም ቁጥር በመክበብ ይመልሱ:: መልስዎ ከቀረቡት ምርጫዎች የተለየ ከሆነ በተተወው ክፍት ቦታ ላይ በተወሰኑ አረፍተ ነገሮች መልስዎን ይግለጹ::

1. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚሰጠው:-

ሀ. በአፍ መፍቻ ቋንቋነት ነው::

ለ. በሁለተኛ ቋንቋነት ነው::

ሐ. የተለየ መልስ ካለዎት ይግለጹ ____________________

____________________________________________

2. ለዘጠነኛ ክፍል የሚሆኑ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሲመረጡ ለተገቢነታቸው በመመዘኛነት የታየው ምንድነው?

    ሀ. የተማሪዎች ፍላጎት
    ለ. የተማሪዎች ችሎታ
    ሐ. ቋንቋው በትምህርት ቤት የሚሰጠው አገልግሎት
    መ. ቋንቋው በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚሰጠው አገልግሎት
    ሠ. የቋንቋው ሥነ ልሣናዊ ባህሪ
    ረ. መልስዎ እዚህ ከተጠቀሱት የተለየ ከሆነ ይግለጹ ____________

    ________________________________________

3. ለዚህ ክፍል የሚሆኑ መርሃ ትምህርትና የመማሪያ መጽሀፍት የሚዘጋጁት በአንድ ቡድን /ፓነል/ ነው?

    ሀ. አዎ                    ለ. አይደለም

4. ለዚህ ክፍል ተማሪዎች በሚቀርበው የቋንቋ ትምህርት ውስጥ በአራቱ የቋንቋ ክሂሎች /ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ፣ መጻፍ/ መሀከል ለማዳመጥ ክሂል ምን ያህል ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ብለው ያምናሉ?

    ሀ. ከአራቱ ክሂሎች መሀከል በአንደኛ ደረጃ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል::
    ለ. ከአራቱ ክሂሎች መሀከል በሁለተኛ ደረጃ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል::
    ሐ. ከአራቱ ክሂሎች መሀከል በሶስተኛ ደረጃ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል::
    መ. ከአራቱ ክሂሎች መሀከል በአራተኛ ደረጃ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል::
    ሠ. የተለየ አስተያየት ካለዎት ይግለጹ ____________

    ________________________________________

5. በጥያቄ "4" ለማዳመጥ ክሂል የሰጡትን የትኩረት ደረጃ አስመልክቶ ምክንያትዎን ቢገልጹ? ____________

________________________________________

________________________________________

6. የሚከተሉት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የተመረጡ ናቸው:: በእርስዎ አመለካከት እነዚህ ይዘቶች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል የማዳበር ብቃታቸው ምን ያህል ነው?

የስምምነትዎን መጠን ከተሰጡት ምርጫዎች የአንዱን ቁጥር በመክበብ ያመልክቱ:—

    5 = በጣም ከፍተኛ
    4 = ከፍተኛ
    3 = መካከለኛ
    2 = ዝቅተኛ
    1 = በጣም ዝቅተኛ

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6.1 | የቃላት ቀጥታ ትርጉም | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.2 | የቃላትን፣ የሀረጎችና የአረፍተ ነገርን ትርጉም ከአገባብ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.3 | በግልጽ ያልተነገሩ መረጃዎችን ከአነጋገሩ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.4 | የውይይት ስርዓት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.5 | የጭውውት ስርዓት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.6 | የክርክር ስርዓት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.7 | ምስጢራዊ አነጋገሮችን መገንዘብ፣ መተርጎምና በነርሱም መገልገል/ቅኔ፣ ዘይቤ፣ የቋንቋ ስነ ውበት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.8 | የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.9 | የሚያስፈልጉና የማያስፈልጉ ዝርዝር ሃሳቦችን መለየት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.10 | በጭብጥና በስሜታዊ አስተያየት መካከል ያለው ልዩነት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.11 | ፍሬ ሃሳቦችን በማስታወሻ መያዝ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.12 | አንድን ርዕሰ ጉዳይ በራስ አባባል መቅረብ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

7\. በዘጠነኛ ክፍል መርሀ ትምህርት ላይ የማዳመጥና ክሂል ለማዳበር የተመረጡ አላማዎችንና ይዘቶችን በተመለከተ የሚሰጡት አስተያየት ካለዎት ይግለጹ

________________________________________

________________________________________

________________________________________

አባሪ 4 የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት አወቃቀር

| የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ አላማ | ዝርዝር አላማ | ይዘት | የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሥራ ክንውን | ግምገማ |
|---|---|---|---|---|
| 1. የማዳመጥና መናገር ክሂሎችን ያዳብራል። | | | | |
| 2. የማንበብ ክሂሉን ያዳብራል። | | | | |
| 3. የመጻፍ ክሂሉን ያዳብራል። | | | | |
| 4. የሥነ ልሣን እውቀትን ያዳብራል። | | | | |
| 5. የስነ ጽሁፍ እውቀትን ያዳብራል። | | | | |

አባሪ 5 **ጥናቱ ያቀረበው የመርሀ ትምህርት ክፍል**

አንደኛ ሴሚስተር

| የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ አላማ | ዝርዝር አላማ | ይዘት | የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሥራ ክንውን | ግ ም ገ ማ |
|---|---|---|---|---|
| የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ያዳብራሉ፡፡ | ተጠያያቂ አስተሳሰብን ያዳብራሉ፡፡ | 15. የውይይት ስርአት | 1. ለውይይት ከመቀረቡበፊት ስለርዕሱ ... ጠቃሚ ሀሳብ ማግኘት ተገቢ መሆኑን ማለማመድ፡፡<br>2. ተማሪዎችን በቡድን መድቦ ... አንዱ ሲወያይ ሌላው አዳምጦ አስተያየት እንዲሰጥ በማድረግ ማለማመድ፡፡<br>3. በውይይት ጊዜ ተራቸውን ጠብቀው እንዲናገሩና እንዲጠይቁ በማድረግ ማለማመድ፡፡<br>4. ... ሀሳቦችን በስዕል፣ በሰንጠረዥ፣ በካርታ በግራፍ፣ ወዘተ ... አስደግፈው ማቀረብ እንዲችሉ ማስተማር፡፡<br>5. የውይይቱን ፍሬ ነገር በውሳኔ ሃሳብ መልክ ... የማሳለፍ ወይም የመጣል ስርአትን እንዲያውቁ ማለማመድ፡፡ | 1. ለውይይት ከመቀረባቸው በፊት መረጃ ሀሳቦችን መሰብሰብ መቻላቸውን ማረጋገጥ ፡፡<br>2. ... ተራቸውን ጠብቀው አስተያየት ... ጥያቄ ... መቻላቸውን መከታተል፡፡<br>3. ሀሳቦችን በልዩ ልዩ መገለጫዎች አስደግፈው ማቀረብ....<br>4. የውሳኔ ሃሳብ የማሳለፍ /የመጣል/ ስርአትን መለመዳቸውን ... |
| | | 16. የክርክር ስርአት፡፡ | 1. ክርክር ለማሸነፍ የተቃዋሚን ደካማ ጎን መረዳት እንደሚያስፈልግ ... ማለማመድ፡፡<br>2. ከክርክር በፊት ... ስለርእሱ ... ነጥቦችን መሰብሰብ እንዳለባቸው ማለማመድ፡፡<br>3. ሲያዳምጡት ክርክር በምክንያት የተደገፉ አስተያየት እንዲሰጡ በማድረግ ማለማመድ፡፡<br>4. የተከራካሪዎች አሸናፊነት የሚወሰነው በሚያቀርቡት ነጥቦች ብዛትና የማስረጃ ጥንካሬ መሆኑን በደረጃው ማለማመድ፡፡<br>5. ... በቡድን መድቦ አንዱን ርዕስ በመደገፍና በመቃወም እንዲከራከሩ በማድረግ ማለማመድ፡፡<br>6. ... ተሰናድተውና ሳይሰናዱ መከራከር፡፡<br>7. ... ተቃዋሚ ክፍል ከሚያቀርበው ሀሳብ መከራከሪያ ነጥቦች ሊገኙ እንደሚችሉ ማስገንዘብ፡፡ | 1. ሲያዳምጡት ክርክር በምክንያት የተደገፈ አስተያየት መስጠት መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡<br>2. በመደገፍ ወይም በመቃወም መከራከር መቻላቸውን ...፡፡<br>3. ... ተሰናድተውና ሳይሰናዱ መከራከር መቻላቸውን ፡፡<br>4. የተቃዋሚ ክፍል ከሚያቀርበው ሀሳብ የመከራከሪያ ነጥቦች ማግኘት መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡ |

| | የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ አላማ | ዝርዝር አላማ | ይዘት | የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሥራ ከንውን | ግ ም ገ ማ |
|---|---|---|---|---|---|
| አንደኛ ሳምንት | | | 17. የጥውውት ስርአት | 1. ከጓመኟቸው ጥውውቶች ... መርጠው ለክፍል ጓደኞቻቸው ማቀረብ።<br>2. ጥውውት በቀልዱና በፌዝ ላይ ብቻ የተወሰነ አለ መሆኑንና ቁም ነገር በሆኑ ሃሳቦች ላይ እንደሚደረግ ማለማመድ። | በሬዲዮና በቴሌቪዥን ፕሮግ ራሞች ከሰሟቸው ጥውውቶች መካከል:—<br>ሀ. ጠቃሚ መስለው የሚታያ ቸውን ለጓደኞቻቸው ማቀረብ ።<br>ለ. ፕሮግራም አቀራቢያቸውን መስለው ማቀረብ መቻላ ቸውን መመልከት። |
| ሁለተኛ ሳምንት | የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ያዳብራሉ። | የተወሰነን ሀሣብ በራስ አባባል የማቀረብ ዘዴን ያዳብራሉ። | 16. የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት | 1. ... በአንዱ ሁኔታ ላይ ውጤት ሆኖ የቀረበ ነገር በሌላ ሁኔታ ላይ መንስኤ ሊሆን እንደ ሚችል በማስረዳት ... ማለማመድ ።<br>2. መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ... ሁኔታዎች ጠቅሶ.. ሊከተሉ የሚችለውን ድርጊትና ውጤቱን እንዲ ገልጹ በማድረግ ማለማመድ።<br>3. ... አንዱ ድርጊት አቅርቦ ... መነሻ ሊሆን የሚችለውን በጽሁፍም ሆነ በንግግር ኢንዲገልጹ በማድረግ ማለማመድ።<br>4. መንስኤ ለድርጊት መፈጠር ምክንያት ሲሆን ከድር ጊት በኋላ ደግሞ ውጤት የሚገኝ መሆኑን በልዩ ልዩ መለመጃዎች ማስተማር።<br>5. ... የመንስኤና የውጤትን ግንኙነትና ልዩነት የሚያስረዱ በማድረግ ማለማመድ።<br>6. የተወሰኑ ርእሶችን መርጦ በሁለት በመክፈል በአንዱ ረድፍ የግማሾችን መነሻ፤ በሌላ ረድፍ የሌሎችን ድርጊቶች ውጤት በመስጠት እያገናኙ ተማሪ በመረጠው ርዕስ አጠር ያለ መግለጫ ጽፎ እንዲያቀርብ በማድረግ ማለማመድ። | 1. ከአንዱ መነሻ ከሆነ ነገር ሊከተሉ የሚችሉትን ድርጊቶችና የድርጊት ውጤ ቶች ተከታትለው መግለጽ መቻላቸውን፤ማየት።<br>2. የመንስኤና የውጤትን ግንኙ ነትና ልዩነት ከሰጧቸው መለመጃ መረዳት መቻላቸውን ማረጋገጥ። |

| የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ አላማ | ዝርዝር አላማ | ይዘት | የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሥራ ክንውን | ግምገማ |
|---|---|---|---|---|
| ሌሎች ክሂሎችን ለማዳበር ተመርጠው እግረ መንገዳቸውን የማዳመጥ ክሂል የሚያዳብሩ ይዘቶች። | | 22. በጭብጥና በስሜታዊ አስተያየት መካከል ያለው ልዩነት<br>23. ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝ<br>24. አንድን ርእስ ጉዳይ በራስ አባባል ማቅረብ። | ቁ. ከሰሙት ንግግር .... ሀቆችንና ስሜታዊ አስተያየቶችን ለየብቻ በመዘርዘር .... ያሳቸውን ምክንያት በዝርዝር እንዲናገሩ በማድረግ ሀቅና ስሜታዊ አስተያየትን መለየት እንዲችሉ ማለማመድ ።<br>1.... ካዳመጡት ያገኙትን ፍሬ ሀሳብ በማስታወሻ እንዲወስዱ ...<br>2. .. ያዳመጡትን ዜና ዋና ሃሳብ በማስታወሻ ይዘው<br>3. ... ውይይቶችን እያዘጋጁ በማቅረብ ሀሳቡን በራሳቸው አባባል አቀነባብረው | |

አባሪ 6 በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተለ ያዩ ክሂሎችን ለማዳበር እንደረዱ ከቀረቡት መምሪያዎች ከማዳመጥ ጋር ግን ኙነት ያላቸው::

## የማዳመጥ መምሪያ

1. ማዳመጥ መልእክት መቀበያ መሆኑን ተገንዘብ::
2. ማንኛውም መልእክት በቃል ሲነገርህ ወይም ሲነበብልህ በጥሞና አዳምጥ
3. አንዱ መልእክት በታዳምጥ ጆሮችህን ብቻ ሰጥተህ ጭጭ አትበል::
4. የሰዎችን ንግግር ስታዳምጥ አታቋርጣቸው:: ማቋረጥ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በስርዓት ይቅርታ በመጠየቅ ያቋረጥክበትን ምክንያት ጠይቅ::
5. ካዳመጥከው ሃሳብ ውስጥ ስህተት የሆነ ነገር ተሰንዝሮ ከሆነ ፊት ለፊት ልክ አይደለም፤ ስህተት ነው፤ ከማለት ይልቅ ስርአት ባለው መንገድ ያለ ተስማማህበትን ሃሳብ ከነምክንያቶቹ በጥሞና ለማስረዳት ሞክር::
6. ለሰዎች ንግግር ተገቢውን ግምት ስጥ እንጂ በንቀት መንፈስ ለማንኳሰስና ለማጥቃቃት አትሞክር::
7. ካዳመጥከው ንግግር ውስጥ ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን ለመለየት ሞክር::
8. ያዳመጥከውን ፍሬ ሃሳብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በጽሁፍ አዘጋጅ::
9. ያዳመጥከውን ፍሬ ሃሳብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባታዛባ ለሌሎች አስተላልፍ / ገጽ 85/

## የማስታወሻ አያያዝ መመሪያ

1. ማስታወሻ የሚያዝባቸው:-
   1.1 በምታዳምጥበት ጊዜ፤
   1.2 ዝግጅት በምታደርግበት ጊዜ፤
   1.3 በግል በምታነብበት ጊዜ ወዘተ ...፤
2. ማስታወሻ ወረቀትና ብእር ወይም እርሳስ ይኑርህ::
3. ዋና ዋና ሃሳቦችን በቃላት፤ በሀረግና በዐ/ነገር ጻፍ::
4. ሁሉን ነገር ሳይሆን ዋና ዋና መረጃዎች ናቸው የምትላቸውን ጻፍ::
5. በዘገባ መልክ እንድትዘጋጅ ከተነገረህ ግልጽ በሆነና ቀደም ተከተሉን ጠብቀህ ባታጋንን፤ ባትጨምርና ባትቀንስ አቅርብ::/ገጽ 87-88/

## የውይይት ዝግጅትና አቀራረብ መምሪያ

ውይይት አላማ ያለው በእቅድ የተዘጋጀና የአንዱን ርእስ ጉዳይ የተለያዩ ገጽታዎችን የሚመለከት ነው::

1. **የውይይት ዝግጅት መምሪያ**

1.1 ርእስን በሚገባ ማስተዋል፤

1.2 ርእሱን በሚመለከት ረገድ፤

1.2.1 ወደ ቤተ መጽሀፍት በመሄድ በርእሱ የተዘጋጁ ልዩ ልዩ ጽሁፎችን በማንበብ ፍሬ ሃሳቦችን ሰብስብ::

1.2.2 ስለ እርሱ የላቀ እውቀት ካላቸው ሰዎች ጋር በቀዳሚያ በመነጋገር ፍሬ ነገሮችን ጨብጥ::

1.2.3 የሰበሰብካቸውን ነጥቦች በቅደም ተከተል አዘጋጅ::

1.2.4 ዝግጅትህ ከተደራሲያኑ ፍላጎት፤ ለምድና እውቀት ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን አጢን::

1.2.5 ዝግጅትህ ሁሉን የሚያሳትፍ፤ የሚያነቃቃና የሚገፋፋ መሆኑን አስተውል፤

1.2.6 ዝግጅትህ የርእስ ጉዳዩን የተለያዩ ገጽታዎች የሚዳስስ መሆኑን አስተውል::

1.2.7 ዝግጅትህ ወቅታዊ መሆኑን አረጋግጥ::

1.2.8 የዝግጅትህን ጠቃሚነት ገምግም::

2. **የውይይት አቀራረብ መምሪያ**

2.1 ለውይይት ስትቀርብ ሰበእናህን አሟላ:: ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል

2.1.1 አለባበስን

2.1.2 ንጽህናን

2.1.3 ሥነ ምግባርን

2.2 የውይይቱን አላማ አስተዋውቅ::

2.3 የውይይቱን ርእስ አስተዋውቅ::

2.4 የውይይትህን ጭብጥ በቅደም ተከተል ለተደራሲያኑ አቅርብ::

2.5 ውይይትህን በምታቀርብበት ጊዜ ለተደራስያን እንደሰማ —ኳ ባለ ድምጽ ተናገር::

2.6 ውይይትህን በምታቀርብበት ጊዜ ሳትፈራና ጊዜየለሽ ሳትሆን ስርአት ባለው መንገድ ውይይትህን አቅርብ::

2.7 የውይይትህ ሃሳብ ተቀባይነትን እንዲኖረው በቂ ምክንያትና ማስረጃ አቅርብ::

2.8 በተቻለ መጠን ተደራሲያንን በአንሻለጽህ አርካ::

2.9 ውይይትህ ፍሬያማ እንዲሆን ጥረት አድርግ::

2.10 ውይይትህ ፍሬ ሃሳብ ካቀረብክ በኋላ ለተደራስያን የጥያቄና የአስተያየት መስጫ ጊዜ እንዲኖር አድርግ::

2.11 ውይይትህ በተወሰነው የጊዜ ገደብ እንዲያበቃ አድርግ::